

«የሪፖርቱ» ዓላማ በሰብአዊ መብት ሰበብ የኢትዮጵያ መንግስትን ወከባ ውስጥ መክተት ነው»

ገጽ 6

"ሰው በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነው"

ገጽ 11


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 021 መስከረም 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




የኢሬቻ በዓል አከባበር



አቶ ሽመልስ አብዲሳ

## ኢሬቻ የሰላም እና የወንድማማችነት አርማ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኢሬቻ የኦሮሞ ታላቅነት የሚታይበት መድረክ የሰላምና ወንድማማችነት ምልክት ነው ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ።

አቶ ሽመልስ አብዲሳ የኢሬቻን በዓል አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ባህል የማንነት፣ የኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ሥርዓት እንዲሁም የአመጋገብና አለባበስ ሥርዓት መገለጫ ነው ብለዋል።

ኢሬቻ ባህል፣ ታሪክና ፈጣሪ የሚመሰገንበት ታላቅ፣ ታናሽ፣ አዛውንት፣ ወንድና ሴት ሳይል በአንድነት ወደ ወንዝና ተራራ ወጥቶ እርቅ፣ ይቅርታ መልካም ምኞትና

ኢሬቻ የሰላም ... ወደ ገጽ4 ዞሯል

## «የኢሬቻ በዓል ምሰሶ የሆኑት ሰላም፣ ፍቅር፣ ወንድማማችነትና አንድነት ሁሌም ሲታወሱና ሲተገበሩ ይገባል»

- ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ዋቅሹም ፍቃዱ



አዲስ አበባ፡- «የኢሬቻ በዓል ምሰሶ የሆኑት ሰላም፣ ፍቅር፣ ወንድማማችነትና አንድነት ሁሌ ሊታወሱና ሊተገበሩ ይገባል ሲሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገለጹ።ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢሬቻ ክብረ በዓልን አስመልክተው የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ታድጎን፣ በትንሾቹና በትላልቆቹ ጠላቶቻችን ላይ ድል ሰጥቶን ወደ ብርሃኑ ወቅት ያሸጋገረን ፈጣሪ ምስጋናው የላቀ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ እንኳን ለብርሃን ወቅት በሰላም አደረሳችሁ ብለዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ ከገዳ ሥርዓት በወረሳቸው ትሩፋቶች የክረምቱን ድቅድቅ ጨለማ አልፎ የፀደይ ብርሃን ወቅት ሲገባ ክረምቱን ያሳለፈ፣ ሰብልን ያበቀለ፣ ማሳውን በልምላሜ ያስጌጠ ፈጣሪውን እርጥብ ሳር በመያዝ ወደ ወንዝ ወርዶ «ማሬሆ..ማሬሆ..ማሬሆ» እያለ ያመሰግነዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኢሬቻ በዓል ጨለማው አልፎ በብርሃን ወቅት የሚሆን ታላቅ የምስጋና በዓል በመሆኑ ሁሉም የኦሮሞና የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንኳን አደረሳችሁ ስል በታላቅ ደስታ ነው ብለዋል።

ፈጣሪን ለማመስገን ወደ ወንዝ የሚወርዱ ታዳሚዎች በእጃቸው የያዙትን እርጥብ ሳር በወንዙ ላይ ከማሳረፋቸው በፊት አባ ገዳዎች፣ «እርስ በራሳችሁ ሰላም ናችሁ?» ፣ «ከፈጣሪያችሁ ሰላም ናችሁ?» ፣ «ለፍጥረት ሰላም ናችሁ?» የሚሉ ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ ያሉት ዶ/ር ዐቢይ፣ ታዳሚውም «ሰላም ነው» በማለት የምስጋና ሥነ ሥርዓቱን እንደሚያከናውን አስገንዝበዋል።

ስለዚህ ሰው ሁሉ ከዚህ ሥርዓት በመማር ፈጣሪን ለማመስገን ወደ ወንዝ ሲወርድም ሆነ አመስግኖ ሲመለስ ሰላም ማውረድ ይጠበቅበታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በኢሬቻ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርበው የተፈጥሮ ሕግ ተዛብተው ፍጥረት እንዳይጎዳ ከመሆኑም ባሻገር በዓሉ የሰላም፣ የአብሮነት፣ የምህረትና የፍቅር አርማ መሆኑን አመልክተዋል።

«የኢሬቻ በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


















ክልሉ ለመከላከያ ሰራዊት ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አደረገ

ገጽ 4

የኢትዮጵያን የቅርስ ክምችት የሚመጥን ሙዚየም ሊገነባ ነው



ገጽ 4

# ሕይወቱን ለአገር ለሚገብር ሰራዊት ደም መለገስ ትንሹ ስጦታ ነው

## - ኢፕድ ለሰራዊቱ የአንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍም አድርጓል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ሕይወቱን ለአገር ለሚገብር ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት ደም መለገስ ትንሹ ስጦታ መሆኑን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኛና አመራሮች ገለጹ። የድርጅቱ ሠራተኞች «የማይተካ ሕይወቱን ለሚሰጠን ሰራዊታችን የሚተካውን ደማችንን እንሰጣለን» በሚል መሪ ቃል በትናንትናው ዕለት ለጀግናው መከላከያ ሰራዊት ደማቸውን ለግሰዋል።

የድርጅቱ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንድም ተክሉ በደም ልገሳው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለፁት፤ በሕይወት መስዋዕትነት አገርን ለሚያቆመው ጀግናው መከላከያ ሰራዊት ደም መለገስ በጣም ትንሹ መስዋዕትነት ነው።

እንደ አቶ ወንድም ንግግር፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ቀዳሚ በመሆን አገሩን በማገልገል ላይ የሚገኝ አንጋፋ ድርጅት ሲሆን፤ በተለይም በህልውና ዘመቻው ላይ ጁንታው አገር ላይ ያደረሰውን ጉዳት በመረዳት ሠራተኞች የወር ደመወዛቸውን እስከመስጠት ደርሰዋል።

የድርጅቱ የይዘት ዘርፍ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በበኩላቸው፤ ሕይወቱን ያለስስት ለሚገብረው ጀግናው ሰራዊት ደም መለገስ ማለት ከሰራዊቱ ጎን መሆኑን ማሳያና ሠራተኛና አመራሮቹም ለአገራቸው የሚሰስቱት እንደሌለ አመላካች መሆኑን



የኢፕድ ሠራተኞችና አመራሮች ለአገር መከላከያ ሰራዊት ደም ለግሰዋል

ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አሸባሪው ትህነግ የሚያደርጋቸውን አገርን የማጥፋት ተግባራት ከስር ስር እየተከታተለ የማጋለጥ ሥራን ሲሠራ መከረሙን የተናገሩት አቶ ፍቃዱ፤ ድርጅታቸው ሁልጊዜ ለአገር ጥቅም በሚቆሙ ሥራዎች ሁሉ ላይ ተሳታፊ መሆኑንም አመላክተዋል።

የመሥሪያቤቱ ጋዜጠኛ እስማኤል አረቦ በበኩሉ፤ ውድ ሕይወቱን ሳይሰስት ለሚሰጠው ሰራዊት ውድ የሆነውን ስጦታ መስጠት የሚያኮራ ነገር በመሆኑ የዚህ አካል በመሆኔ ኩራት ይሰማኛል ብሏል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አገራዊ ጥሪውን ተከትሎ የመከላከያን ጀብዱ ግንባር ድረስ ሄዶ ከመዘገብ ባሻገር የወር ደመወዙን የአገርን ዳር ድንበር ለሚያስከብረው የመከላከያ ሰራዊት በመስጠት ከአገሩ ጎን መቆሙን በተደጋጋሚ ማስመስከሩንም ጋዜጠኛው አውስቷል።

የድርጅቱ ጋዜጠኛ ወይዘሮ ምህረት ሞገስ በበኩሏ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አገር በምትፈልገው ጊዜ ሁሉ ከአገሩ ጎን በመቆም የጀግንነት ተግባርን ሲፈፅም ቆይቷል፤ ደም ልገሳውም የዚህ እርምጃው አካል ነው ብላለች።

ወይዘሮ ምህረት ሠራተኛና አመራሮች ደማቸውን መለገሳቸው ጀግናው መከላከያ ሰራዊት ከሚያበረክተው አስተዋፅዖና መስዋዕትነት አንፃር ደም መለገስ ቀላል ነገር መሆኑን ገልጻለች።

መርሀግብሩን ያስተባበረው የድርጅቱ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጉዳይ ክፍል ተጠባባቂ ኃላፊ ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ በበኩላቸው፤ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት እየሰጠ ለሚገኘው የመከላከያ ሰራዊት ደሙን መለገሱ የሚያኮራ ተግባር መሆኑን ገልፀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሌሎችም ማህበራዊ ኃላፊነትን የመጠበቅ ተግባራት ላይ በንቃት በመሳተፍ ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ኃላፊዋ፤ ድርጅቱ ለሰራዊቱ የአንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉንም ተናግረዋል።



# ኢሬቻ መቻቻልንና ወንድማማችነትን የሚያጎለብት የኢትዮጵያውያን እሴት ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል መቻቻልንና ወንድማማችነትን የሚያጎለብት የመላ ኢትዮጵያውያን እሴት መሆኑን የኦሮሞ አባ ገዳዎችና ሃደ ሲንቄዎች ገለፁ።

የኦሮሞ አባ ገዳዎችና ሃደ ሲንቄዎች በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ የኢትዮጵያውያን የራሳቸው የሆነ ወግና ባህል ያላቸው ሕዝቦች እንደመሆናቸው መጠን ባህሎቻቸውን ሲያከብሩ እርስ በእርስ በመቻቻልና በመፈቃቀር ለበርካታ ዘመናት በሰላም ያሳለፉ ናቸው።

የቱለማ አባ ገዳና የኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረት ፀሐፊ ጎበና ሆላ የኦሮሞ ሕዝብ የሞጋሳ፣ ጉዲፈቻ እንዲሁም የሌሎች በርካታ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያስተሳስሩ ባህሎች ባለቤት በመሆኑ ከሌሎች ኢትዮጵያውን ሕዝቦች ጋር ተጋምዶ የሚኖር ሕዝብ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢሬቻ ክብረ በዓል በሁለት ወቅቶች የሚደረግ መሆኑን ያስታወሱት አባ ገዳ ጎበና፤ በበልግ ወቅት በተራራዎች ላይ ዝናቡን የሰላምና የልምላሜ እንዲያደርግ የሚማፀኑበት፤ በፀደይ ወር ደግሞ በመልካዎች በመገናኘት ክረምቱን በሰላም ማለፉን የሚያመላክት የምስጋና በዓል መሆኑን አመልክተዋል።

በዚህ ቀንም ከተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ብሔርና ብሔረሰቦች የሚገኙበት በዓል በመሆኑ የሕዝቦች አንድነት የሚንፀባረቅበት፣ ባህሎቻቸውንም የሚለዋወጡበት መሆኑን ተናግረዋል።

ያሁኑ ትውልድ ይህን በዓል ሲያከብር የኢትዮጵያን ባህልና ማንነቱን በተገቢው በመረዳት የአፍሪካ ተምሳሌት የሆነችውን አገር በመጠበቅ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል ብለዋል።

የቱለማ አባ ገዳዎች ህብረት አባ አለንጋ የሆኑት አባ ገዳ ሲሳይ ታደሰ በበኩላቸው፣ የኢሬቻን በዓል ለማክበር ወደ ክብረ በዓሉ ስፍራ የሚመጣ ማህበረሰብ በአንድነትና በፍቅር ጠባቂ ሳያስፈልገው እርስ በርሱ በመጠባበቅ በዓሉን ማሳለፍ እንደሚገባው ተናግረዋል።

የኢሬቻ በዓል ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበርና አገርም እንደ ሌሎች ክብረ በዓላት ሁሉ ከዚህ በዓልም ተጠቃሚ እንደትሆን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባው ገልፀው፣ በዓሉን የፖለቲካ ማራመጃ መድረክ የሚያደርጉ ማናቸውም ቡድኖች ከዚህ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ጠይቀዋል።

የቱለማ ሀደ ሲንቄ ወይዘሮ አፀዱ ቶላ ሃደ ሲንቄዎች ሰላምን የሚያበስሩበት እርጥብ ሳር፣ እርቅን የሚያወርዱበት በትር (ሲንቄ) እንዲሁም ወተት በቅል 'ኤሌምቱ' በመያዝ ከአባ ገዳዎች ፊት 'መሬዎ...' በማለት ሰላምን በመስበክ ወደ ኢሬቻ ስፍራ የሚሄዱ መሆኑን ገልፀዋል።

በመሆኑም ሁሉም ብሔርና ብሔረሰቦች እንደ ሌሎች የአደባባይ በዓላት ሁሉ በኢሬቻ በዓል ላይ መሳተፍ እንደሚፈልጉ ገልፀው፣ የኦሮሞ ሕዝብ በበዓሉ ፍቅርን በማሳየት የሚመጡ እንግዶችን በሥርዓቱ በመቀበል እንቅፋት ሳይመታቸው አክብረው እንዲመለሱ የራሱን አስተዋፅኦ እንዲወጣ ጠይቀዋል።

# በዓላቱ የሕዝቡን አንድነትንና አብሮነት የማጠናከር ዕሴታቸው የጎላ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የመስቀል ደመራ፣ ያሆዴ፣ ጊፋታ፣ መስቀላዮ፣ ኢሬቻ እና የመሳሰሉት የአደባባይ በዓላት የሕዝቡን አንድነት እና አብሮነት የማጠናከር ዕሴታቸው የጎላ ነው ሲሉ የዘርፉ ምሁራን ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከፍተኛ ባለሙያ መምህር መኩብብ ገብረማርያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ እነዚህ በዓላት በተለያዩ ዝግጅቶችና ሰፋ ያለ የኅብረተሰብ ክፍል ባካተተ መልኩ የሚከበሩ በመሆናቸው የሕዝቡን አንድነት እና አብሮነት የማጠናከር ዕሴታቸው የጎላ ነው።

በዓላቱ አብሮ ከመብላት፣ ከመጠጣትና ልዩ ድባቦችን ከመፍጠር ባለፈ ወዳጅነትን በማጠናከር እና ወንድማማችነትን በመፍጠር ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ያሉት መምህር መኩብብ፤ በዓላቱ በአደባባይ የሚከበሩ መሆናቸው ደግሞ የሰዎች ትስስር እንዲጠናከር ከፍተኛ ሚና አላቸው ብለዋል።

በመስቀል ደመራ፣ ያሆዴ፣ ጊፋታ፣ መስቀላዮ፣ ኢሬቻም ሆነ ሌሎች የአደባባይ በዓላት አከባበር ላይ ከበዓላቱ አስቀድመው የተለያዩ ዝግጅቶች ስለሚኖሩ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን መስተጋብር በማስፋት ትስስርን የሚያጠናክሩ ናቸው። በተጨማሪም ከሌሎች አካባቢዎች የሚኅበኙ ሰዎች መኖራቸው አንድነትን ለማጠናከር በር ይከፍታልም ብለዋል።

በነዚህ በዓላት በተለይ በአንዳንድ አካባቢዎች የተጣሉ ሰዎች እንዲሳተፉ ስለማይደረግ መታረቂያ አውዶች ጭምር ናቸው ያሉት መምህር መኩብብ፤ ይህ ደግሞ በዓላቱን ቂምና በቀል፤ ጥላቻና ቁርሾ እንዳይኖር እና ወንድማማችነት እንዲጠናከር የሚረዳ አገር በቀል በዓላት መሆን ያስቻላቸው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ መምህር መኩብብ ገለፃ፤ በዓላቱ የማኅበረሰባዊ መስተጋብር ምንጭ እንደሆኑ ሁሉ በተለያዩ መንገዶች በማሳደግ ልንጠቀምባቸው ይገባል። ከኢኮኖሚ ጋር በማስተሳሰር የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ጎን ለጎን ማሳደግ በዓላቱ እንዲያድጉ ይረዳል። ለመስቀል በዓል መቅረብ የሚገባቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲሁም በኢሬቻ በዓል ላይም በተመሳሳይ ቀርበው ሊሸጡ የሚችሉ ነገሮችን ማኅበረሰቡን በማስለመድ ወደ ኢኮኖሚ ጭምር ማሳደግ ይገባል።

በተጨማሪም የአንዱ አካባቢ ማኅበረሰብ ወደ ሌላው በዓሉ ወደ ሚከበርበት አካበቢ እንዲንቀሳቀስና የአገር ውስጥ ቱሪዝሙ እንዲነቃቃ ማድረግም ለበዓሎቹ ዕድገትና መነቃቃት አስተዋፅዖ ስለሚያደርግ ትኩረት ተደርጎ ሊሠራ ይገባል ሲሉ ገልፀዋል።

በዓላቱን ከአለባበስ፣ ከዜማ፣ ከእንቅስቃሴና ከመሳሰሉት በመውሰድ ኪነጥበባዊ ዕሴታቸውን ማዋረስም እንደሚያስፈልግ እና መጻሕፍት፣ የፎቶ ኤግዚቢሽኖች፣ ፊልሞችና ሌሎችም በበዓላት ዙሪያ በመሥራት እንዲዳብሩ ማድረግ ይገባልም ብለዋል።

በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎርና ሥነ ጽሑፍ መምህር ደርብ ጌታቸው በበኩላቸው፤ የመስቀል እና ኢሬቻ በዓላት አብሮነትንና አንድነትን ከማጠንከር አኳያ ሰፊ ሚናን ይጫወታሉ ብለዋል።

በኢትዮጵያ በተለይ የአደባባይ በዓላት ሃይማኖታዊ እና ዕምነታዊ መሠረት ስላላቸው ያላቸው ሕዝባዊ መሠረትም በዚሁ ልክ ሰፊ ነው ያሉት መምህር ደርብ፤ ቁጥራቸው ከፍ ያለ የማኅበረሰብ ክፍሎች ማሳተፋቸው ደግሞ ለአብሮነትና ለአንድነት መጠናከር ሚናቸውን ለመወጣት ዕድል ፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

በጊዜ ደረጃም ረዘም ያለ የዝግጅት እና የማክበሪያ ጊዜያት ስለሚወስዱ የማኅበረሰቡን ተግባቦት እና ግንኙነት በማሳደግ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉም ሲሉ ገልፀዋል።

በደቡብ ክልል ጉራጌ አካባቢ የሚከናወነውን የመስቀል በዓል ለማሳያ ያነሱት መምህር ደርብ፤ አካባቢው የሚከበረው የመስቀል በዓል የማኅበረሰቡን ግንኙነት ከዓመት እስከ ዓመት የሚያጎለብት ሆኖ እናገኘዋለን ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ መምህር ደርብ ገለፃ፤ በጉራጌ አካባቢ የቂቤ፣ የገንዘብና የመሳሰሉ መዋጮዎች ስለሚኖሩ በየወሩ የማኅበረሰቡን ግንኙነት የሚያበለፅግ ነው። ይህ ኅብረተሰቡ አንድነቱና አብሮነቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚያስችል ትልቅ ዕሴት ነው ብለዋል።

በተጨማሪም በበዓላቱ ፀብ እና ቂም ያለበት መሳተፍ አለመቻሉ እና አስቀድሞ ዕርቅ የሚፈጠር መሆኑ ደግሞ የበዓላቱ ዕሴቶች የአብሮነትና የአንድነት ምሰሶን እንዴት እንደሚያጠናክሩት የሚያሳይ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ቱባ ባሕሎቹ በተቻለ መጠን በሌላ ባህል እንዳይዋጡ በማድረግ በዓሎቹን ማጠንከር ይገባል ያሉት መምህር ደርብ፤ በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የኦሮሞ አባቶች ልጆቻቸውን በፈረስ ይዘው በዓሉን እንዲታደሙ ያደርጋሉ፤ ይህ ዓይነቱ ልምድ በዓላት ሳይበረዙ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ እና በዓሎችን ለማጎልበት የሚረዳ ነው ብለዋል።

ዜና

# ኢሬቻ ፤

# አብሮነትን በማጎልበት ዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ሚና የሚጫወት በዓል ነው

ውብሸት ሰንደቁ



አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል አብሮነትን በማጎልበትና ወንድማማችነትን በማጠናከር ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በዓል ነው ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ኢሬቻ ከማመስገን አልፎ አንድነት የሚፀናበት አገራዊ ሀብት ነው፡፡ የኢሬቻ ባህላዊ ዕሴትና የአከባበር ሥርዓት በኢትዮጵያ ወንድማማች እንዲጠናከር፤ አብሮነት እንዲጎለብት በማድረግ ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በዓል ነው፡ ፡

በኢሬቻ ዕለት ከተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች በተጨማሪ ከኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚሳተፉ የአንድ አገር ልጆች በአንድነት የሚሰባሰቡበት፤ በፍቅር የሚደምቁበትና የሚጠያየቁበት በዓል ነው ያለው መግለጫው፤ ኢሬቻ በአንድ ቦታ፤ የአንድ አገር ልጆች ተሰባስበው አገራዊ ዕሴታቸውን የሚያዳብሩበት የህብረት መገለጫም ነው ብሏል፡፡

ኢሬቻ እንደ በአገር ደረጃ ካሉ ቅርሶች አንዱ ሲሆን የማይዳሰስ ቅርስ ተደርጎ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት ዩኔስኮ የተመዘገበው የገዳ ሥርዓት አካል በመሆኑ የአገር ሀብት መሆኑን በመጥቀስ በዓሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች የሚታደሙት መሆኑንም አትቷል፡፡

በኢሬቻ በዓል ሴቶች፣ ወንዶች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች እና ሃደ ሲንቄዎች በውብ አለባበስ ደምቀው የሚያከብሩት የውበት በዓል በሆኑ ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት እየሆነ ነውም ብሏል፡፡

ኢሬቻ ለሕብረብሔራዊ አንድነት ግንባታና አብሮነት ዓይነተኛ ሚና ያለው ቅርስ ነው ያለው መግለጫው፤ በመሆኑም ባህላዊ ዕሴቶቹ ተጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፍ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መውጣት እንደሚገባው አሳስቧል፡፡

ኢሬቻ ምሥጋና የሚቀርብበት ብቻ ሳይሆን የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የእርቅና የሰላም በዓልም በመሆኑ የኢሬቻ ቀን ከመድረሱ በፊት የተቀያየመና የተጣላ ታርቆ፣ ይቅር ተባብሎና ቂም በቀልን አስወግዶ ፈጣሪውን እያሰበ ከወዳጅ ዘመዶች ጋር የሚከበር በዓል መሆኑን መግለጫው አሳውቋል፡፡

በበዓሉ አደይ አበባ እና እርጥብ ሳር ተይዞ በአባ ገዳዎች እና ሃደ ሲንቄዎች ዝማሬ የሚሰማበት፤ የተለያዩ አካባቢ ወጣቶች ባህላዊ ጭፈራና ዘፈን የሚያሳዩበት ባህላዊ የጥበብ መድረክ በመሆኑ ከአገር ውስጥና ከውጭ በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ ለአገር ኢኮኖሚ መነቃቃት ከፍተኛ ድርሻ የሚጫወት መሆኑም ተገልጿል፡፡

የኢሬቻ በዓል ከአገር አልፎ የዓለም ሀብት በመሆኑ፤ የቱሪዝም ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ማክበር ያስፈልጋል ያለው መግለጫው የበዓሉ ዕሴት ሳይበረዝ እንዲቀጥል ባለቤት የሆነው መላው ሕዝብ የበዓሉን ዕሴት ሳይለቅ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት እንዲያከብረው መንግሥት ጥሪውን ያቀርባል ብሏል፡፡

የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ሕዝብ ክረምት አልፎ ፀደይ በክረምቱ ወራት ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ ሲገናኝ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን ላሸጋገረው አምላክ ምሥጋና የሚያቀርብበት እና ለብዙ ሺህ ዘመናት ሲከናወን የቆየ አገራዊ ትውፊት ነው፡፡

# የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር ሥር ዋሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ከባድ የግድያ፣ የውንብድና እና የዘረፋ ወንጀልን ሲፈጽሙ የነበሩ የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር መዋላቸውን የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ገለፀ።

የሽብር ተልዕኮ ተቀብለው በንፁሃን ዜጎች ላይ ሦስት የግድያ፣ አንድ የመግደል ሙከራ፣ 46 በጦር መሣሪያና በድምጽ አልባ የስለት መሣሪያዎች የታገዘ የዘረፋና የውንብድና ወንጀሎችን በመፈፀም ኅብረተሰቡ በሥጋት እንዲኖር ሲያደርጉ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የጋራ ግብረ-ኃይሉ ገልጿል፡፡

ከሕወሓት የሽብር ቡድን ጋር በመቀናጀት በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሞጆ፣ በዝዋይ፣ በሻሸመኔ፣ በቱሉቦሎ፣ በወሊሶ፣ በቡታጅራና በወልቂጤ በሚወስዱ መንገዶች ላይ በአራት ቡድን ተደራጅተው የፌዴራልና የክልል የፀጥታ አካላትን የደንብ ልብስና አንፀባራቂ ልብስ በመልበስ፣ ከፍተኛ የብርሃን ኃይል ያለው ፓውዛ እና በጦር መሣሪያ በመታገዝ ተሽከርካሪዎችን እያስቆሙ ከባድ የዘረፋና የግድያ ወንጀል ሲፈጽሙ የነበሩ የኦነግ ሸኔ አባላት በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ እነዚህም አብደላ ከድር፣ ቦና አያኖ፣ ታሪኩ ሲርባ ፣ ቃሲም ገመቹ፣ ዲታ ካሼ፣ መሐመድ አደም፣ ጫላ ወንድሙና ጀማል ከድር የተባሉ ተጠርጣሪዎች መሆናቸውን የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ጠቅሷል፡፡

እነዚህ ተጠርጣሪዎች የራይድ ተሽከርካሪዎችን በከፍተኛ ገንዘብ በመኮናተር ወደ ክልል ከተሞች በመውሰድ የተለያዩ ሰበቦችን በመፍጠር ካመሹ በኋላ በሌሊት ወደ አዲስ አበባ እንሂድ በማለት በጉዞ ላይ ሳሉ ጨለማና ጭር ያለ ቦታ ሲደርሱ አሽከርካሪውን በማስቆም የአሽከርካሪዎችን አንገት በስለት ወግቶ በመግደል በአሽከርካሪዎች ላይ አሰቃቂ ወንጀል መፈፀማቸውን ሁሉም ተጠርጣሪዎች አምነው የወንጀል ቦታውንና አፈፃፀማቸውን ለምርመራ ቡድኑ መርተው ማሳየታቸውን ገልጿል፡፡

በሽብር ተግባራት ላይ የተሰማሩት የሕወሓትና የሸኔ የሽብር ቡድኖች በአገር ላይ ግልጽ ጦርነት ከፍተው ንፁሃንን በጅምላ በመግደል ሕዝቡን ስሜት ውስጥ በማስገባት አገሪቱ ወደ ለየለት ብጥብጥ እንድትገባ ለማድረግ የሸረቡት ሴራ መሆኑን የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል ገልጾ፤ ይህ ሳይሳካላቸው ሲቀር በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የግድያና የዘረፋ ቡድኖች በማሰማራት የከተማ ውስጥ ሽብርና ጦርነት ለመፍጠር ሲቀንቀሳቀሱ እንደነበር ግብረ-ኃይሉ ደርሶባቸዋል ብሏል።

የሽብር ድርጊቱ ተሳታፊዎች በፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይሉ ብርቱ ክትትልና በኅብረተሰቡ መረጃ ሰጪነት ሁሉም የወንጀሉ ተሳታፊዎች በቁጥጥር ስር ማዋሉን ገልጾ፤ አዲስ አበባ እና ሌሎች የአገራችን ከተሞች ከመሰል የሽብር እና የወንጀል ድርጊቶች የመከላከልና ወንጀሎቹም ተፈጽመው ሲገኙ ተጠርጣሪዎችን በሕግ ቁጥጥር ሥር የማዋል ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ-ኃይል አሳስቧል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በሐረርና በድሬዳዋ በተለያዩ አካባቢዎች የአድራሻ ለውጥ እያደረገች የሸኔን የሽብር ቡድን በህቡዕ ስታደራጅ የነበረችው የሽብር ቡድኑ ከፍተኛ አመራር ጫልቱ መሐመድ አብዲ በቅጽል ስሟ (ጃል ቦንቱ ጉሚ) ተብላ የምትጠራው ተጠርጣሪ በሸኔ የሽብር ቡድን በኬንያ ሶሎሎ የውትድርና እና የካድሬ ስልጠና ወስዳ የሽብር ቡድኑን ተቀላቅላ ጃል ገመቹ አቦዬ ከሚባል የሸኔ ሽብር ቡድን ከፍተኛ አመራር ጋር እየተገናኘች ወጣቶችን በመመልመል ወደ ኬንያ ሶሎሎ ማሰልጠኛ እየላከች የሽብር ቡድኑን እንዲቀላቀሉ በማድረግና ኢትዮ-ኬንያ ድንበር ድረስ በመዘዋወር ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የሽብር ተግባር ስትፈጽም ቆይታ በቅርቡ በተደረገው ኦፕሬሽን በድሬዳዋ ከተማ ከ13 ግብረ አበሮቿ እና ኤግዚቢቶች እንዲሁም ከተለያዩ ምስጢራዊ ሰነዶች ጋር በቁጥጥር ሥር መዋሏን ግብረ-ኃይሉ ገልጿል።



## «የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በማስተዋወቅ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እየተሠራ ነው»

- አቶ ሽመልስ አብዲሳ
የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በማስተዋወቅ የቱሪዝም ኢኮኖሚን ይበልጥ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ተናገሩ። የኢሬቻ ሳምንት መርሃ ግብር አንድ አካል የሆነው የቱሪዝም ሽልማትና የኦሮሚያ ሚስ ቱሪዝም መርሀ ግብር በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

በዚህ መድረክ ላይ የተገኙት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የክልሉን የቱሪዝም ሀብት ለማስተዋወቅ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከቱሪዝም የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይበልጥ ማሳደግ እንደሚገባ ገልፀዋል።

ክልሉ ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት በመሆኑ ከዘርፉ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታችንን ለመጨመር በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት ይህንን ዓላማ በማንገብ ኮሚሽኑን አቋቁሞ ማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን የቱሪዝም መዳረሻዎችን በመለየት ከዚህ ዘርፍ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ምንጭ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት ናት ያሉት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ ይህን ሀብት በማቀናጀት በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘርፉን በማልማትና በማስተዋወቅ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ፋይዳ እንዲያስገኝ ይሠራል ብለዋል።

በሌላ በኩል የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የክልሉን ባህልና ታሪክ በማስተዋወቅና በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ተቋም መሆኑንና ማኅበረሰቡን ከዚህ ሴክተር ተጠቃሚ ለማድረግና ማግኘት ያለባቸውን ፋይዳ እንዲያገኙ ለማስቻል የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ በበኩላቸው ኮሚሽኑ የክልሉን ቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ በሚሠራቸው ዋና ዋና ተግባራት ትኩረት ሰተው ሲሠሩ የቆዩ ተቋማትና ግለሰቦችን አመስግነዋል፡፡

ኮሚሽኑ በኦሮሚያ ክልል ላይ ብቻ በማተኮር የሚሠራ ሳይሆን እንደ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ በመሆኑ ለዚህ ስኬታማነት የድርሻችሁን የተወጣችሁ ተቋማትና ግለሰቦች ልትመሰገኑ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢሬቻ ሳምንት አካል የሆነው የቱሪዝም ሽልማትና የኦሮሚያ ሚስ ቱሪዝም መርሀ ግብር ላይ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳና ሌሎች የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች አባገዳዎችና የተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦች ተገኝተዋል።

በሁለተኛው የኦሮሚያ ሚስ ቱሪዝም ውድድርም ሃዊ ማቲዎስ የ2015 ዓ.ም የኦሮሚያ ቱሪዝም አምባሳደር በሚል ተሰይማለች፡፡ በ2014 ዓ.ም የኦሮሚያ ሚስ ቱሪዝም አምባሳደር በመሆን ስታገለግል የቆየችው ሀሊማ አብዱልሽኩር በምሥራቅ አፍሪካ ኦሮሚያ ቱሪዝም አምባሳደር በመሆን ተሰይማለች፡፡

በቱሪዝም ዘርፉ እንዲሁም ኦሮሚያን በማስተዋወቅ ረገድ በዘመናቸው ከፍተኛ ሥራዎችን ሲሠሩና በጎ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ የቆዩ ግለሰቦች እንዲሁም ተቋማት የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ባዘጋጀው የዕድሜ ዘመን ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

# ክልሉ ስመከላከያ ሰራዊት ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አደረገ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ክልል አሸባሪው ትህነግ ሦስተኛውን ዙር ጦርነት ከጀመረ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ለአገር መከላከያ ሰራዊት ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አደረገ።

ክልሉ የአሸባሪ ሕወሓት ቡድን አገርን ለማፍረስ የጀመረውን የተደራጀ ዘመቻ ለመመከትና ከመከላከያ ሰራዊት ጎን መቆሙን ለማሳየት 20 ሚሊዮን ብር የጥሬ ገንዘብና ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የዓይነት ድጋፍ አስረክቧል።

ድጋፉን ያስረከቡት የሲዳማ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ኤልያስ እንደተናገሩት፤ የሲዳማ ሕዝብ ለመከላከያ ሰራዊት ድጋፍ ሲያደርግ ለ2ኛ ጊዜ መሆኑን በመጥቀስ በመጀመሪያ ዙር የተለያዩ የዓይነት ድጋፎች ማድረጉን አስታውቀዋል፡፡

የመከላከያ ሰራዊቱ የኢትዮጵያን ህልውና ለማስጠበቅና አሸባሪው ቡድን ለ3ኛ ጊዜ የከፈተውን ጦርነት ለመቀልበስ በሚያደርገው ተግባር አዲስ አመትን በማስመልከት ድጋፍ ማድረጉን ያስታወሱት



አቶ አሸናፊ፤ የአሁኑ ለሁለተኛ ዙር የተደረገ ድጋፍ ብለዋል፡፡ የክልሉ ሕዝብና መንግሥት በስንቅና በሞራል በመደገፍና ደጀንነታቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል።

ይሄ ድጋፍ በዋናነትም የሰራዊታችንና ጥምር ጦሩ እያደረገ ላለው እንቅስቃሴ አድናቆትን ለመግለጽ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ፤ ከጎናችሁ ነን፤ አይዟችሁ ጠንክሩ፣ በርቱ ለማለትና ለሰራዊቱ ደጀን መሆናችንን ለማረጋገጥ




ነው እዚህ የተገኘነው ብለዋል።

የሲዳማ ሕዝብ በኢትዮጵያ ጉዳይ የማይደራደርና መስዋትነትን ለመክፈል የተዘጋጀ ሕዝብ ነው ያሉት ኃላፊው፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነት የማይደራደርና ኢትዮጵያዊነቱ እስኪታወቅ ድረስ አስፈላጊውን ሁሉ የሚያደርግ ሕዝብ ነው ሲሉም አክለዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሊዊጂ እንደተናገሩት፣ የአሸባሪውን ሕወሓት አገር የማፍረስ እኩይ አላማ ለማክሸፍ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች እየተፋለሙት መሆኑን ገልጸው፣ በግንባር የተሰለፉትን በመደገፍና በየአካባቢው ሰላምና ፀጥታን በመጠበቅ ረገድ ሕዝቡ እያደረገ ያለው ተሳትፎ የሚደነቅ ነው ብለዋል።

የክልሉ ነዋሪዎች ለመከላከያ ሰራዊት የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ በትናንትናው ዕለትም ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ መደረጉን ጠቅሰዋል።

የክልሉ ሕዝብ እና መንግሥት ላደረገው ድጋፍ አመስግነው፣ ድጋፍ ያለው ሰራዊት ሁሌም አሸናፊ ስለሆነ የሽብር ቡድኑ የከፈተው ጦርነት በድል እስኪጠናቀቅ የመከላከያ ሰራዊቱን በስንቅና በሞራል የመደገፉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

ከተደረገው ድጋፍ 20 ሚሊዮን ብር የጥሬ ገንዘብና ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የዓይነት ድጋፍ መደረጉንም ገልጸዋል። የክልሉ ነዋሪዎች ላደረጉት ድጋፍም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

## «የኢሬቻ በዓል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የኢሬቻ በዓል በሀሳብና በተግባር የመታነጽ በዓል እንደመሆኑ መጠን በቀልና ስም ማጠልሸት የበዓሉ መገለጫ አለመሆናቸውን በማወቅ መታቀብ ያስፈልጋልበበዓሉ በተፈጥሮ ሕግ ዙሪያ ትምህርት በአግባቡ ስለሚሰጥ ፍትሕን ማጉደልና እውነትን መደበቅ ሕጉን እንደመጣስ ይቆጠራልበመሆኑም ሕዝቡ በፍጹም ንጹሕ ልብ ለምስጋና መቅረብ እንደሚጠበቅበትም ገልጸዋል።

በገዳ ሥርዓት አብሮነትና ወንድማማችነት ትልቁን ሥፍራ እንደሚይዙ ያብራሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ ከዚህ አንጻር አብረው መሥራትና አብረው መብላት፣ መደጋገፍና አብረው መቆምና ለፍትሕ በጋራ መታገል የጥንት እሴት በመሆኑ በእሴቱ መሠረት ሰው ሁሉ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በብሔርና በጾታ ሳይለያዩ በእኩል ማየትና መቅረብ አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል

ዛሬ ከአገር አልፎ በዓለም ደረጃ እውቅናን ያተረፉና ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በጋራ የሚያከብሩት እንደ ኢሬቻ ያሉ በርካታ ሕዝባዊ በዓላት እንዳሉን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በባህልና በሃይማኖት ተቻችለን በጋራ በሰላም እንድንኖር የሚያደርገን የጋራ እሴቶች ያለን ኩሩ ሕዝቦች ነን ብለዋል

በታሪካችን አንድ ሆነን በጠላቶቻችን ፊት ተሸንፈን አናውቅም፣ ጀግንነት እንጂ ባንዳነት መለያችን አይደለም፣ በግንባር ጦርነትም ሆነ በተደረገብን የሴራ ጦርነት በአንድነት ወጥተን በሁሉም ግንባር ድል አድራጊ መሆናችን የባለፉት አራት ዓመታት ተጋድሎ ማየት በቂ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሌሎች ግንባሮች ድል እንዳስመዘገብነው ሁሉ ዋና ጠላታችን ድህነትን ድል ለማድረግ ሁሉም በተሰማራባቸው የሥራ መስኮች ሁሉ በእልህና በቁጭት ተግቶ እንዲሠራ አሳስበዋል።

## ኢሬቻ የሰላም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ስኬት፣ ሰላምና ብልጽግና እንዲሁም አንድነት የሚበሰርበት ታላቅ የኦሮሞ ክብረ በዓል ነው ብለዋል።

ኢሬቻ የሰላምና የእርቅ ምልክት ነው ያሉት አቶ ሽመልስ አብዲሳ፣«የፈጣሪና ምድር፣ የፈጣሪና ፍጥረታት» እርቅ የሚበሰርበት ቦታም ነው ብለዋል በመልዕክታቸው።

የኀዘንና የደስታ እንዲሁም የአምልኮ ሥርዓትን የሚያመለክት መሆኑን ጠቅሰው፣ የባህል እድገት ከማህበራዊ ለውጥ ጋር ስለሚመጋገብ የሁሉም እድገት ባህል ነው ማለት እንችላለን ሲሉም ገልጸዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ የዓለም ፍልስፍና የሚረዳና ለአኗኗር ትርጉም የሚሰጥ ሕዝብ መሆኑንም በመልዕክታቸው ጠቅሰዋል።

የኦሮሞ ሕዝብ ባህል ለትውልድ እንዲሻገር የሚያደርግ ጠንካራ ሥርዓት የዘረጋ ሕዝብ ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ከፈጣሪ ጋር ያለው መቀራረብ ሥርዓት ያለውና የራሱን የዘመን አቆጣጠር መተንበይ የቻለ፣ ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ለዓለም ያበረከተ ታላቅ ሕዝብ ነው ብለዋል።

እንደ ኦሮሚያ ክልል ኦሮሞ ወደ የጥንቱ ባህሉ መመለስ አለበት ስንል አባቶቻችን ትናንት በዘረጉት መሠረት አጥንተን በእውቀት የታጀበ ለትውልዱ ዋስትና የሆነ ሥርዓት ማረጋገጣችን ነው ሲሉም ነው የገለጹት።

ባህልን ማበልጸግ፣ ጥበብን ማሳደግ፣ ቋንቋን ማልማት የኅብረተሰብን አኗኗር በማሻሻል ተወዳዳሪ ትውልድ ማፍራትና ፈጠራን በማስፋፋት የኦሮሚያ ክልል ማህበራዊ ልማት ግቦች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

«ሰው ከሰው ጋር ከታረቀ ነው ፈጣሪም ከሰው ጋር የሚታረቅ» የሚባለው፣ በኦሮሞ ባህል ቂም በቀል ተይዞ ወደ «መልካ» (ወንዝ) አይኬድም ነው ያሉት። ኦሮሞ ወደ «መልካ» ሲሄድ ጥላቻን በፍቅር፣ ቂምን በይቅርታ አልፎ ሲገነባ የነበረው ጠንካራ የማህበራዊ ግንኙነት ለመግለጽ መሆኑንም አንስተዋል።

ኦሮሞ ወደ ጥንቱ ባህሉ ተመልሶ የተጣላ በማስታረቅ የሰላምና እርቅ መንገድንም እንደሚመርጥ ጠቅሰው፣ ሰላምና እርቅን የኑሯችን መሠረት አድርገን በመካከላችን ሰላም ለመፍጠር ይቅር መባባል አለብንም ነው ያሉት።

ኢሬቻ የኦሮሞ ታላቅነትን የሚያሳይ፣ የብሔር ብሔረሰቦች አንድነትና ወንድማማችነት ምልክት መሆኑን ጠቅሰው፣ ባለፉት ሥርዓት ተቀብሮ ተደብቆ ቢቆይም በተደረገ ተጋድሎ የተደበቀ ባህል ወጥቶ የተረሳ ታሪክ ተመልሷል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው እንዳሉት ኢሬቻ ከኦሮሞ ውስጥ ይመንጭ እንጂ ስለአብሮነት የሚሰበክበት፤ አብሮነት ከንግግር ባለፈ በተግባር የሚኖርበት መሆኑን እያስረፀ የመጣበት ነው፡፡

ኦሮሞ በኢሬቻ ፈጣሪን ያመሰግንበታል እንጂ ተፈጥሮን አያመልክም ብለዋልዋቃ ኡማ ኡመማ፤ ማለት የተፈጥሮ ፈጣሪ፤ ተፈጥሮን የፈጠርክ አምላክ ምስጋና ይገባሃል፤ ውሃውን የደፈረሰውን አጥርተህልናልና እናመሰግናለን፤ እኛም ታርቀን ሰላም ሆነን፤ «ገራ ቁልቁሉ» ሆዳችን ንፁህ አድርገን ተሰብስበናልና እባክህ ንፁህ አድርገን፣ ታረቀን በማለት በባህላዊ መንገድ ልመናቸውን የሚያቀርቡበት እሴት ነው ብለዋል።

ይህ እሴት የመላው ኢትዮጵያውያን እሴት ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በገዳ ሥርዓት ምክንያት ከእኛም አልፎ ለዓለም ሕዝብ ያስተዋወቀን ነው ብለዋል።

እንደ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማ አስተዳደሩ በጠቅላላው የኢሬቻ በዓል ማክበር ከጀመረበት 4 ዓመት ወዲህ ባህሉን ለማሳደግና ግንዛቤ ለመፍጠር ሰፋፊ ሥራዎችን መሥራቱን አውስተዋል።

በ5ቱም በር እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ከተማዋን በማሳመርና በማድመቅ፤ ኢሬቻ የሰላም ነው፤ የወንድማማችነት ነው በማለት ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራን ነው ብለዋል።



# የኢትዮጵያን የቅርስ ክምችት የሚመጥን ሙዚየም ሊገነባ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ያለውን የቅርስ ዓይነት፣ ስብጥርና ክምችት የሚመጥን ሙዚዬም በአዲስ አበባ ሊገነባ መሆኑ ተጠቆመ፡፡

ሰሞኑን በብሔራዊ ሙዚየም በተካሄደው የቅርሶች ቋሚ አውደርዕይ መክፈቻ መርሃ-ግብር ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሣህለ-ወርቅ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ያላትን የቅርስ ሀብት ዓይነት፣ ስብጥርና ክምችት የሚመጥን ሙዚየም የላትም፡፡

በመሆኑም ይህንን ችግር ሊፈታ የሚችልና እንደ አገር ያለውን የቅርስ ሀብት ዓይነት፣ ስብጥርና ክምችት የሚመጥን ሙዚየም መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡

የሚገነባው ሙዚየምም በቅርስ ጥናትና ጥበቃ የስብስብ ክፍል የሚገኙ ዘመን ያስቆጠሩ የአርኪዮሎጂ ግኝት ስብስቦችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ፣ ለማኅበረሰቡ ለማሳወቅና ለማስጎብኘት የሚያስችል ደረጃውን የጠበቀና ለማስጎብኘት በቋሚነት ክፍት የሚደረግ እንደሚሆንም ፕሬዚዳንቷ ተናግረዋል፡፡

ለሚገነባው የሙዚየም ግንባታ እውን መሆንም ሁሉም የበኩሉን ርብርብ ሊያደርግ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵያን ቅርሶች በማሰባሰብ፣ በመጠገን፣ በመጠበቅ፣ በማጥናት እንዲሰበሰቡ እገዛ እያደረጉ ላሉት የፈረንሳይና ሌሎች አገራትም ፕሬዚዳንቷ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ረሚ ማሪሾ ባደረጉት ንግግር፣ በኢትዮጵያ የሚሠሩ ሁለንተናዊ የቅርስ ጥናት፣ ምርምር፣ ጥበቃ፣ ክብካቤ ሥራዎችን ላይ የፈረንሳይ መንግሥት ለዘመናት ሲያደርገው የነበረው እገዛ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

የሁለቱ አገራት ግንኙነት ለ125 ዓመታት የዘለቀ መሆኑን የገለጹት ረሚ ማሪሾ፣ ለቅርስ ዘርፉ የተሰጠው ትኩረትም በአገራቱ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

የፈረንሳይ መንግሥት የኢትዮጵያ የቅርስ ምርምር፣ ጥናትና ጥበቃ ሥራዎች ላይ በአርኪዮሎጂ ጥናትና ምርምር ሥራ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የፈረንሳይ መንግሥት በኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል በመክፈትም በተለያዩ ዘርፎች ምርምር እንዲካሄድ አግዟል ብለዋል፡፡

በተጨማሪ በቅርስ ምርምር ዙሪያ በሁለቱ አገራት መካከል አሁንም ጠንካራ ግንኙነት ያለ መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፣ ከታሪካዊ ግንኙነቱ በመነሳት ወደፊት ቅርሶችን በማልማት ዙሪያ ብዙ መሥራት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

የፈረንሳይ መንግሥትም ከመቼውም በላይ በኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃና ልማት ዙሪያ እንደሚሠሩ አመላክተዋል፡፡

አምባሳደር ረሚ ማሪሾ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙትን ቅርሶች በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም (ዩኔስኮ) እንዲመዘገቡ ለማድረግ እንደሚሠሩም ገልጻዋል፡፡

በሌላ በኩልም የፈረንሳይ መንግሥት የላሊበላንና የብሔራዊ ቤተ መንግሥትን ጥገና እና ማልማት በተመለከተ እያደረገ ያለው ድጋፍ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፈረንሳይ መንግሥት የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ጥገና ትኩረት ሰጥቶ በቅርብ ከፍጻሜ እንዲያደርሰው ቃል ገብተዋል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በበኩላቸው፣ በኢትዮጵያ ያለውን የቅርስ ዓይነት፣ ስብጥርና ክምችት የሚመጥን ሙዚዬም መገንባት ለዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያን የዓለም ሕዝብ ሁሉ ባላት የቅርስ ዓይነት፣ ስብጥርና ክምችት ሊጎበኛት ይገባል ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፣ ኢትዮጵያ የብዙ አስደናቂ ቅርሶች ባለቤት የሆነች በመሆኗ እነዚህን ቅርሶች ለማስቀመጥና ለዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ለማስጎብኘት የሚያስችል ዘመኑን ደረጃውን የጠበቀ ሙዚየም መገንባቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውም ገልጸዋል፡፡





**አቶ ጉዮ ገልገሎ**
**የኦሮሚያ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ ሀላፊ**

Biiroo Misooma Magaalaa fi Manneenii Oromiyaa
የኦሮሚያ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ
Oromia Urban Development and Housing Bureau

# እንኳን ለ2015 ኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ መልዕክት

ኢሬቻ ከገዳ ሥርዓት እሴቶች አንዱ ነው። በበዓሉም ፈጣሪ ከጨለማ ወደ ብርሀን ስላደረሰን ምስጋና የምናቀርብበት፣የሰላምና የዕርቅ፣የፍቅርና የወንድማማችነት እንዲሁም የኦሮሞ ህዝብን አንድ ያደረገ ፈጣሪን የሚያመሰግንበት በዓል ነው።

ኦሮሞ የአንድነታችን ዕሰቶች በማጠንከር ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካ ቀንድን ለመገንባት ትልቅ አቅም ያለው ህዝብ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያን ወደ ብልፅግና ለማሻገር ፈተና ቢገጥመንም፤ ችግሮች ከመሰረታቸው ለመፍታት በሚቻል ሁኔታ እየተሰራ ይገኛል። በውስጥና በውጭ የገጠሙንን ፈተናዎች በመጋፈጥ ትላልቅ የልማት ስራዎችን በመስራት የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመፍታት የህዝቦቻችንን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሰራ ነው። እየተሰሩ ካሉት ስራዎች የከተማ ልማት ስራዎችን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል። ለአብነት ዕውቅና ባላቸው 717 የኦሮሚያ ከተሞችን ለኑሮ ምቹና ዜጎች በደስታ እንዲኖሩባቸው ለማድረግ ትላልቅ ግቦችን በመያዝ እየተሰራ ይገኛል።

በ2014 ዓ.ም የኦሮሚያ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ የተለያዩ ግቦችን በማስቀመጥ ሲሰራ እንደነበረ እና የላቀ ስኬቶችን ያስመዘገበበት ዓመት ነበር። የኢንሼቲቭ ስራዎችን በመለየት በልዩ ሁኔታ በመስራት የከተሞችን ስራ ባህል ለመቀየር ትላልቅ ስራ ተከናውነዋል። ከነዚህ ኢንሼቲቮች የከተማን ህብረተሰብ ምግብ ዋሰትና ለማረጋገጥ የከተማ ግብርና የተሰራ ሲሆን፤ ከተማ የተመረተ የሚሸጥበት ብቻ ሳይሆን የሚመረትበትም ለማድረግ የተሰራበት ዓመት ነበር። ሁለተኛው በከተሞቻችን ከተለዩ ችግሮች ውስጥ አንዱ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ያለ ችግር ነው። በዚህ ዙሪያ የሚሰጠውን አገልግሎት በማዘመንና ድጂታላይዝድ በማድረግ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጥ ንቅናቄ ሲደረግ የቆየና ወደፊትም ተጠናክሮ የሚሰራበት ይሆናል።

ሦስተኛ የክልሉን ከተሞች ምቹ የመኖሪያ ቦታ እንዲሆኑ በከተማ ፕላን መሰረት የተለያዩ የከተማ አረንጓዴ ልማት ፓርኮችን በማልማት ለአገልግሎት እንዲበቁ ተደርገዋል። ሌላኛው በዝቅተኛ ኑሮ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የመኖሪያ ቤት ችግራቸውን ለመቅረፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች በመስራት ማስተላለፍ የተቻለበት ዓመት ነበር።

በሌላ በኩል የከተሞች መሰረተ ልማት አቅርቦትና ተደራሽ ለማስፋፋት በተሰራ ስራ ጥራቱን በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ሲሰራ ነበር። በዚህ ዓመት የመንግስት በጀት፣ የልማት አጋሮች፣ ህብረተሰብ ተሳትፎና ወዘተ. ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት ከ 5890 በላይ ፕሮጀክቶች ተሰርተዋል። የከተሞችን ዕድገትን በማረጋገጥ የብልፅግና መሰረት የተጣለበት መሆኑን መረዳት የተቻለበት ነበር። የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ለማሳደግ በተሰራ ስራ ከ100 ፐርሰንት በላይ መሰብሰብ ተችሏል። በተጨማሪም በህዝብ ተሳትፎ ስራን ንቅናቄ በመፍጠር መንግስት ሊደርስ ያልቻለባቸውን ስራዎች በገንዘብ በ3.6 ቢልዮን ብር ተሰርተዋል። በዜግነት አገልግሎት ሰው ባለው ጉልበት፣ ገንዘብና መሳሪያ በማሳተፍ በ3.9 ቢልዮን ብር ከምግብ ድጋፍ እስከ "ቡሁራ ቦሩ" ትምህርት ቤት የተሰራ ሲሆን በ2015 ዓ.ም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

በክልላችን ከተሞች በ2015 ዓ.ም በአዲስ መንፈስና በላቀ ብርታት የከተማ አረንጓዴ ልማት ፓርኮች ማልማት፣ ከተማ ግብርና ስራዎችን ማስፋት፣ ቁጠባ ቤቶችን መገንባት፣ አገልግሎት አሰጣጥ ማዘመን፣ ማዘጋጃቤታዊ ገቢን ማሳደግ፣ የታቀዱትን መሰረተ ልማቶችን በጥራትና በታቀዱለት እንዲጠናቀቁ ማስቻል፣ ህዝብ ተሳተፎንና ዜግነት አገልግሎት ስራዎችን ማስፋት፣ የከተማ ፅዳት ዘመቻ ስራዎችን ወደ መደበኛ ስራ ለማሻገር በንቅናቄ በመደገፍ መሥራት ተጠናክሮ ይቀጥላል። ስለሆነም በቢሮው የተያዙትን ግቦች ለማሳከት የክልላችን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ባለሀብቶች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የከተማ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላትና ወዘተ የድርሻችሁን እንድትወጡና ከጎናችን ሆናችሁ አብረን እንድንሰራ በአክበሮት እጠይቃለሁ።

በመጨረሻም የክልሉና የሀገራችን ህዝቦችን የከተማ ባለቤት ሆኖ ምቹ ኑሮ እንዲኖር ለማድረግ የሚገጥሙንን ውጣ ውረድና ፈተና በመሻገር ብልፅግናን ጉዟችን በቀጣይነት ለማረጋገጥ እንሰራለን። ይህን ደግሞ በአንድነት ተስፋ ይዘን፣ ወንድማማችነት፣ ፍቅር እና መደጋገፍን ከኢሬቻ እየተማርን ማስቀጠል እንደሚገባ ማሳሰብ እወዳለሁ። በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፀጥታ አካላት ጋር በመሆን ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ እጠይቃለሁ።

## በድጋሚ እንኳን ለ2015 ኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

## መልካም በዓል!!!

## የኦሮሚያ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የሪፖርቱ ዓላማ በሰብአዊ መብት ሰበብ የኢትዮጵያ መንግስትን ወከባ ውስጥ መክተት ነው››

- አቶ ሱራፌል ጌታሁን
በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ

ማህሌት አብዱል

የዛሬው የዘመን እንግዳችን መምህርና ተመራማሪ ናቸው ። አቶ ሱራፌል ጌታሁን ይባላሉ ። ትውልድና እድገታቸው ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ ሲሆን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዛው ከተማ በሚገኙት ቡርኪቱና ዶዶላ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው የተከታተሉት ። በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ዲፕሎማቸውን በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሰርተዋል ። በፖለቲካ ሳይንስና አለምአቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በፒስ ኤንድ ሴኩሪቲ ትምህርት መስክ ሁለተኛ ዲግሪያቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል ።

የተለያዩ ምርምሮችንና ጥናቶችን ያካሄዱት እኚሁ ሰው በተለይም በአባይ ወንዝ ተፋሰስ ሃገራት ውሃን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችና ትብብሮችን በሚመለከት ባካሄዱት ጥናት ይታወቃሉ ። እንዲሁም የለውጡ መንግስት መምጣቱን ተከትሎ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓት ሂደትና ሽግግር ላይ ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች ዙሪያ ያከናወኑት ጥናት ተጠቃሽ ነው ። ላለፉት አስር ዓመታት በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እያገለገሉ ያሉት እኚሁ ሰው የዛሬው የዘመን እንግዳችን ናቸው ። ከፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ከአቶ ሱራፌል ጌታሁን ጋር በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ በተለይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በቅርቡ በኢትዮጵያ ላይ ባወጣው ሪፖርት ዙሪያ ውይይት አድርገናል፤ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል ።

**አዲስ ዘመን፡- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ ተፈፅሟል ያሉትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዲያጣሩ ያቋቋመው ኮሚቴ ሪፖርት አውጥቷል። በዚህ ሪፖርት ላይ ያለዎትን ምልከታ በማስረዳት ውይይታችንን ብንጀምር?**

**አቶ ሱራፌል፡-** እንደምታስታውሽው ከዚህ ቀደም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር በጋራ ያወጡት ሪፖርት ነበር ። በተለይ የዘር ጭፍጨፋ እያሉ ለሚያነሱት ነገር ምንም ተጨባጭ ማስረጃ እንደሌለና ከዚህ ቀደም ‹‹ረሃብን እንደጦር መሳሪያ ተጠቅመዋል›› እየተባለ የሚነሳ ከፍተኛ ውንጀላ ነበር ። እነዚያ ውንጀላዎች ምንም አይነት ማስረጃና መረጃ በሌለበት ነገር ላይ በአሉባታና አሸባሪው ቡድን የፈጠረው ወሬና ፕሮፖጋዳ እንደሆነ አረጋግጧል ። በሌላ በኩል ግን ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ጉዳዮች ላይ ዘርዝሮ አስቀምጦ ነበር ። አማፂው ቡድን ደግሞ ያደረሰውን ከፍተኛ የሰው ፍጅት እንዲሁም የሰብአዊ መበት ጥሰት፤ ከዚህም ባሻገር የማህበራዊ ተቋማት ውድመትን በዝርዝር አስቀምጦም ነበር ። በጣም በሚገርም ሁኔታ በጥምረት የተሰራው ይህ ሪፖርት ተቀባይነት አግኝቶም ነበር ። በብዙ ሃገራትም ጭምር ይሁንታ ተሰጥቶትም ነበር ።

ይሁንና ይህንን በጋራ የተሰራን ጥናት ባፈረሰ መንገድ ድርጅቱ ሌላ ኮሚቴ አቋቁሞ የፖለቲካ ይሁንታ ያለው በአንፃሩ ደግሞ መሬት ላይ ያለውን እውነታ የማይዳስስ ሪፖርት አውጥቷል ። እንደእኔ እምነት ይህ ሪፖርት መሰረታዊ ስህተት ያለበትና አግላይ የሆነ ሪፖርት ነው ። ይህንን ጥናት ሲያካሂዱ ያናገሩት የትኛው ክልል የሚኖሩትን ሰዎች ነው? የትኛው አካባቢ ሄደው በተጨባጭ ስለደረሰው ውድመት ምንያህል በቂ መረጃ አግኝተዋል? የሚሉት ጉዳዮች ግልፅ አይደሉም ። ይልቁኑ ከማህበራዊ ሚዲያ በተለይም የአሸባሪ ቡድኑ አፈቀላጤዎች ቲዩተር የተወሰደ ሪፖርት የሚመመስል አምድታ ነው ያለው ።



ከአሸባሪው ቡድን ፕሮፖጋንዲስቶች ያገኙትን ነገር ይዘው መጥተው እንዲህና እንደዚህ አይነት በደል ተፈፅሟል ቢልም ተቀባይነት አይኖራውም

ሲጀመር ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት የነበረውን ሪፖርት ወደጎን በመተው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሲጮህና ሲደሰኩር የነበረውን ነገር ነው ይዞ መምጣቱ በራሱ የሪፖርቱን ታዓማኒነት ሙሉ ለሙሉ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከተው ነው ። ከዚህ ቀደም እነሂዩማን ራይትዎች ኬኒያ ናይሮቢ ስደተኛ ካፕ ላይ ተቀምጠው በስልክ የሚደርሰውን የሃሰት ወሬ ሪፖርት አድርጎ ማውጣቱ በግሌ በጣም ነው የሚያሳፍረኝ ። አንደኛ በአፋርና በአማራ ክልል የደረሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና ጉዳት ለማጣራት ያለመፈለጉ ድርጅቱ የሚዛናዊነት ችግር እንዳለበት ማሳያ ነው ። እውነት ስለተደፈሩት ሴቶች ጉዳይ ስለማጣራታቸው ጥርጣሬ አለኝ፤ በተለይ ኮምቦልቻ፤ ቆቦ ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማጣርት ምን ያህል ሙከራ አድርገዋል? እነማን ናቸው በዚህ ቃለመጠይቅ ላይ የተካተቱት? የሚለው ነገር ግልፅ አይደለም ። ከዚያ ይልቅ የጁንታው አፈቀላጤ ጌታቸው ረዳ የሚነግራቸውን የሃሰት ፕሮፖጋንዳና መረጃ ይዘው እንደመጡ ግልፅ ነው ።

በአጠቃላይ ይህ ሪፖርት ሚዛናዊ አይደለም፤ ፈፅሞ ከእውነት የራቁ መረጃዎችን ያካተተ ሰነድ ነው ማለት ይቻላል ። አስቀድሜ እንዳልኩሽም በዚህ ሪፖርት ላይ ዋቢ ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችል ታዓማኒ የሆነ ምንጭም የለውም ። በመሆኑም ከአሸባሪው ቡድን ፕሮፖጋንዲስቶች ያገኙትን ነገር ይዘው መጥተው እንዲህና እንደዚህ አይነት በደል ተፈፅሟል ቢልም ተቀባይነት አይኖራውም ። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብትን ጨምሮ ይህንን ሪፖርት ራሺያ ቻይና ቬትናምና ሌሎችም ሃገራት በጥርጣሬ ሁኔታ ነው ያዩት ። በተለይ ከዚህ ቀደም በሚዲያ የሚደረግ ቅስቀሳ ነበር፤ የሕወሓት ተወካዮች በከፍተኛ ደረጃ የሰራው ስራ ቢኖር በዲጂታል ዲፕሎማሲ ገለልተኛ የሆኑትን አካላት መውቀስ ነበር ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ሪፖርት ሚዛናዊነት የጎደለው ስለመሆኑ ማሳያ የሚሆን ስአብነት ቢጠቅሱልን?**

**አቶ ሱራፌል፡-** እንደሚታወሰው ላለፉት ስምንት ወራት ለትግራይ ህዝብ ያለምንም ገደብ ሰብአዊ ድጋፍ ሲደረግ እንደነበር እየታወቀ ይህንን እንኳን በሪፖርቱ ላይ አለማካተታቸው ሪፖርቱ ከመሰረቱ ሚዛናዊነት የጎደለው ስለመሆኑ ያመላክታል ። ከሁሉ በላይ ደግሞ መጨረሻ ላይ የሚሰጠው ምክረ-ሃሳብም ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ በትግራይ ጉዳይ ሌላ ችግር ስለመጣ አንድ ውሳኔ ያሳልፋል የሚል በቀጥታ በውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለመግባት ያለመ ስለመሆኑ ግልፅ ሆኗል ። ይህም የራሱ ፖለቲካ አንድምታ ያለውና በእጅ አዙር ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባት መንደርደሪያ እንዲያበጅላቸው ያቀዱት ነው። በተለይ እነአሜሪካ ኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አካል መሆኑ ግልፅ ነው ።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰላም ድርድር ያስተጓጎለው ይኸው ፅንፈኛ ቡድን እንደሆነ ይታወቃል። ዋግህምራ 25 ሰዎችን ከስደተኛ ጣቢያ አውጥቶ ሲረሽን ዝም ነው ያሉት ። ለምን አላወገዙም?። ለዚህም ነው በእነዚህ ተቋማት ላይ በአንድም በሌላም ጥርጣሬ እንድናነሳ የሚያደርገን ። በጣም በሚያሳዝን መልኩ ጦርነቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ እንደማይፈልጉ ይህ ሪፖርት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ። ምክንያቱም በዚህች ሃገር ላይ ሰላም እንዲመጣ ከተፈለገ መጀመሪያ የአሸባሪውን ቡድን በቁጥጥር ስር ማዋል እንደሚገባ አፅንኦት በሰጡት ነበር ። እነሱ ጦርነቱ በሰላም እንዲቋጭ ቢፈልጉ ኖሮ በቅርቡ የተመድን 70ሺ ሊትር ነዳጅ ዘርፎ በአማራና በአፋር ህዝብ ላይ ጥቃት ሲያደርስ አላወገዙም። ያኔ ለምን ድፍረትና አቅም አጡ? ከዚህ ይልቅም ምርጫቸው ያደረጉት የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና በማሳደር እንደፈለጉ ለማሽከርከር ነው ። በአጠቃላይ የተካተቱት መረጃዎች ፈፅሞ ከእውነት የራቁና ሚዛናዊ ያልሆኑ ከመሆናቸውም ባሻገር ከዚህ ሪፖርት ጀርባ ካለው እውነታ ጋርም የሚፃረር ሆኖ ነው ያገኘሁት ።

**አዲስ ዘመን፡- ሌሎች ሃገራት ውስጥ በተከሰተ የእርስ በርስ ግጭት ዙሪያ መሰል ጥናት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተካሂዶ ያውቃል? በተለይ መንግስትና የተገዶ ማህበረሰቦችን ባላካተተ መልኩ የሚደረግ እንዲህ አይነት ጥናት ምንን ያሳያል?**

**አቶ ሱራፌል፡-** አዎ ይህ ድርጅት ሁልጊዜም ቢሆን የሚያከናውናቸው ጥናቶች እንደአሜሪካ ያሉ ሃያላን ሃገራትን ጥቅም ለማስጠበቅ አላማ አድርገው የሚነሱ ናቸው ። ሲፈልጉ የእነሱን ጥቅም እስካልጎዳ ድረስ የቱንም ያህል ህዝብ ቢያልቅና የሰብአዊ መብት ቢጣስ ደንታ የላቸውም ። ጥቅማቸውን የሚነካ መስሎ ከታያቸው ደግሞ በሰበብ ባስባቡ ጫና ለመፍጠር የሚያስችላቸውን መሰል ጥናቶች በማካሄድ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማስተባበር ይጠቀሙበታል ። ይህ አቋማቸው ደግሞ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ላይ በተደጋጋሚ የታየ ነው ።

ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አንዱ የሚወቀስበት ጉዳይ በምስራቃዊ ኮንጎ እ.ኤ.አ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም ከአምስት ሚሊዮን ሰው በላይ ሲሞት በዝምታ ያለፉበት ሁኔታ ነው ። ምክንያቱም ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ሆነ ተቋሙን እንዳሻቸው የሚያሽከረክሩት ሃያላን ሃገራት በዚያ አካባቢ ላይ የምዕራብውያኑ ኩባንያዎችና የዘይት ማዕድን የሚያወጡና የሚዘርፉ ግለሰቦችን ለመታደግ ሲሉ ነው ። በዚያች ሃገር ላይ ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ተካሂዶ ሳለ የእነሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

ምዕራባውያኑ ዝምታን ነው የመረጡት ። አንድም ቀን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ደፍሮ በዚያ ጉዳይ ላይ ሪፖርት ያወጣበት ነገር የለም ።

በሌላ በኩል ደግሞ እንደሚታወሰው በሱዳን ዳርፉር ላይ የተፈጠረውን የርስ በርስ ግጭት አስታኮ በመግባት ጉዳዩን ወደ ዘር ጭፍጨፋነትና ሰብአዊ መብት ጥሰት በማዞርና የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ያሳመኑበት ሁኔታ ነበር ። በጣም የሚያስገርመው ነገር በዳርፉር ጉዳይ ላይ የቀድሞው የሱዳን ፕሬዚዳንት አልበሽር ለመክሰስ አንድ የአሜሪካ ፀሐፊ በየሳምንቱ ከ200 እስከ 400ሺ ሰው እየተጨፈጨፈ እንደሆነ እየፃፈ ዓለምአቀፉ ማህበረሰብን ለማነሳሳት ጥረት ሲያደርጉ ነበር ። አልበሽርን ለመክሰስ ሲሉ ብቻ ግጭቱን የዘር ማጥፋት እንደሆነ በድፍረት ይፅፉ ነበር ። እነሱ አጋነው ባወጡት ሪፖርት ምክንያት ነው ዓለምአቀፉ ማህረሰብ አልበሽር ላይ እንዲነሳባቸው ያደረጉት ።

በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ላይ ያወጡት የዚያ ሪፖርት ዋነኛ አላማው አስቀድሜ እንዳልኩሽ የፖለቲካ ፍላጎት ነበር ። ልክ አሁን እኛ ላይ እንደሚያደርጉት የሱዳን መንግስትን የማወከብና የመክሰስ ሁኔታ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ ህዝብ በሚያልቅባቸው ሃገራት ዝምታን የመረጡበት ሁኔታ ነው ያለው ። ለምሳሌ የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ በርማ ላይ የፓርቲው ወታደር ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈፅሟል፤ እስካሁንም ድረስ የምዕራብውያን ኩባንያዎች ናቸው በርማ ላይ ነዳጅ የሚቆፍሩት ። አሜሪካን ጨምሮ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተካሄደውን ጭፍጨፋ «አፋቸውን ሞልተው የዘር ማጥፋት» ብለው ለመጥራት አልደፈሩም ። እንዳውም ሰለጭፍጨፋው የሚናገሩትን አካላት ዝም ለማሰኘት ነበር ጥረት የሚደርጉት ።

አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነው ነገር ልክ እንደ ዳርፉር ነው ። አለምአቀፉ ማህበረሰብ በአንድም በሌላ የኢትዮጵያ ጦርነት ከራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም መከበር ጋር ነው በቀጥታ የሚያያይዙት ። በፖለቲካ ፍላጎት የተቃኘው ይህ ሪፖርት የሚያሳየው ይህንን ነው ። አሜሪካኖች ኢራቅና ሶሪያ ላይ በሮኬት ከተማ ሲያወድሙና ህዝብ ሲጨፈጨፍ እንዲህ አይነት ሪፖርት ለምንድነው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያላወጣው?። እስራኤልስ በጋዛ ላይ ያንን ሁሉ በደል ስትፈፅም ለምን እንዲህ አይነት ሪፖርት አይወጣም? ብሎ መጠየቅ ይገባል ። ይሄ ድርጅት በአጠቃላይ የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ሚዛናዊነት የጎደለውና እውነታን ያላገናዘበ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ኃላፊነት የጎደለውና የአንድ ወገን ፍላጎትን ብቻ ያማካለ ሪፖርት ለምን ጉዳይ ማስፈፀሚያ እንደሆነ ግልፅ ነው ።

በተደጋጋሚ እንደታየው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰብአዊ ድጋፍ ስራው በትህነግ ቡድን ሲስተጓጎልበት ከመክሰስ ይልቅ ዝምታን ነው ምርጫው ያደረገው ። ይህ ተቋም በተጨባጭ እውተኛ ቢሆን ኖሮ የእርዳታ ስራው በአሸባሪ ቡድኑ ሲስተጓጎል ዝም ባላለ ነበር ። ማን ነው የህፃናትን አልሚ ምግብ ዘርፎ በምሽግ ውስጥ እያደረገ ያለው? የመንግስታቱ ድርጅት ሃቀኛ ቢሆን ኖሮ ይህንን ተግባር በይፋ መኮነን ነበረበት ። ለሰብአዊ እርዳታ የገባ ነዳጅ ሲዘረፍ ዝምታን መርጠው ይህንን የሽብር ስራ የደገፉበት ሁኔታ ተገቢ አልነበረም ።

እውነት ለመናገር አሁንም አለም አቀፉ ማህበረሰብ ወይም በተመድ ስር ያሉ ተቋማት ሊያደርጉ የሚገባው ትህነግ ተጨማሪ ችግር የትግራይ ህዝብ ላይ የሚያደርስ በመሆኑ ከዚህ ተግባሩ እንዲታቀብ ማድረግ ነበር ። የፌደራል መንግስቱ ላይ የሚያደርገውን ጩኸቱንም በአማፂ ቡድኑ ላይ ማድረግ ነበረበት ። በተመሳሳይ እንደሚታወሰው ይህ ጦርነት እንደተጀመረ እነዚህ ድርጅቶች በዝምታ ያለፉበት ሁኔታ ነበር ። ምክንያቱም በዚያ ጦርነት የራሳቸው ፍላጎትና ዓላማ ስለነበራቸው ነው። ጦርነቱ በተራዘመ ቁጥር ግን ለትግራይ ህዝብ ስቃይና መከራ ነው የሚተርፈው ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሰላም እንዲሆን እንደማይፈልጉ ይታወቃል ። ጦርነቱን በማራዘም መንግስትን ማዳከምና የራስን ፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀም ነው አላማቸው ።

አሁን የያዙት ነገር «የትግራይ ህዝብ በፌደራል መንግስቱ አደጋ ውስጥ ገብቷል» ብሎ ከበሮ በመደለቅ እነሱ በሚፈልጉት መንገድ በሃገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ነው ፍላጎታቸው ። በሌላ በኩል ደግሞ የሪፖርቱ ዓላማ በሰብአዊ መብት ሰበብ የኢትዮጵያ መንግስትን ወከባ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ነው ። በተለይ እነሱ መጀመሪያ ለመክሰስ የሄዱበት መንገድ አለ፤ ከዚያ ውጪ ሲኮን የፈለገ ጥሩ ነገር ቢሰራ እነሱ የማይቀበሉበት ነው የሚሆነው ። የተመድ የምግብም ሆነ የጤና ድርጅቶች እውነተኛ ተቋማት ቢሆኑ ኖሮ ትግራይ አማፂ ቡድን ላይ ጫና መፍጠርና ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይጠበቅባቸው ነበር ።

በተጨማሪም እነዚህ የተመድ ተቋማት አሸባሪ ቡድኑ የሰረቀውን ንብረት እንዲመልስ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የእርዳታ ቁሳቁሶች በትክክል ለህዝቡ አለመድረሳቸውን ማሳወቅ ነበረባቸው ። ሌላው ይቅርና የሱዳን የስደተኞች ካምፕ ላይ የትህነግ አሸባሪ ቡድን አሸባሪዎች እየተመለመሉ እየሰለጠኑ ስለመሆናቸው የኢትዮጵይ መንግስት ደጋግሞ ሲናገር ሰሚ አላገኘም ነበር፤ ሆኖም ከአንድ ዓመት በኋላና ካምፑ ባዶ ከሆነ በኋላ የተባበበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን መረጃ አለኝ አለ፤ መረጃ ካለው ለምን ቀድሞ አላስቆመም? በጣም የሚሳዝን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ሪፖርት በኢትዮጵያ ላይ ምን ያስከትላል ብለው ይሰጋሉ?**

**አቶ ሱራፌል፡-** ሪፖርቱ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡን በከፍተኛ ደረጃ ሊያታልሉ ይችላሉ የሚል ስጋት አለኝ ። በተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ስር የሚወጣው ሪፖርት የተቋሙን ዓላማ የሚወክል ነው ተብሎ የሚነሳው ። ግን ሪፖርቱ አስቀድሜ እንዳነሳሁት ከዚህ በፊት የወጣውን ሪፖርት የጣሰ፣ ተዓማኒነት የጎደለውና ስህተት ያለበት ነው ። ከዚህ ባሻገር እነሱ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ መንግስት ለመጣል የሚፈልጉት ማዕቀብ እንዳለ ግልፅ ነው ። በተለይም እነአሜሪካ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካኝነት አንድ ማዕቀብ መጣል፣ ሲቪል ሶሳይቲዎች መንግስት ላይ ጫና እንዲፈጥሩ እና የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ሃይል በአካባቢው እንዲሰማራ ማድረግ ዋነኛ ነው ፍላጎታቸው። ምክንያቱም የእጅ አዙር ቅኝ ግዛትን አሻፈረኝ ያሉ ሌሎች አገራት ላይም የተደረገው ይህ ነው። ሱዳን ላይ ያደረጉት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው ።



እርግጥ በኢትዮጵያ ካለው ነባራዊ ሁኔታ እዛ ካለው ሁኔታ ይለያል ። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ አይነት ሪፖርቶች የፖለቲካ አንድምታው በከፍተኛ ሁኔታ የጎላ ስለሆነ መንግስትን በማዋከብ ጫና ውስጥ እንዲገባ ከማድረግና እነሱ በሚፈልጉት መልኩ ድርድሩን ማካሄድ ነው ። በአማራና በአፋር ክልል እየደረሰ ያለውን የሲቪል ተቋማት ውድመት፣ ሞትና ስደት ሪፖርቱ የሸፈነው ነገር የለም ። ሁሉም ወቀሳ የቀረበው በፌዴራል መንግስቱ ላይ ነው ። እናም የኤርትራን መንግስት በተወሰነ መልኩ የኮነነበት ሁኔታ አለ ። በአንፃሩ ደግሞ ስለሽብር ቡድኑ ተግባር የተባለ ነገር የለም ።

ይሁንና አሁንም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ነው ያለው ። አሁንም ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ ካልተሰራና ስለትግራይ ዓለም አቀፍ ማሕበረሰብን ማስረዳት ካልተቻለ መንግስትን ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ይከትተዋል ። ይህ ከመሆኑ አስቀድሞ በዴሞክራሲው በኩል መሰራት ያለባቸው ትላልቅ የቤት ስራዎች አሉበት። የሀሰት ፕሮፖጋንዳዎችን መመከት መቻል ይገባዋል ። ይህንን ደግሞ ማድረግ የሚቻለው በእውነተኛ ማስረጃ አቅርቦ በመሞገት ነው ።

የአሜሪካ ልዩ መልእክተኛ መቀሌ ደርሰው ሲመለሱ ያወጡት ሪፖርት አስደንጋጭ ነበር ። የሰብአዊ ድጋፍ አስመልክቶ ምን ያህል በእነዚህ ሰዎች እንደተሸወዱ ያሳያል ። አሁን አገሪቱ ካለችበት ሁኔታ አኳያ ሌላ ማዕቀብ የመሸከም አቅም የላትም ። በመሆኑም ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መሰራት አለበት ብዬ አስባለሁ ። የኢትዮጵያ ወዳጆች በሀገሪቱ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና በመቃወም እንዲተባበሩ ማድረግ ያስፈልጋል ። በዚህም የውጭ ሃይሎች ዝምታ እንዲሰበር ማድረግ ይገባል ። በዋናነት በተለያዩ አገራት የሚገኙ አምባሳደሮች በተለያዩ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ስለኢትዮጵያ ሁኔታ በማስረዳት ኢትዮጵያ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና መቀነስ አለባቸው ።

በመሰረቱ መንግስትም ሪፖርቱን እንደማይቀበለው ወዲያውኑ ነው ያስታወቀው ። ሌሎችም ሃገራት ተቃውመውታል ። የኢትዮጵያ መንግስት ከዚህ ቀደም ወንጀል ፈፅመዋል ያላቸውን ወታደሮች አስሯል። በራሱ መንገድ አጣርቶ የወሰዳቸው እርምጃዎች አሉ ። እነዚህ እርምጃዎች በመንግስት መወሰዳቸውን በሪፖርቱ አልተካተተም ። እነዚህን ነገሮች በማንሳትና በዲፕሎማሲ መንገድ በመጠቀም መንግስት የራሱን ስራ ይሰራል ብዬ አምናለሁ ። በተለይ ሪፖርቱን የተቃወሙ ሃገራትን በማስተባበር ዓለምአቀፍ ማህበረሰቡን የማሳመን ስራ መሰራት አለበት ብዬ አምናለሁ ። ይህንን ሪፖርት ኢትዮጵያ እንደማትቀበለውና የፖለቲካ አላማ እንዳለው፤ በአንፃሩ የሽብር ቡድኑን የመደገፍ አዝማሚያ እንዳለው ለማሳየት በከፍተኛ ደረጃ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ አሁንም ቢሆን የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ አሸባሪው ሕወሓት ጉዳይ ላይ ዝምታን መምረጡ የትግራይን ህዝብ መከራና ስቃይ ነው ያረዘመበት ። ይህ የሚያሳየው ቡድኑ አንድም የእነዚህ ተቋማት መሸሸጊያ መሆኑን ነው ። ይህንን በማጋለጥ በኩል መንግስት ከፍተኛ ስራ መስራት አለበት ብዬ አምናለሁ። በተለይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ ረገድ ሰፊና ተከታታይ ስራ መስራት ይጠበቅበታል ። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ውስጥ ያሉ ተቋማት ራሳቸው በየጊዜው የሚያወጡት ሪፖርት እርስበርሱ የተጣረሱ መሆኑን መተቸትና ለኃያላን አገራቱ መጠቀሚያ እንደሆነ ማጋለጥ ያስፈልጋል ። ደግሞም እንደኛ በዚህ መልኩ የተጎዱ ሃገራት በመኖራቸው እነሱንም ማስተባበርና ከጎናችን እንዲሰለፉ ማድረግ ይገባል ።

በአጠቃላይ በሃገር ውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባቱንም ነገር በዚያው አለም አቀፍ ህግ መሰረት በማድረግ መቃወምና ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይኖርብናል ። በተለይ በኤምባሲዎቻችን በኩል የአለም ህዝብ እውነታውን እንዲረዳና ተመድም ሆነ የሚመሩት ሃገራት ሴራን ማጋለጥ ይገባል ። በአሸባሪው ብድን ላይ ድርጅቱ ዝምታን መምረጡ የሃገራቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ምን ያህል እየጎዳ መሆኑን ማሳየት ይጠበቅበታል ።

እንዲሁም መንግስት በራሱ መንገድ ሰብአዊ መብት እንዲከበር የጀመራቸው ሥራዎች መቀጠል አለባቸው ብዬ አምናለሁ ። በቋንቋና በዲፕሎማሲ ክህሎት የዳበረ እውቀት ያላቸው ዲፕሎማትና ባለሙያዎችን መመደብና በዋናት ይህንን ጉዳይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ማድረግ ይገባል ። በተጨማሪም በዲጂታል ዲፕሎማሲው በኩል ብዙ ስራ መስራት መቻል አለበት ብዬ አስባለሁ ። እንዲሁም በአለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ የተሻለ እውቀትና ተናግሮ የማሳመን ብቃት ያላቸው ሰዎች እየቀረቡ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ማስረዳት ይገባቸዋል ። ይሄ እንደሃገር የመጣብን ችግርና በእጅ አዙር የሚደረግ ቅኝ ግዛት በመሆኑ አሻፈረን ልንል ይገባል ።

እኔ አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ መሰራት አለበት ብዬ አምናለሁ ። በተለይ የተመድ ተቋማትን ግልፅ አድሏዊ ሪፖርት የተቋማት ከተቋቋመበት ዓላማ ውጪ አካሄድን በመንግስት በኩል ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ስራ ሰርቶ ቡድኑ እያደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ና ፖለቲካዊ ችግር፤ እንዲሁም የእነዚህን ተቋማት ዝምታ በደንብ አድርጎ ለአለም አቀፍ ተቋማት ማሳወቅ አለበት ። በተለይ እነዚህ ተቋማት ላይ ጫና ማሳደር አለበት ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አለም አቀፉን ማህበረሰብ ጠርቶ ማወያየትና ሪፖርቱን እንዲነቅፉ ማድረግ ይገባል ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሱራፌል፡- እኔም አመሰግናለሁ ።**

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “እንቆቅልሾቻችሁን ስለምን መፍታት አቃታችሁ?”

በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

**“መተከዣ”፤**

“ልብ ከሀገር ይሰፋል” ይላሉ፤ ደግ ነው። ችግሩ ሀገር ከልብ የሰፋ እንደሆነ ነው። ከሀገር የሰፋ ልብ ፍልስፍናው ሁሉ “ከራስ በላይ ነፋስ” የሚሉት ብጤ ነው። እነከሌ ብለን ባንዳፈራቸውም፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሀገራት ዋነኛው መርሃቸው፣ ሕልማቸውም ሆነ ቅዠታቸው “ገናና ነን! ሀብታም ነን! ሁሉ በእጃችን ሁሉ በእጃችን!” በሚሉ የትምክህት መገለጫዎች የተቃኘ ነው።

በራሳቸው የዕለት ተዕለት ጉዳይ መመጻደቃቸው ብቻም ሳይሆን በዓለም ካርታ ላይ ሳይቀር ሀገራችን “በጽጌሬዳ ቀለማት ካልደመቀልን” በማለት “በጠብ ያለሽ በዳቦ ፉከራ!” ግብግብ እስከ መፍጠርም ሊደርሱ ይችላሉ። በስንዴ ልገሳ ሰበብ እጅ እጃቸውን የሚያዩአቸውን ሀገራት ሉዓላዊነት እንደምን ሲዳፈሩ እንደኖሩ በማስረጃ ማሳየት ይቻላል። “እኛ ብቻ እንድመቅ! እኛ ብቻ እንግነን! እኛ ብቻ ዓለምን አንቀጥቅጠን እንግዛ! ሌሎች ይንበርከኩልን!” ጉጉታቸውና የሴራ ቅንብራቸውም ይህንኑ ተልዕኳቸውን ለማሳካት እንደሆነ ከእኛም ሆነ ከእነ እከሌ ሌሎች ሀገራት ታሪክና ዐውድ እያጣቀስን ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ እንችላለን።

በአንጻሩ የልባቸውን አድማስ ከሀገር ይልቅ በጣሙን ለጥጠው የሚያሰፉ ሀገራት እምነታቸው፣ የዲፕሎማሲ ጥበባቸውም ሆነ የፖለቲካዊና መንግሥታዊ አቋማቸው “አንካ በእንካ - win win” መርህ ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን ስትራቴጂያቸውን የሚያጠብቁት በመከባበርና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ በመመሥረት ነው። ሀገሬ ይህንን ዓይነቱን “የልብ ስፋት” መርህ አጥብቃ ስለምትከተል ባደንቃትና ባደምቃት ይገባት ይመስለኛል።

ችግሩ የእኛ የምንላት ሀገር የታሪኳን ርዝመትና ገናናነት ያህል ቁልቁል ስታንስ እንጂ ሽቅብ ለመንጠራራት ያለመቻሏን ሳስብ በውስጤ ቅይም እልባታለሁ። ከፈጣሪ ዘንድ የተሰጣትን የምድር በረከት ታቅፋና በማህጸኗ ሰውራ እንደ ንፉግ እናት ልጆቿ በርሃብና በችግር ሲጠቁ እያየች ቀድማ ባለመባነንም “ከጉስቁልና፣ ከርሃብና ከድህነት ጋር” አቆራኝታን ለዘመናት ማኖሯ ሲታወሰኝም “ከማኅጸኗ እንደ ወጣ ልጅ” ፊቴን አጥቁሬ ብገስጻት፣ ወይንም መከፋቴ ሲበዛ ብወቅሳት ለምን ብላ ልትሞግተኝም ሆነ ልታስሞግተኝ አይገባም።

እርግጥ ነው የሀገሬ ታሪኳም ሆነ ውሎ አምሽቶዋ “ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ!” እንዲሉ ያለፈችባቸው የመከራዎቿ ዘመናትና ዓመታት ሲጻፉ የኖሩት ጥቋቁር ፈተናዎቿ እየተገጣጠሙ እንደሆነ አይጠፋንም። “ለእኔ እናት ምን በጃት፤ ያም ድንጋይ ያም አፈር ያም ኮተት ጫነባት” እንዲሉ፤ በእሾህ በሚመስሉ የቅርብ ጎረቤቶቿና የሩቅ ጠላቶቿ እየተጎነታተለች ዘመኗን በሙሉ አሳሯን ስትበላ መኖሯ አይሰወርብንም።

ከቤት ውላጅ የራሷ ልጆች መካከልም ቢሆን እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ “ባጋቱት ጡቶቿ እንዳንባረክ” የጠቡትን ጡት እየነከሱና መከራዋን እያበዙ እንደሚያስለቅሷት እያስተዋልን ነው። ስለዚህም ነው “ከእሾህ እንደተጠጋ ቁልቋል ዘላለሟን ስታለቅስ” የምትኖረው። ብዙ ሀገራት ከኋላዋ ተነስተው በኢኮኖሚ አቅማቸው እያስከነዷት፣ በእውቀትና በሥልጣኔ ጥበባቸው እያቁለጨለጯት ሲገሰግሱ እርሷ ግን “ከውስጥና ከውጭ መከራዎቿ ጋር እየተፋለመች” በኤሊ ዝግመት ለምን ስትንፏቀቅ እንደኖረችና እንደምትኖር ምክንያቶቹን ደጋግመን እየሰለቅን ስንቆዝም ስለከረምን እንደ አዲስ ለማሰብም ሆነ ለማብሰልሰል መሞከሩ ልብን ያታክታል፤ ጉልበትን ያርዳል፣ ሀሞትንም ያፈሳል።

እንደ ቅንጦት ባያስቆጥርብን፤ ቢያንስ “ያለ ጭንቅና መሸማቀቅ” የዕለት ዳቧችንን ገመና ሸፍነን ብናድር ትልቅ ፀጋ ነበር። የጦርነትና የጦር ወሬ ከመስማት ጆሯችን ጦም መዋል በጀመረ ጊዜም ለፈጣሪ የሚዥጎደጎድለት “ሥዕለት” በቁጥርም ይሁን በመጠን “ይህ ልኩ” ተብሎ ለመዘርዘር የሚያዳግት ይመስለናል።

ሥርዓተ መንግሥታት እየተቀባበሉት ዛሬን የደረሰው ሀገራዊ ዘርፈ ብዙ መከራችን መቼና እንዴት እንደሚቋጭ የሚነግረን ወይንም የሚተነብይልን ጠቢብ ብናገኝና ቁርጡን ብናውቅ፤ እኛ ልጆቿ “ሀገራችን ወዴት እየሄደች ነው?” ብለን ግራ ለተጋባንበት ጥያቄ፤ እርሷም ለራሷ “ወዴት እየሄድኩ ነው?” ብላ ለተቸገረችበት እንቆቅልሽ “እፎይታ” ማግኘት በቻልን ነበር። “ብልጭ ድርግም” የሚለው የዛሬው ሀገራዊ ተስፋችንም በታቀደለት መስመር እየተፋጠነ እንዳይጓዝ እንኳን እየገጠመን ያለው ዘርፈ ብዙ ችግር ከማንም የተሰወረ አይደለም።

“ብልህ ከሌሎች ይማራል”፤

ጸሐፊው ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ በሀገሩ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ምሥራቃዊ ሀገራት ኤምባሲዎች ውስጥ ከጥቂት ወዳጆቹ ጋር ለመገናኘት ዕድል ገጥሞት ነበር። የመገናኘቱ ዋና ዓላማም ከመጻሕፍት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነበር። አንደኛው በቅርብ ምሥራቋ ሀገር በእስራኤል ኤምባሲ ሲሆን ሰበበ ምክንያቱ ደግሞ በትውልደ ኢትዮጵያዊው ደራሲ በአምሳሉ መሐሪ የተደረሰው “ቤተ-እስራኤል ከትናንት እስከ ዛሬ” የሚለው መጽሐፍ ነበር።

በሁለተኛነት የተገኘነው በሩቅ ምሥራቋ ሀገር በጃፓን ኤምባሲ ሲሆን ለመገናኘታችን ምክንያት የሆነው የዲፕሎማቱ ወዳጄ የደራሲ አሰፋ ማመጫ አርጋው “የጃፓን መንገድ፤ ቋሚ ጥቅም እንጂ ቋሚ ጠላት የለም” የሚለው መጽሐፍ ነው። በእነዚህ ሁለት የኤምባሲ ጽ/ቤቶች በጥቂት ቁጥር የታደምነው እንግዶች አቀባበል የተደረገልን የፕሮቶኮል ይዘቱ በጠነነ አኳኋን ሳይሆን ቤተሰባዊ ወዳጅነቱ ጠንከር ባለበት ዐውድ ነበር። የሁለቱም ኤምባሲ አምባሳደሮች ቁጭ ብድግ እያሉ ስለ ሀገራቸውና ሀገራችን እንድንጨዋወት ድባቡን ያመቻቹልን “ጉርሻው ብቻ ሲቀር” ደማቅ የእራት ገበታ ዘርግተውልን ነበር።

በኢትዮጵያ፣ በብሩንዲ፣ በቻድና በአፍሪካ ኅብረት የእስራኤል አምባሳደር የሆኑት ትውልደ ኢትዮጵዊው ክቡር አለልኝ አድማሱ በሚጣፍጠውና በሚራቀቁበት ቋንቋችን ለዛ ባለው ጨዋታ እያዋዙ ያካፈሉን ቁምነገሮች በእጅጉ ተሰምተው የሚጠገቡ አልነበሩም። የኢትዮጵያን ጥንተ ታሪክና አሁናዊ እውነታ ከእስራኤል ታሪክ ጋር እያዛመዱ እንደ “ቤት ልጅ” በቁጭት ይሰጡት የነበረው አስተያየት ስለራሳችን ብዙ እንድንጠይቅ ምክንያት ሆኖናል።

ደራሲ አምሳሉ መሐሪም የተሸመኑበት የኢትዮጵያና የእስራኤል ውብ ባህልና ሕይወት በመጽሐፋቸው ብቻም ሳይሆን ከአንደበታቸው ጭምር እየፈሰሰ ሊያስረዱን የሞከሩበት አቀራረብ ከልብ እንድናመሰግናቸው ግድ ብሎናል። ህልማቸውና ምኞታቸው ሁሉ እትብታቸው የተቀበረበት ቀደምት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ልክ እንደ እስራኤል በልጽጋና ተውባ ማየት እንደሆነ ይናገሩ የነበረው “የድህነታችን እንቆቅልሽ እየመረራቸው፣ የችግሮቻችን ግዝፈት እያስተከዛቸው” ነበር። መጽሐፉን በቋንቋችን ጽፈው ለቀረቡልን ደራሲ አምሳሉ መሃሪ ለሀገራቸው ስላላቸው የላቀ ፍቅር አመስግነን ወደ ጃፓን ኤምባሲ ጎራ እንበል።

ዲፕሎማቱና ደራሲው ወዳጄ አቶ አሰፋ ማመጫ “የጃፓን መንገድ” የሚለውን መጽሐፋቸውን ለመጻፍ መነሻ የሆናቸው የሀገሪቱ በአጭር ጊዜ ሰልጥኖ በኢኮኖሚዋ በዓለም ላይ ሦስተኛ ደረጃ ላይ የቆመበችበት ምሥጢር ለሀገራችን እንቆቅልሽ እንደ ማነቃቂያና ማንቂያ እንዲሆን በማሰብ እንደሆነ አስረድተውናል። በኤምባሲው የተደረገልን ግብዣ ዋነኛ ዓላማም በቋንቋችን የተዘጋጀውን ይህንን መጽሐፍ ያበረከቱልንን ደራሲ፤ ክብርት አምባሳደሯ በወዳጆቻቸው ፊት በጃፓን መንግሥትና ሕዝብ ስም ለማመስገን ታስቦ እንደሆነ በኢትዮጵያ የጃፓን ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ክብርት ኢቶ ታካኮ ገልጸውልናል። በርግጥም ለደራሲው ምሥጋና ሲያንስባቸው ነው። ክብርት አምባሳደርንም ሆነ ደራሲውን የምናመሰግነው ከልብ ነው።

እስራኤልና ጃፓን በቆዳ ስፋታቸው ከኢትዮጵያ ጋር ሲነጻጸሩ በእጅጉ አነስተኛ የሚባሉ ናቸው። ለምሳሌ፡- የጃፓን የቆዳ ስፋት 377,915 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን የኢትዮጵያ ደግሞ 1,104,300 ስኩዌር ኪሎ ይሆናል። ይህ ማለት ሀገራችን ጃፓንን 192% ትብልጣለች ማለት ነው። በሕዝብ ቁጥር ሲነጻጸሩ ግን ጃፓን 125.93 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ ሲኖራት ኢትዮጵያ በ10 ሚሊዮን ገደማ የሕዝብ ብዛት ከጃፓን ታንሳለች።

ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ነፍስ ወከፍ ምርትን (Per capita GDP) በተመለከተም እ.ኤ.አ የ2022 ትንበያ የሚያመለክተው የእኛዋ ኢትዮጵያ 650.00 ዶላር ሲገመት ጃፓን ደግሞ 36,200.00 ዶላር እንደሚደርስ ይጠበቃል። ዓመታዊ የዜጎችን ገቢ ከማነጻጸር ይልቅ ሹልክ ብሎ በማድበስበስ ማለፉ ይመረጣል። የሕዝብ ቁጥሩን ንጽጽር ለጊዜው አዘግይተን ከእስራኤል ጋር ያለው የኢኮኖሚ እድገት ከጃፓን ጋር ሲተያይ ሁለቱ ሀገራት እጅግ ተቀራራቢዎች ናቸው።

ጃፓን በዓለማችን ላይ ሦስተኛዋ ባለ ግዙፍ የኢኮኖሚ ጌታ ለመሆን የደረሰች ሲሆን በአንጻሩ እስራኤልም የዋዛ እንዳልሆነች በጥናት ላይ የተመሠረቱት መረጃዎች ያረጋግጣሉ። አሁንም የእኛን የኢኮኖሚ ደረጃ በሆድ ይፍጀው እናልፈዋለን።

እጅግ የሚገርመው ጉዳይ ጃፓንም ሆነች እስራኤል ሁለቱም ሀገራት ኢኮኖሚያቸው አገግሞ ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ የቻሉት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አድቅቆና አላሽቆ ከትቢያ ላይ የመነሳት ያህል ማገገም በመቻላቸው ነው። እ.ኤ.አ ሐምሌ 1937 በአሜሪካኖቹ አቶሚክ ቦንብ የጋዩትና ወደ አመድነት የተለወጡት የጃፓኖቹ ሁለት ከተሞች የሂሮሺማና የናጋሳኪ ሰቅጣጭ ታሪክ ዛሬም ሲወራ ለእምባ ይዳርጋል። እስራኤልም ብትሆን ከናዚዎች አሰቃቂ ጭፍጨፋ ተርፋና መንከራተቷ አብቅቶ ነፃነቷን ተጎናጽፋ እንደ መንግሥት የቆመችው እ.ኤ.አ በ1948 መሆኑን ስናሰላ ዛሬ የደረሰችበት ለመድረስ ምን ያህል መራራ ዋጋ እንደከፈለች ለመረዳት አያዳግትም።

በርግጠኝነት ለመናገር የሚቻለው፤ ከማናቸውም ሀገራት ይልቅ እነዚህ ሁለት ሀገራት ለኢትዮጵያውያን ያላቸው ቅርበት የቤተሰብ ያህል የተጠጋጋ ነው። ለምሳሌ፡- የኢትዮጵያን ከተሞች ያጥለቀለቁት የጃፓን ቶዮታ መኪኖች ናቸው። ይህ የመኪና ብራንድ በእኛ ዜጎች በአንደኝነት መመረጥ ብቻም ሳይሆን “በአምልኮት” ደረጃ የሚወደድ ነው። ከቶዮታ ውጪ ሌላ መኪና በዓለም ላይ የተሰራ እስከማይመስል ድረስ ሁሉም ሰው ምርጫው ከእነዚሁ መኪኖች አይዘልም።

እነ ኒሳን፣ ሆንዳ፣ ሱዙኪ፣ ማዝዳ፣ ሚትሱቢሺንና አይሱዙን የመሳሰሉትን በዝርዝሩ ውስጥ እናካት ካልንም የሌሎች ሀገራት ብራንዶች ድርሻ ኢምንት የሚባል እንደሚሆን አያጠራጥርም። ስለዚህም በኢኮኖሚያችን ውስጥ ጃፓን ያላት ቦታ ቀላል እንዳልሆነ ለማመን አይከብድም። በአንጻሩ እስራኤልም ለአብዛኞቹ ኢትዮጵያን ከሃይማኖታዊ፣ ከዕለት ጸሎት፣ ከታሪክና እስከ ደም ውርርስ በሚደርስ መተሳሰር የተጋመድን ስለሆነ ቅርርባችን የቤተሰብ ያህል ነው።

እነዚህን ሁለት ሀገራት የሚያመሳስላቸው የጋራ ታሪክ መከራን ተቋቁሞ የማሸነፍ ብርታታቸውና የሕዝባቸው ጠንካራና አይበገሬ የሥራ ባህል ነው። ጃፓን በውቂያኖስ መካከል የተመሠረተች ሀገር ከመሆኗ አንጻር በየዓመቱ በአደገኛ ዐውሎ ነፋስና በተያያዥ የተፈጥሮ ክስተቶች ሳትጠቃ ኖራ አታውቅም። የፉኩሺማ የኒኩሌር ኃይል ማብላያ ጣቢያዋን ሳይቀር አደጋ ላይ እስከ ማድረስ የደረሰው የሰሞኑ የሱናሚ አደጋ ጉዳቷ እንኳን አንዱ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

በአንጻሩ እስራኤል ነጋ ጠባ ስትታገል የምትኖረው ከከበቧት ደመኞቿ ጋር እየተፋለመችና የበረሃ መስፋፋትን ለመግታትና ላለመሸነፍ እየተጋች ነው። የዓለም ሕዝብ የሚሻማበት የጃፋ ብርቱካን የሚበቅለው ከዚያ ከተገራው የምድረ በዳ አሸዋ ውስጥ የመሆኑ ምሥጢር እንኳን ለሩቅ ተመልካቾች ቀርቶ ለእነርሱም ቢሆን ሳይገርማቸው አይቀርም። የሁለቱ ሀገራት የኢኮኖሚ ግዝፈትና የሕዝቦቻቸው የአእምሮ እውቀት የበለፀገው በዚህን መሰል ተግዳሮች ውስጥ እያለፉ ነው።

“አዬ ጉድ!” እያልን ከእነዚህ ሀገራት ጋር የምንነጻጸረው በመራራ ትዝብት ራሳችንን በራሳችን እየቀጣን ነው። ትዝብቱ በእኛ ብቻ ተውስኖ የሚያበቃ ሳይሆን ተፈጥሮ ራሷና ፈጣሪም ጭምር መስክሩብን ብንል ምን ምላሽ እንደሚሰጡን አይጠፋንም። የተባረከ ምድር ይዘን፣ “የሺህ ዘመናት” ኩራት ተከናንበን፣ “ገናና ነበርን” እያልን ለመተረክ እየጀገንን፤ ስለምን ዳቦ አሮብን “በርሃብና በድርቅ ልምጭ” ስንገረፍ እንደምንኖር ራሳችንን ልንሞግት ይገባል።

“የማይሰለጥን ፖለቲካ ታቅፈን እሹሩሩ” እያልን የምናላዝነውም እስከ መቼ እንደሆነ ግራ ያጋባል። “ፉከራችን ጣሪያ ነክቶ” ተግባራችን ትቢያ ላይ ሲንፈራፈር የሚኖረውም ለምን ያህል ጊዜና ዘመናት እንደሆነ ምሥጢሩ ተሰውሮብናል። ማረሻ ከሚጨብጡ እጆች ይልቅ ስለምን ቃታ ለመሳብ እንደምንሽቀዳደምም እንቆቅልሽ ሆኖብናል።

“ልማድ ውሎ ሲያድር ባህል ይሆናል” እንዲሉ ሥራ ጠልነታችን፣ በላባችን ወዝ ሳይሆን በዘረፋ ለመክበር መቃዠታችን፣ ከመቻቻል ይልቅ መቧቀስ መውደዳችን እነሆ ዛሬ የደረስንበት ደረጃ ላይ አድርሶናል። በዚሁ እንቀጥል ካልንም ነገ ወደየትኛው እንጦሮጦስ ተወርውረን እንደሚለይልን ማናችንም እርግጠኞች አይደለንም።

ሁለቱ የተከበሩ የምሥራቅ አምባሳደሮች በገበታ ጭውውት ወቅት በዋነኛነት የመከሩን ልክ እንደተመካከሩ ሁሉ “እንቆቅልሾቻችሁን ስለምን መፍታት አቃታችሁ?” የሚል ነበር። “ጥያቄ አቅርቤያለሁ መልሱን ብትሰጡኝ” አለ አንጎራጓሪው ድምጻዊ። በወዳጆቻችን መጻሕፍትና ግብዣ ምክንያት ይህን ያህል ከቆዘመን ዘንዳ ነገን መጠበቅ የሚገባን በመሰል ትካዜ ውስጥ ተዘፍቀን ሳይሆን በተነቃቃ ተስፋ ከራሳችን ጋር መሃላ ገብተን መሆን ይገባዋል። ሰላም ይሁን።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ትንሿን ፅናትን የደፈራት ግለሰብ ምን ተቀጣ?

አስመረት ብስራት



አንዳንዴ መጥፎና ዘግናኝ ድርጊት ፈጻሚዎችን አግኝቼ አንድ ጥያቄ ልጠይቃቸው እፈልጋለሁ።ጥያቄዬም አሰቃቂ ወንጀል ለመፈጸም አንጀታችሁ እንዴት ቻለ? የሚል ነው። በተለይም ህፃናት ላይ እጃቸውን የሚያነሱትን በምን ቃል እንደምገልፃቸው ግራ ግብት ይለኛል። በህጻናት ላይ ጥቃት የሚያደርሱ ምን ዓይነት አእምሮ ያላቸው ሰዎች ናቸው? ምን አይነት ስነ ልቦና ቢኖራቸውስ ነው ወደ እርምጃ የሚገቡት? ምንስ አይነት ማህበረሰብ ውስጥ ቢያድጉ ነው? ምን አይነት ሞራል ያላቸው ይሆኑ እልና ጤነኞችስ ናቸው ስል እጠይቃለሁ? ብቻ ሁሉም በህጻናት ላይ የሚፈጸም ድርጊት ከአዕምሮ በላይ ነው።

ህጻናት የአካል ዕድገታቸው የአእምሮ ብስለታቸው በደንብ ያልዳበረ፤ በቀላሉ ሰዎችን የማመንና የመታለል ባህሪ ያላቸውና መሰረታዊ ፍላጎታቸው እንዲሟላ በትልልቅ ሰዎች ላይ ጥገኛ የሆኑ ናቸው።ታዲያ ምነት ጥለውብን በንጹህ ልቦናቸው የተጠጉንን ህጻናት ምን ሲባል ለማጠቃት ልብ ይነሳሳል? እንዴት ነው የህፃንነት ጠረናቸው ከላያቸው ሳይጠፋ፣ ኮልተፋ አንደበታቸው በደንብ ሳይፈታ ለእኩይ ምግባር መፈፀሚያ የሚሆኑት? ይህ ሁኔታ ከልክ በላይ ግራ ያጋባል። የዛሬ ባለታሪካችን ህፃን ፅናት ትባላለች። የዚህችን ልጅ ታሪክ ልነግራችሁ ስለወደድኩ ነው የጥያቄ ጋጋታ ማብዛቴ። ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

### የትንሿ ፅናት እናት

የፅናት እናት ወጣት ናት፤ ያውም አፍላ ወጣት በሚባል የእድሜ ክልል የምትገኝ። በኑሮ ዝቅተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች የተገኘች ልጅ ናት። እናት አባቷን ጨምሮ አራቱ ታላላቆቿ በቀን ያገኙትን ለመስራት ተፍ ተፍ ሲሉ ይውላሉ። ለቤተሰቧ አምስተኛ ልጅ የሆነችው የፅናት እናትም ገና ባልጠና ጉልበቷ ነበር ራሷን ለመርዳት ቆሎ መሸጥ የጀመረችው። በየጠጅ ቤቱና በየግሮሰሪው በምሽት እየተዘዋወረች ቆሎ በመሸጥ ራሷንም ሆነ ቤተሰቧን ለመደጎም ትጥራለች።

ቀላ ያለች ናት፤ ሰውነቷ ከሳ ያለ ቢሆንም ቆንጆ መሆኗን ተክለ ሰውነቷ ይመሰክራል። ያችን እንቡጥ ጽጌረዳን እንኳን መጠጥ ቤት ያያትን ይቅርና የአላፊ አግዳሚውን አይን ጭምር ታማልላለች።ታዲያ ከእለታት አንድ ቀን ግሮሰሪው ውስጥ ቁጭ ብሎ የሚጠጣ አንድ ጎልማሳ አይን ውስጥ ገባች። ቆሎ ከገዛት በኋላ ያለሰበችውን ለእሷ ብዙ ብር አስጨብጦ ሸኛት።

ባልታሰበው ልግስና የተደሰተችው የፅናት እናት የያዘችውንም ቆሎ ሳትጨርስ ነበር ለቤተሰቧ የሚያስፈልገውን ነገር ገዛዝታ ወደ ቤቷ የገባችው። ከዛ በኋላ በተደጋጋሚ ወደ ግሮሰሪው እየሄደች ቆሎ ትሸጥና ከለመደችው የተሻለ ገቢ እያገኘች ትመለሳለች።

እንዲህ እንዲህ እያለ የተወሰነ ጊዜ የመጠጥ ቤቱ ሰውዬ የፅናት እናትን ካላመዳት በኋላ አብራው ተቀምጣ መጠጥ እንድትጠጣ ይጋብዛታል። ከዛ ቀን በፊት አልኮል ቀምሳ ባታውቅም ያንን ደግ ሰው ላለማስቀየም ስትል መቀማመስ ጀመረች ። ቀምሳ የማታውቀው አልኮልና በቅጡ ጠግቦ የማያውቀው ሆዷ ባዶነት ተደምሮ የፅናትን እናት ለመጣል ብዙም አልፈጀበትም ወዲያው ሰክራ ዝልፍልፍ አለች። እያደባ ቀን ሲጠብቅ የነበረው አጥማጅ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ወደ መኝታ ክፍል ይዟት ገባ። ያኔ ነው እንግዲህ ይህች የሁሉ ልጅ የሆነችው ፅናት የተፈጠረችው።

ከሆነው ነገር በኋላ ያንን ሰው ዳግም በአካባቢው ያየው ሰው አልነበረም። ብታጠያይቅም ከስሙ በስተቀር ምንም አይነት አድራሻ ያልነበራት የፅናት እናት በፍለጋ ላይ ሆና ቀናት በቀናት ላይ እየተደራረቡ ሶስት ወር ተቆጠረ። የፅናት እናት ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ያማት ጀመር። ሆዴን አሞኝ ነው በሚል በአቅራቢያዋ ያለ አንድ ጤና ጣቢያ ስትመረመር የሶስት ወር ነፍሰጡር መሆኗን አወቀች። የወጣቷን ማርገዝ የሰሙት ቤተሰቦቿ ክብራችን ተነካ፤ አዋረደችን ብለው ከቤት ሲያባርሯት የሚያውቋት ሰዎች ሰብስበው በሰጧት ትንሽ ገንዘብ አሁን የምትኖረበትን ቤት ተከራየች።

አቅሟ እስከደከመ ድረስ ቆሎ እየሸጠች ወሯ ሲሞላ ፅናትን ወለደች፤ አራስነቷን በጎረቤቶቿ ድጋፍ አልፋ ልክ ጉልበቷ ሲጠና ዳግም ወደ ለመደችው ስራ ልጇን አዝላ ተመለሰች። ፅናት ከጀርባዋ ከወረደች ቀን አንስቶ ግን ጎረቤቶቿ ግማሹ አልባሽ፤ ገሚሱ አጉራሽ ሆኗት አንድም ቀን ስለልጇ ስጋት ሳይገባት ፅናት አምስት አመት ሞላት።

### ተወዳጇ ፅናት

ድንቡሽቡሽ ያለች ደስ የምትል ህፃን ናት። ከመጣው ከሄደው ጋር መለጠፍ የምትወድ ሁሉ ዘመዴ የሆነች ልጅ ናት። አንዱ አቅፎ ወስዶ ከረሜላ ገዝቶ ይመልሳታል። ሌላኛዋ ወስዳ ገላዋን አጥባ ፀጉራን ሰራርታ አሳምራ ትመልሳለች። ብቻ እዛው ሰፈር ውስጥ ድክ ድክ ትበል እንጂ ለማያውቃት ሰው የየትኛው ቤት ልጅ እንደሆነች በቅጡ መለየት ይከብደዋል።

ፅናት አራት አመት እንደሞላት በአቅራቢያዋ ያለ የመንግስት ቅድመ መደበኛ ትምህርት ከጀመረች በኋላ የፅናት እናት ሰው አስቸገርኩ የሚለው ሀሳቧ ቀለል ብሎላታል። ቦርሳዋን አንግታ የግቢውን ሰው በሙሉ ተሰናብታ ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ እናቷ ልብስ አጠባውንም የጉልበት ስራውንም ስትሰራራ ቆይታ ልጇን አምጥታ ግቢ ውስጥ ታስቀምጣታለች።ከዚያ በኋላ ቆሎ ለመሸጥ ትወጣና እስክትጨርስ አምሽታ ትመለሳለች።

ፅናትም ያገኘችው ቤት አምሽታ ከሰጧት በልታ እዛው ተኝታ ታገኛት ነበር። አንዷት የተረገመች ቀን ግን ይህንን እንድታደርግ አልፈቀደላትም። ያስጠጋኛል፤ ይደግፈኛል ያለችው ጎረቤት ልጅነቷን አስጣላት።

### ክፉ አድራጊው ሰው

ብዙዎቻችን በህጻናት ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ብለን የምንጠረጥራቸው ሰዎች መጠጥ በብዛት የሚጠጡ፤ የሚያጨሱ፤ በህጻንነታቸው ጥቃት የደረሰባቸው እና አፈንጋጭ የወሲብ ባህሪይ ያላቸውን ሰዎች ብቻ ናቸው ብለን እንገምታለን ።ነገር ግን ከእነዚህ ሰዎች በተጨማሪ ህጻናት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ አይችሉም ብለን የምናስባቸው ሰዎች በልጆች ጥቃት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ልናገኛቸው እንችላለን።

ይህ ሰው ከየትኞቹ አይነት ሰዎች እንደሚመደብ ግራ ቢገባም ይህችን አንደ አባቷ አባባ የምትለውን ህፃን በክፉ አይን ሊመለከታት ችሏል። ባለትዳርና የልጆች አባት የሆነው አቶ ወልደሚካኤል አሚጋ ይህችን የአምስት አመት ህፃን የሚንከባከባት መስሎ ጥቃት ያደርስበታል።

### የጭካኔው ሰደፍ

ሚያዚያ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 12፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ልዩ ቦታው ደብረ-አባይ ኢንዱስትሪ መንደር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ዕድሜዋ 5 ዓመት የሆናትን ህፃን እጇን ይዞ ነው የሄደው። ሁልጊዜ እጇን ይዞ ሱቅ በመሄድ ዳቦም ብስኩትም ይገዛላት ስለነበረ የህፃን ልቧ ስለሚገዛላት ነገር እያሰበ ከሰሩ ድክ ድክ እያለች ተከተለችው።

ሱቁን አልፈውት ሲሄዱ በጥያቄ መልክ ቀና ብላ እየተቁለጨለጨች ‹‹አባባ ይሄው ሹቁ...›› አለችው። ‹‹አ ረሳሁት እኮ...›› በማለት ሎሊፖፕ ከገዛላት በኋላ ‹‹ነይ አንድ ቦታ ደርሰን እንመለሳለን›› በማለት ይዟት የታጠረ ባዶ ቦታ በመውሰድ መሬት ላይ በጀርባዋ አስተኝቶ ድርጊቱን ፈፅሟል።

ምንም ጉዳዩ ያልገባት ህፃን ሰውየው የሚያደርገውን ከመመልከት በስተቀር ምንም እንቅስቃሴ አላደረገችም። የልጅ ገላዋን ባላሰበችው ሁኔታ የሚሰነጥቅ የህመም ስሜት ሲሰማት ከማልቀስ በላይ በሆነው ስቃይ ውስጥ ደክሟት ራሷን ሳተች። ጨካኙም ሰው አባባ እያለች የተከተለችውን ህፃን ላይ የጭካኔ እርምጃውን ከመፈጸም አልተቆጠበም። ልቡም አርራራም ሰውነቱም አልታዘዝ አላለውም። እና ለዘላለም የማይረሳ የአካልም የስነ ልቡናም ጥቃት ፈጸመ።

የ5 አመቷን ህጻን የደፈረው ግለሰብ ይህ ድርጊቱ ይጋለጥ ሲለው ለመፀዳዳት ወደ ታጠረው አጥር ውስጥ የገቡ ወይዘሮ ይመለከቱታል። ድምፃቸውን በማጥፋትም የተወሰኑ የአካባቢውን ሰዎች በመጥራት እንዳያመልጥ እየጠበቁ ፖሊስ በማምጣት በቁጥጥር ስር እንዲውል ያደርጉታል። ፖሊስም እጅ ከፍንጅ የያዘውን ተከሳሽ ወደ ህግ ቦታ ህፃኗንም ወደ ጤና ተቋም ይልካል።

### ምክር ለወላጆች

ኢንስፔክተር ተሻለ አየነው በህፃናት ላይ የሚከሰት ጥቃት ጉዳይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተባባሰ የመጣ መሆኑን አንስተዋል። ይህንን ለመከላከል እንዲቻልም ወላጆች ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ምክር ያሉትን ለግሰዋል። ወላጆች በቤት ውስጥ ህጻናትን ብቻቸውን ትተው አለመውጣት፤ ህጻናት ልጆችን በቤት ውስጥ ከማን ጋር ትተን እንደሚወጡ ማወቅ፤ ከህጻናት ጋር በግልጽ መወያየት፤ ህጻናት ራሳቸውን የሚከላከሉባቸውን ዘዴዎች ማስተማር፤ በትምህርት ቤት ስለ ስርዓተ ፆታ ማስተማር፣ ልጆች ራሳቸውን የሚከላከሉባቸውን ዘዴዎች ማሳወቅ እንዲሁም ማኅበረሰቡን ስለ ስነ-ፆታና ወሲባዊ ትንኮሳ ማስተማር ያስፈልጋል። የስርአተ ፆታ ትምህርቶችን፣ በህጻናትና በልጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ጭምር በማሳየት መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ማስተማር፣ ስልጠና መስጠት ብሎም ወርክሾፕ ከተቋማት ጋር በትብብር መስራት ችግሮችን ለማቃለል አይነተኛ መፍትሄ መሆኑን ይናገራሉ ።

### የፖሊስ ምርመራ

በለጋ እድሜዋ በለጋ አካሏ ላይ ግፍ የተፈጸመባት ጽናት አካሏን መመለስ የህክምና እርዳታ እንድታገኝ ተደርጓል። ሆኖም ግን ድርጊቱ በአእምሮዋ ሊወጣ አልቻለም። አልፎ አልፎ የመደንገጥና የመርበትበት ሁኔታዎች እያሳየች ነበር።

የህግ የበላይነት መረጋገጥ አጥፊም መቀጣትና ለሌላውም መማሪያ መሆን አለበትና ፖሊስም የአይን ምስክሮችና የሆስፒታል የምርመራ ወረቀትን በመመልከት ወንጀለኛው ላይ ተጨማሪ ምርምራ ሲያካሂድ ቆይቶ የሰነድ ማስረጃዎችን አጠናክሮና አደራጅቶ ለኮልፌ ቀራኒዮ ምድብ ዐቃቤ ህግ አቅርቧል።

የፖሊስን ማስረጃ ተከትሎም በፍትህ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የኮልፌ ቀራኒዮ ምድብ ዐቃቤ ህግ ግለሰቡ በፈፀመው በህፃናት ሴቶች ላይ የሚፈፀም የግብረ-ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ክስ ተመስርቶበታል።

በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ቀራኒዮ ምድብ ሴቶችና ህፃናት የወንጀል ችሎት የቀረበው ተከሳሽ አቶ ወልደሚካኤል አሚጋ የተከሰሰበት ክስ በችሎት ተነቦለት የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ክዶ ተከራክሯል።

አቃቤ ህግም አራት የሰው ምስክሮችን አቅርቦ በማሰማት ተከሳሹ ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በበቂ ሁኔታ አስረድቷል። በዐቃቤ ህግ በቀረበበት ክስ እና ማስረጃ መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል። ውሳኔውንም ለመስጠት ቀጠሮ ተሰጥቷል።

### የውሳኔ ሀሳብ

ፍርድ ቤቱም በተከሳሹ ላይ የመጨ ረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀነ ቀጠሮ ተገኝቷል፡፡ ግራ ቀኙንም ተመልክቶ ተከሳሽ ወልደሚካኤል አሚጋን በ14 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## “ሰው በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነው”

**ደበል ካሳ**

ሰው በምድር ላይ ሲኖር የሚያገኛቸው ጥሩም ሆኑ መጥፎ ነገሮች በሙሉ በሁለቱ ጆሮዎቹ መካከል በሚገኘው በታላቁ ህያው ኮምፒውተር አማካኝነት የሚፈጠሩ ናቸውአስደሳችም ሆኑ አሳዛኝ፣ ክፉም ሆኑ በጎ፣ በህይወት ዘመናችን የሚፈጠሩ ነገሮች ሁሉም በእኛው የሚታዘዘው የዚህ ህያው ኮምፒውተር ውጤቶች ናቸውፈረንሳዊው የሃሳብ ሊቅ ሞንቴስኩ እንዳለው በዚህ ዓለም ላይ በየቦታው ራሱን የእስር ሰንሰለት ውስጥ ቢያገኘውም ሰው በተፈጥሮው ነጻ ሆኖ ነውና የተወለደው ሰው የሚሆነውን ፈልጎ የመረጠውን አስተሳሰቡንና አመለካከቱን ነውየሆንነውና የምንሆነው ነገር ሁሉ በራሳችን ምርጫ የተፈጠረና የሚፈጠር ነው፤ ዕጣ ፋንታችንንም የምንጽፈው በገዛ እጃችን ነው፤ ያልዘራነውን አናጭድምና!

እናም መሆን የምንፈልገውን ለመሆንና ማግኘት የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት፣ በአጠቃላይ የምንመኘውን ዓይነት ስኬታማ ህይወትን ለመምራት የኮምፒውተራችንን አሰራር ማወቅ ዋናውን ቁልፍ በእጃችን እንደ መያዝ ይቆጠራልዕጣ ፋንታችን የሚወሰንበት የዚህ ግዙፍ ህያው ኮምፒውተር አሰራሩ ልክ እንደ ሰው ሰራሹ ኮምፒውተር ነው“ኮምፒውተር” የምንለው መሳሪያ ራሱ ከየት የመጣ ነው? በሁለቱ ጆሮዎቻችን መካከል በጭንቅላታችን ውስጥ የሚገኘውን “አዕምሮ” በመባል የሚታወቀውን ይህንን ሰብዓዊ ኮምፒውተር ሞዴል አድርጎ ነው እኮ ኮምፒውተር የተፈለሰፈው

ከሰማይ በታች ሁሉን የማድረግ አቅም ከፈጣሪው የተሰጠው ይህ አዕምሮ ብለን የምንጠራው ግዙፍ ተፈጥሯዊ ኮምፒውተር ታዲያ ብዙዎቻችን በየቦርሳችን ውስጥ ይዘን በየቀኑ ከምንጠቀምበት መሳሪያችን ጋር ተመሳሳይ ነውለዚያም ነው አሰራራቸው አንድ በመሆኑ የኃያሉን ተፈጥሯዊ ኮምፒውተራችንን አሠራር ለመገንዘብ ከሰው ሰራሹ ኮምፒውተር መነሳት የወደድነውምክንያቱም ብዙዎቻችን በተለይም የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሰዎች የኮምፒውተር አሠራርን በደንብ የምንናውቀው በመሆናችን ከዚሁ ብንነሳ የገዛ አዕምሯችንን አሠራር ለማወቅ ስለሚቀል ነውአዕምሮ የሚሠራው ኮምፒውተር በሚሠራበት መንገድ ነውና

በዚህ ከተግባባን የኮምፒውተር አሠራር ደግሞ “Garbage In Garbage Out” በሚባል መሰረታዊ የአሠራር ህግ ላይ የተመሰረተ ነውይኸውም “ትክክለኛ ግብዓት ትክክለኛ ውጤት” እንደማለት ነው ህጉ በአማርኛችን ሲተረጎምማለትም ለኮምፒውተራችን ትክክለኛውን ዳታ ስንሰጠው የምንፈልገውን ትክክለኛውን ውጤት ይሰጠናል፤ የተሳሳተ መረጃ ከሰጠነው ደግሞ የምናገኘው ውጤትም ያው የተሳሳተ ይሆናል፡፡

በሌላ አነጋገር ኮምፒውተራችን የምናገኘው ውጤት እኛ የሰጠነው ነው፤ ትክክለኛም ሆነ የተሳሳተ የምናገኘው ውጤት ሁሉ እኛ ለኮምፒውተሩ ያቀበልነው ነው እንጂ እርሱ በራሱ የሚፈጥረው አይደለምያልሰጠነውን አይሰጠንም

እናም በኮምፒውተራችን አማካኝነት ሥራችንን ስናከናውን ኮምፒውተራችን “ቢሳሳት” ለተሰራው ስህተት ተጠያቂው እኛ እንጂ ኮምፒውተሩ አይደለምምንጊዜም ቢሆን እርሱ የሚሰራው እኛ በምንሰጠው ግብዓት ላይ ተመስርቶ ነውና፤ በህጉ መሰረት የተሳሳተ መረጃ ባንሰጠው እርሱም አይሳሳትም ነበርና!

የአዕምሯችን አሠራርም እንዲሁ ነው! በአዕምሯችን መልካም ነገሮችን ስናስብ በህይወታችን ውስጥ መልካም ነገሮች ይከሰታሉ፣ መጥፎ መጥፎውን ስናስብም መጥፎ ነገሮች ይገጥሙናልደስታን ስናስብ ደስታን፣ ሰላምን ስናስብ ሰላምን፣ ክፋት ስናስብ ክፋትን፣ ጦርነትን ስናስብ ጦርነትን እንጠራለንበአዕምሯችን ያሳሰብነውን መቼም አንሆንም፣ ያልተመኘነውንም መቼም አናገኝም፣ ስለ ፍቅር እያሰብን ጥላቻን ከሚያራምዱ ጋር ልንገጥም፣ ሰላም ናፋቂ ሆነን ጦርነት ውስጥ ልንገባ አንችልምወደድንም ጠላንም፣ ተቀበልነውም አልተቀበልነውም ይህ እውነት ነው

ህጉ ሲጠቃለል ልክ እንደ “Garbage In Garbage Out”፣ መልካም ስታስብ መልካም፣ ክፉ ስታስብ ክፉውን ታገኛለህ” በሚል መሰረታዊ ህግ ላይ የተመሰረተ ሆኖ እናገኘዋለንከትውፊት እስከ ባህል፣ ከሳይንስ እስከ ሃይማኖት፣ ከፍልስፍና እስከ ሥነ ልቦና...ሁሉም ያረጋገጡትም ይህንኑ ነውተመልከቱ፤ “ቸር ተመኝ፣ ቸር እንድታገኝ” በማህበረሰባችን ውስጥ ዘወትር እየሰማነው ያደግነው ብሂል ነውይህ “መልካም ነገሮችን ስታስብ መልካም ነገሮች፣ መጥፎ መጥፎውን ስታስብ ደግሞ በህይወትህ ውስጥ መጥፎ ነገሮችን ትፈጥራለህ” ከሚለው የአዕምሮ አሠራር ህግ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ነው፡፡

በሃይማኖቱ ብትሄድ “ሰው በልቡ የሚያስበውን እንዲሁ ደግሞ ይሆናል” በሚል በግልጽ ተቀመጦ ታገኘዋለህሳይንስ በበኩሉ “Negative energy creates negative vibes, positive energy creates positive ones” በማለት ሲገልጸው ዲበ አካላዊ የሆነውን የአፅናፈ ዓለም ክፍል የሚያጠናው ረቂቃዊው ሳይንስ ወይም ሜታ ፊዚክስ፣ የሥነ ልቦናና የሥነ አዕምሮ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ “ሃሳብ ተመሳሳዩን ይስባል” በማለት “የስበት ህግ” በሚል ይህንኑ ህግ በሌላ አገላለጽ ያስቀምጡታል

የማይታመን የሚመስለውን ይህንን አስደናቂ የአዕምሮ አሰራር ህግን አስመልክቶ “ምስጢሩ” በተሰኘው በዝነኛዋ የሮሆንዳ ባይንሬ መጽሃፍ ውስጥ የተካተተው ታዋቂው የዘመናችን አሳቢ ቦብ ፕሮክተር እንዲህ ይላል“የትም ሁን፤ ህንድ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ፣ ስቶክሆልም፣ ለንደን፣ ቶሮንቶ፣ አዲስ አበባ ወይም ኒውዮርክ ሁላችንም የምንሰራው በአንድ ኃይል ነውበአንድ ህግ ነው- እርሱም የስበት ህግ ነውወደ ህይወትህ የሚመጣ ማንኛውንም ነገር ወደ ህይወትህ የሳብከው አንተው ነህወደ አንተ የተሳበውም በአዕምሮህ ውስጥ ስለህ በያዝካቸው ምስሎች አማካኝነት ነው

በመሆኑም በአዕምሮህ እያሰብከውና እያውጠነጠንከው ያለኸው ማንኛውም ነገር ወደ አንተ እየሳብከው መሆኑን ተረዳ”የምስጢሩ ደራሲ ትቀጥልና “የስበት ህግ የዓለማችን እጅግ ሃይለኛው ህግ መሆኑን በህይወት የነበሩ እጅግ ታላላቆቹ መምህራን ነግረውናል” ትለናለችእንደ ዊሊያም ሼክስፒር፣ ሮበርት ብራውኒንግና ዊሊያም ብሌክ የመሳሰሉት ገጣሚያን በግጥሞቻቸው ብለውታልእንደ ሉድ ቫን ቤቶቨን የመሳሰሉት ሙዚቀኞች በዜፈናቸው ገልጸውታልእንደ ሊዮናርዶ ዳቬንች የመሳሰሉ ሰዓሊያን በስዕሎቻቸው አመላክተውታልሶቅራጥስ፣ ፕሌቶ፣ ኤመርሰን፣ ፓይታጎረስ፣ ሰር ፍራንሲስ ቤከን፣ ሰር አይዛክ ኒውተን፣ ዮሐንስ ወልፍጋንግ ቮን ጎተና ቪክተር ሁጎን የመሳሰሉ ፈላስፋዎች በጽሁፎቻቸውና በአስተምህሮወቻቸው አዳርሰውታልየሁሉም ስሞች ህያው ናቸውበታሪክም ሁሌም እንደተዘከሩ ይኖራሉ፡፡

እንደ ሂንዱይዝም፣ የሄርሜቲክ ልማዶች፣ የቡድሃ፣ የአይሁድ፣ የክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች የአስተምሮቻቸው አካል አድርገው ሰብከውታልየባቢሎን፣ የግብጽና ሌሎችም ጥንታዊ ስልጣኔዎች ጽፈው አስተላልፈውታልበሁሉም ዘመናት የተደረጉ ጥናታዊ ጽሁፎች በተለያየ መንገድ ዘግበውታልከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስት ሺህ ዓመተ ዓለም በድንጋይ ላይ ተጽፎ ተገኝቷልህጉ ከጊዜ ጋር የጀመረ ነውሁልጊዜም እዛው የነበረና የሚኖር ነውየዓለምን ሥርዓት፣ የህይወት ተሞክሮህን የሚወስን ህግ ነውየትም ሁን ማን የስበት ህግ የህይወትህን ተሞክሮ የሚሰራው እርሱ ነው፡፡

ይህ ኃያል ህግ ይህን ሁሉ የሚያደርገው በሃሳቦችህ አማካኝነት ነውእናም ክፉም ይሁኑ በጎ በህይወትህ የሚፈጠሩ ነገሮች ሁሉ የአስተሳሰብህ ውጤቶች ናቸው፣ የህይወትህ ፈጣሪ በአዕምሮህ ውስጥ የምታውጠነጥነው ሃሳብህ ነውመጥፎ ስታስብ መጥፎ፣ መልካም ስታስብ መልካም ነገሮችን ትፈጥራለህGarbage In Garbage Out” ለኮምፒውተር “Garbage Idea Garbaje Life” ለሰው! ይኸው ነውሰው በልቦናው እንደሚያስበው እንዲሁ ነውና!

# ዓለም አቀፍ

## በኡጋንዳ 6 የጤና ባለሙያዎች በኢቦላ ቫይረስ ተያዙ

በኡጋንዳ አምስት ሐኪሞች እና አንድ የአንስቴዢያ ባለሙያ በኢቦላ ቫይረስ መያዛቸው ተገለጸ የሕክምና ባለሙያዎቹ በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጠ በኋላ ለሕክምና ወደ ለይቶ ማቆያ መወሰዳቸውን ዘ ኢስት አፍሪካን ዘግቧል

የሙቤንዴ የኢቦላ ቫይረስ በሽታ ግብረ-ኃይል፣ የወረርሽኝ ዋና ማዕከል፣ የኡጋንዳ የሕክምና ማኅበር እንዲሁም ብሔራዊ የሐኪሞች ቡድን በተናጠል በሰጡት መግለጫ በሽታው ከታማሚዎች ወደ ሕክምና ባለሙያዎቹ መተላለፉን አስታውቀዋል።

የኢቦላ ቫይረስ በኡጋንዳ ሲቀሰቀስ ይህ ለአምስተኛ ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያው በጉሉ ወረዳ በፈረንጆቹ 2000 ላይ የተቀሰቀሰው ነው ተብሏልበወቅቱ የሕክምና ቡድን መሪ የነበሩት ዶክተር ማቲው ሉክዊያ በቫይረሱ ሕይወታቸው ማለፉ ይታወሳል

እንደ ኡጋንዳ ጤና ሚኒስቴር በአሁኑ ወረርሽኝ




እስካሁን 24 ሰዎች በቫይረሱ ተይዘው የአምስቱ ሕይወት አልፏል። እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ከሆነ ኢቦላ በቫይረስ የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ምልክቶቹም ድንገተኛ ትኩሳት፣ ከፍተኛ ድካም፣ የጡንቻ እና የጉሮሮ ቁስለት ናቸው።ይህ የበሽታው የመጀመሪያ ምልክት ሲሆን በመቀጠልም ማስታወክ እና ማስቀመጥን ጨምሮ አንዳንዴ ውስጣዊ እና ውጫዊ መድማት ያጋጥማል።

እንደ ቺምፓንዚ ያሉትን ጨምሮ ቫይረሱ ካለባቸው እንስሳት ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ሲኖር ቫይረሱ ወደ ሰዎች ይተላለፋል። ከሰዎች ወደ ሰዎች ደግሞ የሚተላለፈው በደም ንክኪ፣ ከሰውነት በሚወጣ ፈሳሽ እና በቫይረሱ ከተበከለ አካባቢ ጋር በሚኖር ግንኙነት ይተላለፋል።

በቫይረሱ ሕይወቱ ያለፈ ግለሰብ አስከሬንን መንካትም ለቫይረሱ ያጋልጣል። ቫይረሱ ምልክት ለማሳየት ከሁለት እስከ ሦስት ሳምንት ሊፈጅበት ይችላል። ህክምናውም ቢሆን አስቸጋሪ የሚባል ነው። በሽታው በአፍሪካ ተደጋግሞ ሲያጋጥም አንድ ጊዜ ደግሞ በፊሊፒንስ መከሰቱ ታውቋል።

## ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ አብሮነት፣ ትብብር እና ልማት ላይ እንዲያተኩር ቻይና ጠየቀች

ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ የአብሮነት እና ትብብር መንፈሱን እንዲያሳድግ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) የቻይና ምክትል ቋሚ ተወካይ ዳይ ቢንግ ጠየቁዳይ ቢንግ መልዕክታቸውን ያስተላለፉት በ77ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ መሆኑን ሲጂቲ ኤን ዘግቧል፡፡

ዳይ ቢንግ በመድረኩ በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚስተዋሉ የማኅበራዊ ፣ ሰብዓዊ እና የሙብት ጉዳዮችን በተመለከተም አንስተው መዳሰሳቸው ነው የተገለጸው፡፡ ዳይ ቢንግ ልማት ለሠላም እና መረጋጋት መሠረት መሆኑንም አንስተዋልኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታትም ልማት ቁልፍ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ ቀጣናዊ ግጭቶች ፣ የምግብ ዋስትና ፣ የኃይል አቅርቦት፣ የዓየር ንብረት ለውጥ እና የመሳሰሉ የተወሳሰቡ ጉዳዮች ላይ በትብብር መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ያደጉ ሀገራት ልምዳቸውን ለታዳጊ ሀገራት በማካፈል እንዲሁም የዕድገት ግብዓቶችን በማቅረብ እና በመደገፍ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጠይቀዋል፡፡

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የልማት ጉዳይን ዋና እና አንገብጋቢ ጉዳዩ አድርጎ እንዲመለከተውም አሳስበዋል፡፡ልማትን ዕውን ለማድረግ የዓለምአቀፉን ማኅበረሰብ የተቀናጀ የፖሊሲ ትብብር እና ትግበራ አጋርነት ማስፋፋት እንደሚያሻም ዳይ ቢንግ ተናግረዋል፡፡

ቻይና የአፍሪካ ሀገራትን የግብርናና የማምረቻ ዘርፍ ምርቶችን ወደ ሀገሯ በማስገባት የተጀመረውን እድገት እንዲቀጥል እንደምታደርግም ተናግረዋልቤጅንግ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በዲጂታል ኢኮኖሚ፣ በጤና፣ በአረንጓዴ ልማትና በሌሎችም ዘርፎች ተባብሮ የመስራት ፍላጎት እንዳላት ታውቋል፡፡




የቻይና ምክትል ቋሚ ተወካይ ዳይ ቢንግ

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ቤተሰብና በዓል

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

የምናብ ታሪካችን ወደ አንድ ለበዓል ትልቅ ቦታ ወደ ሚሰጥ ቤተሰብ ይወስደናል። የቤተሰቡ አባላት በአመት ውስጥ ካሉት በዓላት መካከል በአንዱ በዓል ላይ ከያሉበት ተሰባስበው ቤተሰባዊ ጊዜ የማሳለፍ ልማድ አላቸው። የዘንድሮ በዓል ላይ ለመገኘትም ከየአቅጣጫው ጉዞ አድርገው ከአባትና እናታቸው ቤት ደርሰዋል። አንዱ ወንድማቸው ግን በሚጠበቅበት ጊዜ አልደረሰም። የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ የተሰማራው ወንድማቸው በሚጠበቀው ሰዓት ሊደርስ እንደማይችል ይጠብቁትም ነበር።

ይህ የቤተሰብ አባል ዘወትር ስራን ምክንያት በማድረግ እንደ ሌሎቹ የቤተሰብ አባላት በትኩረት አለመገኘቱም ሁሉም ቅይማት እንዲሰማቸው ያደረገ ነው፤ ለቤተሰብ ቦታ የለውም በማለት። በተመሳሳይ ስራ ላይ የተሰማሩ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ግን መኪናቸውን አቁመው ለቤተሰብ ቦታ በመስጠት ከበዓሉ ሲገኙ የወጣት ወንድማቸው ጉዳይ ግን ሁሌም ይከነክናቸዋል። ዘወትር የሚያቀርቡበት ክስ ለቤተሰብ ቦታ አይሰጥም ከቤተሰብ በላይ ገንዘብ ይበልጥበታል የሚል ነው።

ዘግይቶም ቢሆን ማምሻው ላይ የቤተሰቡ አባል ከስፍራው ደረሰ። ዛሬ የገጠመው ግን የተለየ ሆነ፤ ታላቅ ወንድሙ የእርሱን መግባት አይቶ ተነስቶ ወጣ። ምክንያቱ "ብሞት በቀብሬ ላይ ከማይገኝ ጋር አብሬ በዓል አላሳልፍም፤ እርሱ ወንድሜም አይደለም" የሚል ነው። ሌላው የቤተሰብ አባል በመቀጠል፤ "እርሱ በእዚህ ሰዓት የሚመጣው ለቤተሰቡ ንቀት ስላለው ነው፤ ከቤተሰብ በላይ ገንዘብን ስላስቀደመ ነው"በማለት ተነስቶ ወጣ። እናት እና አባት ግን በሁኔታው አዘኑ። ልጃቸው ዘግይቶ የመጣ መሆኑ ደስ ባያሰኛቸውም በልጆቻቸው መካከል አታካሮ በመፈጠሩ አዘኑ። ሁለቱም ልጆች ወጥተው ሄዱ፤ ለደስታ የታሰበው በዓል ለሃዘን ሆነ።

በማግስቱ ማለዳ እናት መኪና አስነስቶ የሄደውን ልጃቸውን ፍለጋ በበዓል ቀን አርባ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የሚገኘው የልጃቸው ቤት ሄዱ። የእናትነት አንጀታቸው አላስችል ብሏቸው ለልጃቸው ቁርስ ቋጥረው አደረሱ። የእናት ልብ፤ የአባት ቀልብ።የተቀሩት የቤተሰብ አባላትም በማዘን ድባብ ውስጥ ሆነው በዓሉን አሳለፉት።

ለወትሮውም አልኮል መጠጥ መውሰድ ልማዳቸው የሆኑት የቤቱ አባወራ በእለቱ አብዝተው ከወደ ውሃው ወሰዱ። አብዝተው መውሰዳቸውም በልባቸው ስለሌላው የቤተሰብ አባላት የቋጠሩትን አውጥተው እንዲናገሩ ስላደረጋቸው የቤተሰቡ በዓል እንደወትሮው ሳይሆን ይበልጥ መበጥበጡን ቀጠለ። አታካሮ እንዲሁም እምባን የቋጠሩ አይኖች ታዩ፤ ቤተሰቡ ውስጥ በይሉኝታ ተሸፍኖ ተደብቆ የነበረው ሁሉ በመጠጥ ሃይል ወጣ። ቤተሰቡ በሃዘንም ሆነ በደስታ አብሮ ሲቆም በውስጡ ያለ ሽንፍልና ሳያጠራ በመሆኑ በንግግር እርስበእርስ መጎዳዳት ሆነ። በጥንቃቄ ሊያዝ የሚገባው ቤተሰብ የተሰኘው ተቋም በግጭት ውስጥ ታመሰ።

ሁኔታውን በእርጋታ የሚመለከቱ የነገ የቤተሰብ መሪዎች ህጻናትና ታዳጊዎች በስፍራው አሉ። ከልጆቹ መካከል የስምንት ዓመት ልጅ በስተመጨረሻ በውስጡ የያዘውን በልጅ አንደበቱ ይናገር ጀመር እንዲህ በማለት "እማማ፤ አባባ፤ እህትዓለም፤ ወንድምዓለም ለካስ ሁለት አይነት ሰዎች ናችሁ። ስትናደዱ ሌላ፤ ሳትናደዱ ሌላ። እውነተኛው ግን የትኛው ነው? ስትናደዱ የምትሆኑት ወይንስ ሳትናደዱ?" ብሎ ጠየቃቸው። የህጻኑ ጥያቄ እውነትነት ያለው በመሆኑ ሊመልስለት የሚችል አልነበረም። ሁሉም አንገቱን አቀርቅሮ የምን ውርጅብኝ ወረደብን እያለ ያብሰለስላል። በበዓል ስም የተሰባሰበው ትልቅ ቤተሰብ ቀላል በሚመስለ ጸብ እያዩት በውስጡ ያለው ችግር እንደ ዳንቴል እየተተረተረ ሄደ።

ትልቅ የሚባል ቤተሰብ አነስተኛ በምትባል ግጭት ምክንያት ብጥብጥ ውስጥ ገብቶ ቅጽበት በሚባል ደረጃ ቤተሰብ ተጎድቶ ሊበታተን እንደሚችል የሚያሳይ። እንዲህ ባለ ገጠመኝ ውስጥ እስከወዲያኛው የሚሆን ስንጣቅ የመፈጠሩን ያህል ህይወትን የሚያሳጣ ክስተት ሊከሰት እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። እርቅ የሚባለው የባህላችን ጠንካራ ክፍል ባይኖር ኖሮ በትንሽ በትልቁ ቤተሰብ ሊበተንም ይችል ነበር። ለእርቅ ቦታ መስጠት በቻሉ በርካታ ቤተሰቦች ውስጥ ችግሮች በእርቅ እየተፈቱ፤ እየተጠገኑ፤ እየተስተካከሉ ሲሄዱ፤ በተቃራኒው መንገድ ላይ የተገኙ ቤተሰቦች ግን እየኖሩ ግን ተለያይተው ሲኖሩ እንመለከታለን።

ጉዳዩን የሰሙ በአካባቢው የተከበሩ አባት ከቤታቸው ከበዓል ፕሮግራም ተነስተው ወደ ጎረቤታቸው መጥተው ነገሩን በውል ከተረዱ በኋላ በስልክ እርቀው ያሉትንም አናግረው ሰላም ለማውረድ ሞከሩ። ሙከራው በእለቱ ባይሳካም ሁሉም ከበዓል ድባብ ወጥቶ በእርጋታ ነገሩን ወደፊት ሊያየው ሃሳብ ቀርቦ ተስማሙ። ብዙ ብር ወጥቶ ከሌሎች ፍላጎቶች ተቀንሶ የተደገሰው ድግስ፤ ከተለያየ ቦታ የተሰባሰበው ቤተሰብ፤ ለነገሮች ባለ የእይታ ልዩነት ምክንያት የናፈቀውን በዓል በአግባቡ ሳያጣጥም ወደየቤቱ ተበተነ። በእርቅ ወቅት ነገሮች መስመር እንደሚይዙ ተስፋ ያደረጉት ሽማግሌም መካከለኛ ሆነው ተገኙ። ለዚህ ቤተሰብ መልካም እንዲሆን እየተመኘኝ'ቤተሰብና በዓል' ብለን እንቀጥል።

### ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር

የምናብ ታሪካችን ቤተሰብ ውስጥ የተከሰተውን ነገር ስናይ ቅድሚያ ሊሰጠው ስለሚገባ ነገር እናነሳለን። ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር አጠገባችን ካሉ ሰዎች አድናቆትም ሆነ ትችት እንድናስተናግድ ሊያደርገን ይችላል። ቅድሚያ በምንሰጠው ነገር የሚገጥመንን ተግዳሮት እንዴት ማለፍ እንዳለብን ማሰብ አስፈላጊነቱ የሚገባን እንደ ወጣቱ የቤተሰብ አባል የከፋ ተቃውሞ ሲገጥመን ሊሆን ይችላል። አስቀድሞ ያንን መግራት የቻሉ ግን እነርሱ ጥበበኞች ናቸው።

በመርህ ደረጃ ቅድሚያ ልንሰጠው ስለሚገባ ነገር ቅድሚያ መስጠት ችግር ሳይሆን ትክክለኛ ውሳኔ ነው። ነገርግን ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር አደጋ ይዞብን እንዳይመጣ ማሰብ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ቅድሚያ የሰጠነው ነገር ሌላ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባን ነገር እየደፈጠጠ መሆን አለመሆኑንም መረዳት አለብን ። ቅድሚያ የምንሰጠውን ለይቶ ማወቅ አንድ ነገር ሆኖ ቀጣዩ ነገርግን ቅድሚያ በምንሰጠው ነገር ሊከተል የሚችለውን ተግዳሮት ለይቶ በተግዳሮቱ ላይ መስራት ነው። የትራንስፖርት ባለሙያው ዘወትር ለስራው ትኩረት እየሰጠ ከቤተሰብ የጋራ መገናኛ በዓል ሲጎድል ቅድሚያ ሊሰጥ ለፈለገው ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም ቤተሰቡ እንዲረዱት ማድረግ ግን ነበረበት፤ ነገርግን አልሆነም። ባለመሆኑም ግጭት ተፈጠረ፤ ግጭቱም ሌሎች ግጭቶችን እየፈጠረ ሄደ።

በህጻንነት እድሜ ላይ ያሉ ልጆች ፊትለፊታቸው ላለው ነገር ቅድሚያ ይሰጣሉ። ፊትለፊታቸው ያለውን ነገር ተመልክተው መጨበጥ የፈለጉትን ለመጨበጥ ማድረግ የሚገባቸውን ያደርጋሉ። ማድረግ የሚገባቸው ማልቀስ ከሆነ በሚችሉት አቅም ያለቅሳሉ። ለመጨበጥ የሚሞክሩት ነገር የሚጎዳቻው ይሁን አይሁን የሚያውቁበት መንገድ የለም። ጎጂም ቢሆን ያደርጉታል። በጊዜ ሂደት ግን ጎጂውን ከመልካሙ እየለዩም ይመጣሉ፤ መቅደም ያለበትን ከሌላው ይለያሉ። በእድሜ ውስጥ በማደግ ሊታዩ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባውን ነገር ማወቅ መቻል ነው።

ከቤተሰብ ጋር ጊዜን መስጠት ቅድሚያው ያደረገና ጊዜውን በስራ በማሳለፍ ተጨማሪ ገቢ ማግኘትን ቅድሚያው ያደረገ ሁሉም ቅድሚያ የሰጡት ነገር አለ፤ በውስጣቸው በከበደው ነገር ልክ። ሁለቱም በራሳቸው ሚዛን ትክክል ናቸው። በዓልን ለመደገስ ተበድሮም ቢሆን የሚያደርገው ሰውና በአቅሙ ልክ ብቻ የሚደግስ ወይንም ከአቅሙ በታችም የሚደግስ ሁሉም ቅድሚያ የሰጡት ጉዳይ አለ። አሁንም ሁሉም በሚዛናቸው ትክክል ናቸው። ጥያቄው ቅድሚያ የሰጡት ነገር ምን አስከትሎ እንደሚመጣ ይረዳሉ የሚል ነው።

ከድርጊቱ ቀጥሎ የሚመጣውን አውቆና ተዘጋጅቶ መስራት አስፈላጊ ነገር ነው። የጥበብም መንገድ ያለው እዚያ ውስጥ ነው። ቅድሚያ የሰጠነው ነገር ሌሎችን በምን ደረጃ እንደሚነካም መገንዘብ እንዲሁ የተገባ ነው። የበዓል ሰሞን ያለውን ነገር ሁሉ አድፋፍቶ እለቱን ብቻ በደስታ ለመዋል የሚደረግ ጥረትን በምንም መመዘኛ ትክክል ነው ተብሎ ሊጠቀስ አይችልም። በእለቱ ያለው ገንዘብ ሁሉ መበተን አለበት የሚል ስሌትም በሰፊው የሚስተዋል ይመስላል። የበዓሉ ድባብ ሲያልፍ እያንዳንዱ ሰው የሚጋፈጠው እውነታው ግን ግልጽ ነው። በመሆኑም የጥበብ መንገዳችን ቅድሚያ የሚሰጠውን ለይቶ በማውጣት ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ በመስጠት መንቀሳቀስ መቻል ነው፤ አትራፊነት እንጂ ኪሳራ የሌለው መንገድ። ከህጻንነት ጀምሮ ያለው የእድገት መንገድ ቅድሚያ ሊሰጥ የሚገባውን መለየት እንድንችል ካላደረገ እድሜ ቁጥር ብቻ ይሆናል።

እንደ ማህበረሰብ አኩሪ የሆኑ በርካታ እሴቶች አሉን። እንደ ማህበረሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው ለሚገባ ቅድሚ የመስጠት እድገታችን ግን እንዳስቆጠርነው አመት አይመስልም። የበዓል ሰሞን ዳንኪራ የሚያሳየን ይህንን ነው። ነገሮችን በልክ ማድረግ አለመቻል እስከ ህይወት መጥፋት ድረስ ሲያደርስ ይስተዋላል። ዳንኪራ ያው ዳንኪራ ነው፤ ስካርም ያው ስካር ነው፤ ከሰዓታት በኋላ ስሜቱ በኖ የሚጠፋ ከትላንቱ ዳንኪራ ሆነ ስካር ጋር ተዳምሮ ነገ ላይ ጎጂ መስራት የማያስችል።

### የቤተሰብ ቦታ

ከዴዝሞንድ ቱቱ አባባሎች መካከል አንዱ "ቤተሰብህን አልመረጥክም፤ እነርሱ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ አንተም እንደሆንከው" የሚል ነው። ለቤተሰብ ትልቅ ቦታ ለመስጠት መነሻ ከሚሆኑት ነገሮች መካከል ቤተሰብን መርጠን አለመወለዳችን እና አጋጣሚ በሚመስል ሁኔታ ውስጥ የፈጣሪ ጣልቃገብነት ያለው በመሆኑ ነው። ትምህርትን መርጠን እንማራለን፤ የመኖሪያ አካባቢን እንዲሁ መርጠን ልንቀይር እንችላለን፤ ነገርግን ከእከሌ ቤተሰብ ልወለድ ብለን ፈጽሞውኑ ምርጫ አላደረግንም።

ቤተሰብ በህይወታችን ውስጥ ትልቅ ቦታ ሊኖረው የተገባ ነው። አንድ ግለሰብ ከራሱ ቀጥሎ የሚያገኘው ቤተሰቡን ነው። ለቤተሰብ ተገቢውን ቦታ በሚሰጡ ሀገራት ላይ የተደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩት የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር የቤተሰብ ጠንካራ መሆኑ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው። ቤተሰብ ቦታ በተሰጠው መጠን ማደግ ይችላል። እድገቱም ሁሉን አቀፍ ይሆናል፤ ከትውልድ ትውልድም ተጽእኖው ይቀጥላል።

ግለሰባዊ ደስታም ጋር እንዲሁ የቤተሰብ ህይወት ቀጥተኛ ተጽእኖ አለው። ደስተኛ ያልሆኑ ሰዎች ቤተሰብ ብንሄድ ተመሳሳይ ነገር የማግኘታችን እድል ሰፊ ነው። ቤተሰብ ውስጥ የሌለ ደስታ በግለሰብ ህይወት ውስጥ ላይታይ ይችላል። ጆን ማእከስዌል የተባሉ ሰው "ቤተሰብና ወዳጅነት ሁለቱ የደስተኝነት ማቀጣጠያ ናቸው" ማለታቸውም ከእዚህ አንጻር ነው።

ቤተሰብ ባለንበት ዘመን ከየአቅጣጫው ፈተና እየበዛበት ያለ ይመስላል። ግለኝነት እየነገሰ በመጣበት ሁኔታ የቤተሰብ እድገት ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ አለው። በሁለት ጥንዶች ጋብቻ ውስጥ የሚወለዱ ልጆች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆሉ ልጆች ለሰፊ ማህበረሰባዊ ቀውስ ተጋላጭ እየሆኑ እንደሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፤ ቤተሰብም እንደ ተቋም ጉዳትን እያስተናገደ እናገኛለን። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1960ዎቹ ውስጥ 95% የሚሆኑት አሜሪካውያን በሁለት ጥንዶች ትዳር ውስጥ እንደሚወለዱ የሚያሳይ ጥናት አሁን ባለንበት ዘመን 40% የሚሆኑ ልጆች በነጠላ ወላጅ ወይንም በጋብቻ ውስጥ ባልሆነ ሁኔታ እንደሚወለዱ ያነሳል https://gillespieshields.com/40-facts-two-parent-families/

ቤተሰብ ትልቅ ተቋም መሆኑን እና ተገቢው ቦታ



ሊሰጠው እንደሚገባ ማመን አስፈላጊ ነው። ለቤተሰብ ቦታ መስጠት መገለጫዎቻችን ግን ሊለያዩ ይችላሉ፤ አንዳንዱ ለቤተሰብ ቦታ መስጠትን የሚያየው በገንዘብ በመርዳት ነው። እንዲህ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦች ለቤተሰባቸው በአካል ከሚሰጡት ጊዜ በላይ ገንዘብ ለመስራት ተሯሩጠው ገንዘብ ቢሰጡ ይመርጣሉ። የብዙ ነጋዴዎች ችግርም ይህ እንደሆነ ይነገራል። ከሀገር ሀገር ተንቀሳቅሰው ገንዘብ ከእጃቸው አድርገው ለቤተሰባቸው የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ማሟላት ዋናው ነገር እንደሆነ ያስባሉ። በገንዘብ ቤተሰብን መርዳት የሚገባ ነገር ቢሆንም ብቸኛው ግን አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በቤተሰብ ውስጥ ያሉ በርካታ ችግሮች ከገንዘብ ጋር ብቻ የተገናኙ አይደሉምና።

ሌላው ለቤተሰብ ጊዜ መስጠትን ዋና ጉዳይ ያደርጋል። በኢኮኖሚ ችግር ውስጥ እየኖሩ ነገርግን ከቤተሰብ ጋር ተጠባቆ መገኘትን የትክክለኛነት ማሳያ አድርጎም ይቀርባል። ቤተሰብ በችግር ውስጥ መሆኑን እያወቁ እግዛ ማድግ አለመቻል ተገቢነት የለውም። ቤተሰበን በገንዘብ፤ በምክር፤ እንዲሁም በመረጃ መርዳት አስፈላጊነት አለው። ጊዜን ብቻ በመስጠት ውስጥ ውጤታማ የቤተሰብ ህይወትን መገንባት አይቻልም። ሁልጊዜ የቤተሰብን ቦታ ለማየት በሚዛን መሆኑን ማሰብ አስፋላጊ ነው።

ሚዛን ነገሮች በልካቸው መሆናቸውን የምናረጋግጠበት ነው። በቤተሰብ ህይወት እንዲሁም በአጠቃላይ በስጋ ዝምድና ውስጥ ጊዜ፤ ገንዘብ እና ምክር ትልቅ ቦታ ይይዛሉ። ጊዜ ለመጨዋወት፤ ለመቀለድ፤ እግር ለመተጣጠብ፤ ያለፈን ትዝታ አንስቶ አብሮ ትዝታን ለመጋራት ወዘተ አስፈላጊ ነው። ገንዘብ ደግሞ በቁሳቁስ፤ እንዲሁም በሌሎች ኢኮኖሚያዊ ትርጉም ባላቸው ነገሮች ከጎን መሆን መረዳዳት አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ጠንካራ የቤተሰብ ህይወት አንጻር በቤተሰብ ውስጥ ያለውን መካፈል ትልቅ ፋይዳ አለው። ያለችውን ትንሿን ቦታ ተካፍሎ አብሮ ከመኖር አንስቶ መሶብ እስከመጋራት ድረስ እጅግ የገዘፈን የችግር ወራት አብሮ ማለፍ ይቻላል። ስንቱ ቤተሰብ በአንድ ክፍል ውስጥ እንደሚኖር ስንመለከት ትርጉሙ ትልቅ መሆኑ ይገባናል። በአንዱ ክፍል ውስጥ ባልና ሚስት፤ ልጆች እንዲሁም አብሮ የሚኖር እህት ወይንም ወንድም ሲጨመርበት እናስተውላለን። በዚህ መንገድ ለቤተሰብ የሚሰጠው ቦታ ትልቅ መሆኑኑን እናስባለን። ምክር ደግሞ ሌላው ነገር ነው። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚያልፍበት የህይወት መንገድ አለ። ይህን የሚያልፍበትን መንገድ ተረድቶ አንዱ ለአንዱ በምክር ለመቆም የሚያስፈልገው ከገንዘብም እንዲሁም አብሮ ጊዜን ከማሳለፍም ከፍ ያለውን ትኩረት ነው። በምክክር የሚፈቱ ብዙ ችግሮች ይኖራሉና።

የበዓል ድግስ በበዛበት ወር ውስጥ ስንሆን በአንድም በሌላም ከቤተሰብ ጋር መገናኘትን መነሻ በማድረግ ቤተሰብን በአግባቡ እናስብ ዘንድ የተጻፈ። ቤተሰብ ግን ከበዓል በላይ ነው።


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ነገን ዛሬ እንሥራ!
DERBA CEMENT
ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ነገን ዛሬ እንስራ
ሆት ላይን 8688
DT
DERBA
Hotline 8688
DERBA DRILLING
የደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ የደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ ማህበር እና የደርባ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ሀይድሮሎጂ ኃ.የተ.የግ.ማህበር
ማኔጅመንት እና ሠራተኞች እንኳን ለ 2015 ዓ.ም እሬቻ በዓል በሠላም አደረሳችሁ እያሉ መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ!
ደርባ ሲሚንቶ
DERBA CEMENT
ሆት ላይን፡ 8688
ስልክ፡+251 11 554 9888 ፋክስ ፡ +251 11 5549808 ፖ.ሣ.ቁ ፡ 23202 ኮድ 1000
ceo@derbacement.com www.derbacement.com አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የእግረኛ መንገዶችና የአረንጓዴ ስፍራዎች ልማት ተምሳሌት

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ከተማዋ በነዋሪዎቿ፣ በስራ አጋጣሚ ወይም እግረ መንገዳቸውን በተመለከቷት ሁሉ አእምሮ ወይም ልብ ውስጥ የመቅረት ልዩ መስህብ አላት። ይሄ ደግሞ የሚመነጨው ከሀይቋ፣ በፕላን የተከተመችና የውብ መንገዶች ባለቤት ከመሆኗና በየጊዜው እያደገች ካለችበት ሁኔታ ብቻ አይደለም፤ ከሰፋፊ ውብ መንገዶቿ በተጓዳኝ ለእግረኞች ከምትገነባቸው ውብ መንገዶች፣ በዛፎች፣ በሳር፣ በአበቦችና በመሳሰሉት ተክሎች ከተዋቡት አረንጓዴ ስፍራዎቿም ነው።

አረንጓዴ ስፍራዎቿ በሞቃታማነቷ የምትታወቀውን ሀዋሳ ነፋሻ፣ ከጸሀይ ሀሩር መሸሻ ጥላ በመሆን ያገለግሏታል፤ የአይን ማረፊያ አርገዋታል፤ የሀገራችን ከተሞች በህንጻና በመሳሰሉት ግንባታዎች እየተጠባቡ ባለበት በዚህ ዘመን፣ ሀዋሳ ለክፍት ቦታዎች ፊትም አሁንም እየሰጠች ያለችው ትኩረት በእጅጉ በአርአያነት ሊያስጠቅሳት የሚችል ነው። ከተማዋ አረንጓዴ ስፍራዎቿን በማልማት በኩል ሁሌም ባተሌ ናት፤ ከከተማ ለጥቂት ጊዜያት ወጣ ብሎ የተመለሰም ሳይቀር በእነዚህ ስፍራዎች ላይ የተጨመረ እንጂ የተቀነሰ አይመለከትም። ይህን ልማቷን የሁሌም አርጋው ኖራለች።

የከተማዋ ማዘጋጃ ቤትም እነዚህን የከተማዋን ክፍት ቦታዎች ወይም አረንጓዴ ስፍራዎች አሁንም በራሱም በማህብረሰቡና በተለያዩ ተቋማት ማልማቱን እንደቀጠለበት በቅርቡ በስራ አጋጣሚ በከተማዋ በተገኘሁበት ወቅት ከማዘጋጃ ቤቱ ምክትል ሃላፊው አቶ ታሪኩ ታመነ መግለጫ ተረድቻለሁ።

በአንድ ወቅት የሀዋሳ ማዘጋጃ ቤት የከተማዋን የአረንጓዴ ስፍራዎችን ማልማቱን አጠናክሮ ለመቀጠል ሲነሳ ክፍለ ከተሞች ለማልማት ፈልገው የቦታ ጥበት አጋጠማቸው ሲሉ ያስታወሱት የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት ምክትል ሃላፊ አቶ ታሪኩ፣ ምን ይሻላል ተብሎ ሲታሰብ ክፍት ቦታዎች/ ፐብሊክ ስፔሶች አሉ፤ ለምን እነሱን አናጣራም /ቼክ አናደርገም/ ብለን ተነሳን ይላሉ። ቦታዎቹ በተለያዩ ሼዶች መያዛቸውን አረጋግጠው ማጽዳት ሲጀመር ሌሎች ፐብሊክ ስፔሶች በግለሰቦች መያዛቸው ተደረሰበት የሚሉት አቶ ታሪኩ፣ በዚህ መነሻነት ሌላ መድረክ ተፈጥሮ ከህብረተሰቡ ጋር መግባባት ላይ ተደርሶ ወደ እርምጃ ተገባ ሲሉ ያሰታውሳሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የሀዋሳ ማዘጋጃ ቤት በ2014 በጀት አመት በህብረተሰብ ተሳትፎ በሚሰሩ ሃያ አራት አጀንዳዎች ነበሩት። በበጀት አመቱ መስከረም አራት ቀን በእዚህ አጀንዳዎች ላይ የንቅናቄ መድረክ ከፈተ። ከተማዋ ጽዱ ውብ አረንጓዴ በሚል የምትታወቅበትን ገጽታዋን አጠናክሮ ለማስቀጠል ሁሉም ባለቤት ሆኖ በብሎክ በመንደር በቀበሌ እቅድ ወጥቶ ወደ ትግበራ እንዲገባ ተደረገ።

የሀዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ምክትል ሃላፊ አቶ ታሪኩ ታመነ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሀዋሳ በተካሄደ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አንድ መድረክ ላይ የተገኙ የሚኒስቴሩ የስራ ሃላፊዎችና ከተለያየ ተቋማት የተውጣጡ የመገናኛ ብዙሃንና የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት የመሰረተ ልማት ስራዎችን ባስጎበኙበት ወቅት እንዳሉት፤ በዚህ በተፈጠረው መነቃቃት ማዘጋጃ ቤቱ መጀመሪያ 12 ሺ ካሬ ሜትር በተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች በህገወጥ መንገድ ተይዞ የነበረ ፐብሊክ ስፔስ ለማጽዳት አቅድ ተያዘ፤ እቅዱ እየተሳካ ሲመጣ አሀዙን ወደ 25 ሺ ማሳደግ ውስጥ ተገባ። በተሰራው የተጠናከረ ተግባር 79 ሺ ካሬሜትር ክፍት ቦታዎች /ፐብሊክ ስፔስ/ ከህገወጦች ማስለቀቅ ተችሏል ።

እንደ ምክትል ሃላፊው ማብራሪያ፤ ንቅናቄውን ተከትሎ ክፍት ቦታዎችን /ፐብሊክ ስፔሶችን/ና የእግረኛ መንገዶችን /ዎክ ዌይዎችን/ የማጽዳቱ ስራዎችን የተለያዩ ከተሞች ሃላፊዎች እየጎበኙ ልምድ እየቀሰሙበት ይገኛሉ። እናንተም ሳትሰሙ አትቀሩም ብዬ አስባለሁ፤ በከተማዋ ስትዘዋወሩ የምትመለከቱትም ይሆናል ሲሉ ምክትል ሃላፊው አብራሩ።

ሀዋሳን ከሌሎች ከተሞች የሚለዩዋት ስትመሰረትም በፕላን የተመሰረተች ከተማ መሆኗ ነው፤ አስፓልቶቿ ከአሁኑም በተሻለ እስከ 30 እና 40 ሜትር ስፋት ያላቸው ፣ ብዙ ላንድስኬፖች፣ የእግረኛ መንገዶች /ዎክ ዌይዎች/ አላቸው። የተለያየ የፓለቲካ አለመረጋጋት በተፈጠረ ቁጥር ግለሰቦች እነዚህን ቦታዎች እየወረሩ ሼዶች እየገነቡ ይሰሩ የነበረበት ሁኔታ ነው ክፍት ቦታዎቹ በአግባቡ እንዳይለሙ አርጓቸው ቆይተዋል።

እነዚህን ህገወጥ ግንባታዎች ወደ ማፍረስ ከመግባታችን በፊት መጀመሪያ ላይ ከህብረተሰቡ ጋር ተግባቦት ፈጥረናል የሚሉት አቶ ታሪኩ፣ ከክፍለ ከተማና ቀበሌ አመራሮችና መዋቅሮች እንዲሁም ከህብረተሰቡ የተለያዩ አደረጃጀቶች ጋር በማእከል ውይይት ተደርጎ የጋራ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ህብረተሰቡ ራሱ አምኖ እርምጃ እንዲወሰድ ነው የተደረገው ሲሉ ያብራራሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች ህንጻዎችን ለሌላ ተግባር በማዋል በመንግስት ክፍት ቦታዎች ላይ የንግድ ስራ ይሰራ እንደነበር ጠቅሰው፣ የማጽዳቱ ስራ ሲከናወን ወደ ህንጻቸው ተመልሰው ስራቸውን እንደቀጠሉ ጠቁመዋል። ሼዶችን ተከራይተው ይሰሩ የነበሩትም ሌላ አማራጭ እንዲፈልጉ ሁለት ወር እድል ተሰጧቸው እንዲነሱ መደረጉን ገልጸዋል።

የማጽዳቱ ስራ አይቀጥልም ብለው በማሰብ ሌላው ሲያፈርስ ያላፈረሱ እንደነበሩም አስታውሰው፣ እርምጃው እየተጠናከረ ሲመጣና ሌሎች ማፍረሳቸውን ሲመለከቱ እነዚህም ያለምንም የጸጥታ ሀይል ጫና ወደ ሼዶቹን ማፈረሳቸውን ነው አቶ ታሪኩ የጠቀሱት።

አሁን መልሶ ማልማቱ ተጀምሯል፤ አቶ ታሪኩ አሮጌው መናኸሪያ አካባቢ ከዋርካ ሆቴል አደባባይ አንስቶ በአሮጌው መነሃሪያ ፊት ለፊት ወይም በሌዊ፣ በሹ ሆቴል ፊት ለፊት ባለው ክፍት ቦታ ላይ እየተካሄደ ያለውን ውብ የእግረኞች መንገድና የተለያዩ የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን በአብነት ይጠቀሳሉ። ይህ ፕሮጀክት በስተቀኝ በኩል ከዋንዛ ሰርክል ተነስቶ ሼል በመባል እስከሚታወቀው ማደያ ድረስ ይዘልቃል። እነዚህ ቦታዎች ለአመታት በአቅራቢያቸው በሚገኙ ድርጅቶችና በተለያዩ አካላት ሼዶች ተገንብተውባቸው ለተለያየ አገልግሎት ሲውሉ ኖረዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ስፍራ ወደ ልማቱ ከመገባቱ በፊት ከህብረተሰቡ ጋር መግባባት ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ እንዲጸዳ ተደርጓል። አካባቢው በምስራቅ ክፍለ ከተማ ስር ይገኛል። በዚህ ክፍለ ከተማ ብቻ 12 ሺ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ማጽዳት ተችሏል።

ይህን መልሶ ለማልማት ብዙ ካፒታል ይጠይቃል ሲሉ ምክትል ሃላፊው ይገልጻሉ። የአሮጌው መነኸሪያ አካባቢ ፕሮጀክት ብቻ እስከ 52 ሚሊየን ብር ድረስ ይፈልጋል። በመንግስት አቅም ብቻ ሊለማ አይችልም። እዚህ አካባቢ/ አሮጌው መነኸሪያ አካባቢ/ አንድን ቦታ በመንግስት በጀት አልምተን ካሳየን በኋላ ሌላውን ዲዛይን ሰጥተን በባለሀብቱ እንዲለማ ለማድረግ አንደ ከተማ ታስቧል ሲሉ ይጠቁማሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ለእግረኛ መንገድ ግንባታው የሚያስፈልጉ ታይሎቹን ተቋራጩ ራሱ እዚሁ እንዲያመርት ተደርጓል፤ ስታንዳርድ ወጥቶለት የጥራት ደረጃው እየተረጋገጠ የሚሰረም ነው፤ ማህበራት ደግሞ የማንጠፉን ስራ እንዲሰሩ ነው የተደረገው። በፕሮጀክቱ ብዙ ወጣቶች ከላይ እስከታች የስራ እድል አግኝተዋል።

ግንባታው ብዙ ነገሮችን ይይዛል። በእግር ተጓዦች /ዎክ የሚያደርጉ/፣ እናቶች አረጋውያን፣ ወዘተ. ይኖራሉ፡ ግንባታዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መቀመጫዎች ይኖራቸዋል፤ ሰው ቁጭ ብሎ መዝናናት እንዲያስችሉ ተደርገው ነው የሚገነቡት። ሳር፣ ዛፎች፣ ብዙ አይነት አበባዎችም ይተከላሉ፤ የእግረኛ መንገዱ የራሱ መብራት ይኖረዋል።

ሁሉም የከተማዋ አካባቢ በዚህ መልኩ ይገነባል፤ ስለዚህ እዚህ ጀመርን እንጂ እየተስፋፋ ይሄዳል፤ ገና ፒያሳ አልሄድንም፤ አጸዳን እንጂ ስራ አልጀመርንም። ስለዚህ እዚህ ሰርተን ካሳየን በኋላ ባለሀብቱ ራሱ እንዲያለማ ለማድረግ ዝግጅት እያደረግን ነው። ሁሉም መንገዶቻችንን እንደዚህ ማልማት ከቻልን የጎብኚዎች ፍሰት ይጨምራል፤ ዜጎች በነጻነት ለአደጋ በማያጋልጥ መልኩ ዎክ እያረጉ መንቀሳቀስ ይችላሉ።

የመኪና የሞተር ሳይክል ማቆሚያ ስፍራ ይኖረዋል፤ ዘመናዊ ሼዶች ይሰራሉ፤ ይህ አካባቢ የንግድ አካባቢ ስለሆነ ለብስክሊት የሚሆን መንገድ አልተዘጋጀለትም፤ ለሎች አካባቢዎች ላይ ለብስክሌት መንቀሳቀሻና ማቆሚያ ይዘጋጃል። ስለዚህ ብዙ ነገሮችን የያዘ ፕሮጀክት ነው፤ የከተማዋንም ገጽታ ይቀይራል ፤ በቀጣይ አመት ስትመጡ እናንተም ዎክ እያረጋችሁ ትዝናናላችሁ የሚል ተስፋ አለኝ ሲሉም ለእኛ መልእክት አስተላለፉ።

አካባቢው በእርግጥም በተለያዩ መንገዶች ተከልሎ ለተለያዩ አገልግሎቶች ውሎ የነበረው ይዞታ ጸድቷል፤ ምንም አይነት ሼድ የለም፤ የሚታየው መንገዱ ለእግረኛ በሚመቹ ውብ ሸክላዎች እየተነጠፉ ናቸው፤ ዛፎች በተለየ መልኩ በዙሪያቸው ግንባታ እየተካሄደ ነው፤ ለመንገደኞች ማረፊያና ለአበባ ማልሚያ እየተዘጋጁ ናቸው፤ በመብራት ማሸብረቅ አንዲቻልም የመብራት መሰረተ ልማቶች አብረው እየተዘረጉ ናቸው። አበቦች ተተክለዋል።

ከታቦር ብቻ 25 ሺ ካሬ ሜትር ነው ያስመለስነው የሚሉት ምክትል ሃላፊው፣ ከሌምቦ ጀምሮ እስከ ሪፈራል ሰርክል ድረስ ብቻ 22ሜትር ስፋት ያለው ሙሉ በሙሉ በግለሰቦች የተያዘ መሬት እንዲጸዳ ተደርጓል፤ 22 ሜትር ስል ስፋቱን ነው። ስለዚህ እጅግ የሚየስደምም ስራ በዚህ አመት ተሰርቷል ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ከሳውዝ ስፐሪንግ ወደ ውስጥ ስትገቡ በግለሰቦች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተቋማት ሙሉ ለሙሉ ክፍት ስፍራዎቹ ፣ የእግረኛ መንገዶቹ በአረንጓዴ አንዲለሙ ተደርገዋል። ሀዋሳ ወደ ውስጥም ሲገባ ልማቱ ይህንኑ የሚመስለው። መንገዶች በአስፋልት በኮብል ስቶን ህብረተሰቡ ደግሞ ፊትለፊቱን በማልማት ሰፊ ተሳትፎ አድርጓል።

ጉብኝታችንን ቀጥለናል፤ የማዳረስ አይነት ጉብኝት ነው። ወደ ሌላው አረንጓዴ ስፍራዎች ልማት ተንቀሳቀስን። ወደ ፍቅር ሀይቅ ከሚወስደውና ከመዳህኒአለም ቤተክርስቲያን አካባቢ ከሚገኘው አደባባይ ወደ አሞራ ገደል በሚወስደው ውብ የአስፋልት መንገድ ጥቂት ተጉዘን ቆመን። ልክ እንደ ተሰባሰብን የከተማው ማዘጋጃ ቤት ምክትል ሃላፊ አቶ ታሪኩ ማብራራታቸውን ቀጠሉ።

ይሄ የምትመለከቱት ደግሞ በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰራ ሲሉ ገለጹልን። የመንገዱ ዳርቻ በሳር እና በአበቦች ተውቧል፤ ለስፓርት መስሪያ የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶች ፣ የልጆች መጫዎቻዎችም አብረው ተገንብተዋል። እግረኞች ቢደክማቸው የሚያርፉባቸው መቀመጫዎች ተዘጋጅተዋል። ጧዋትና ከሰአት በኋላ ወደ አካባቢው የሚመጣ ህብረተሰቡ ሲዝናና ስፓርት ሲሰራ ታያላችሁ አሉን።

እንደ አቶ ታሪኩ ገለጻ፤ ለእዚህ ክፍት ቦታ ግንባታ የከተማና ኮንስትራክሽን መመሪያው የዲዛይንና አንዳንድ ድጋፎችን ከማውጣቱ በቀር ያወጣው ገንዘብ የለም። ሙሉ ወጪው በማህበረሰቡ ነው የተሸፈነው። ይህን ስራ በመንግስት በጀት ማኔጅ ማድረግ ያስቸግራል፤ በከተማ ደረጃ ብቻ ወደ 152 ሎቶች አሉ። አንድ ሎት በትንሹ 500 ካሬ ሜትር ስፋት ይኖረዋል፤ በትልቁ ሲታይ ደግሞ ከ800 እስከ 1000 ካሬ ሜትር ስፋት ይይዛል። 152 ሎቶቹን 152 ማህበራት ናቸው ማኔጅ የሚያደርጉት፤ አንድ ሎት በአንድ ማህበር ማኔጅ ይደረጋል።

ስራው ለወጣቶችም ሰፊ የስራ እድል የፈጠረ ነው። በአንዱ ማህበር አምስት ወጣቶች ይታቀፋሉ። ስለዚህ ስራው ምን ያህል ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚችል መረዳት ይቻላል።

ከህብረተሰቡ ጋር ተቀናጅተን ስንሰራ፣ ለስራው ደግሞ እውቅና ስንሰጥ ይበልጥ እየተበረታታን ክፍት ቦታዎችን ማልማት ይቻላል ሲሉም ነው ምክትል ሃላፊው የተናገሩት።

ቅድም እንደጠቀስኩት 21ሺ ካሬ ሜትር ቦታዎች ተሰሩ ያልኩት እንዲህ አይነት ስራዎች ተደምረው ነው። ይህን ወደ ገንዘብ ስንቀይር 106 ሚሊየን ብር የሚያወጡ ስራዎች ናቸው የተነከናወኑት። የመንግስትን በጀት በእዚህ ስራ መሸፈን ተችሏል ሲሉ አብራሩልን።

ባስጎበኘናችሁ ስፍራዎች ብቻ አይደለም ልማቱ የተከናወነው፤ በከተማው የተለያዩ አካባቢዎች ተመሳሳይ ስራዎች በርካታ ናቸው ይላሉ። ሌሎች አካባቢዎች ብትሄዱ ተቋማት ያለሟቸውን አረንጓዴ ስፍራዎች ማየት ትችላላችሁ፤ ሞቢል አካባቢ ቢጂአይ ያለማው አለ፤ ሌሎች የግል ተቋማት ያለሟቸው ክፍት ቦታዎች የሚገራርሙ ስፍራዎች መሆን ችለዋል።

አቶ ታሪኩ በስራው ውጤታማ ለሆኑትም በቅርቡ ሽልማት እንደተበረከተላቸውም በተለይ ለጋዜጣው ሪፓርተር ሰሞኑን ተናግረዋል። በህብረተሰብ ተሳትፎ በተሰሩ በተለይ በአረንጓዴ ልማትና በ24ቱ አጀንዳዎች መነሻነት ሽልማቱ የተበረከተላቸው። በዚህም ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ከወጡ ክፍለ ከተሞች እንደኛው መኪና፣ ሁለተኛው ሞተር ሳይክል ሶስተኛው ኮምፒውተርና ፐሪንተር ተሸልመዋል። አንደኛ ብሎኮች፣ መንደሮች እና ቀበሌዎች ተሸልመዋል።

ሙሉ ለሙሉ አካባቢያቸውን አረንጓዴ ማድረግ የቻሉ፣ በሌሎች የህብረተሰብ ተሳትፎ አጀንዳዎችም የላቀ ውጤት በማምጣቸው መሸለማቸውን የጠቀሱት ምክትል ሃላፊው፣ የሽልማቱ ሌላው ፋይዳ እስከ አሁን የተከናወነው የአረንጓዴ ልማትና የህብረተሰብ ተሳትፎ ስራ በላቀ መልኩ አንዲቀጠል ለማድረግ ለእዚህም የውድድር መንፈስ ለመፍጠር ነው ይላሉ። ከሽልማቱም በኋላ በ2015 የሚሰሩ እቅዶች ቀርበው በየሩብ አመቱ አፈጻጸማቸው እየተገመገመ እውቅና ይሰጣል ሲሉ አቶ ታሪኩ ጠቁመዋል።



የሀዋሳ ከተማ የእግረኛ መንገዶችንና አረንጓዴ ስፍራዎችን በመንግስትና በህዝብ ተሳትፎ በማልማት ተጠምዳለች፤

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢሬቻ፡- የምስጋና ፤የሰላም፤የአንድነትና የይቅርታ በዓል!

የገዳ ስርዓት ካበረከታቸው ትሩፋቶች መካከል ኢሬቻ አንዱ ነው። ኢሬቻ የምስጋና ፤ የሰላም፤ የአንድነት፤ የይቅርታና የፍቅር በዓል ነው።

ኢሬቻ የምስጋና በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት ታላቅ በዓል ነው። የክረምቱን መውጣት ተከትሎ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል በፈጣሪና በፍጥረት መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያጠናክር የገዳ ሥርዓት ፍልስፍና አካል ሲሆን፤ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ ሀብት፤ የጋራ እሴትና የጋራ ቅርስም ነው።

ኢሬቻ የኦሮሞ ማኅበረሰብ የይቅርታና የመልካም ምኞት መግለጫ እሴት ነው። ኢሬቻ ትልቅ የወንድማማችነት መሰረት የሚጣልበት፣ የተጣሉ ይቅር የሚባባሉበት በዓል ነው። የተጣላ ታርቆ፣ ቂሙን ትቶ በነጻ ልቦና ፈጣሪ ንጹህ ወዳደረገው የውሃ አካል ይሄዳል። ኢሬቻ ቀልብ የሚነጻበት ቦታ ነው። ይህ ደግሞ ዓለም አሁን ላለችበት ነባራዊ ሁኔታ ፍጹም መድሃኒት ነው።

ኢትዮጵያ በብሄርና በኃይማኖት ሰበብ ልዩነት እየፈጠሩና እያሰፉ ሃገር ለማፍረስ በሚጥሩ እኩይ ኃይሎች የተነሳ እየተፈተነች ትገኛለች። ሰላሟን የማይፈልጉ ኃይሎች ቀዳዳዎችን እየፈለጉ ሊያፈርሷት እየሞከሩ ነው። ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን በዚህ ወቅት የኢሬቻ ታላቅ እሴቶች በተግባር በማዋል ጥላቻን አስወግደን ይቅርታን አስቀድመንና ፍቅርን አንግበን ኢትዮጵያን ከማማዋ ላይ ለመመለስ መጣር አለብን።

ኢሬቻ ከጨለማ ወደ ብርሃን የመውጫ ምልክት ነው። ድቅድቁ የሃምሌና የነሃሴ ጨለማ አልፎ የመስከረም ብርሃን በሚፈነጥቅበት ውብ ጊዜ የሚከበር። ይህ ደግሞ አሁን ሀገራችን ካለችበት ውቅት ጋር ይመሳሰላል። ኢትዮጵያ በርካታ የጭንቅ ጊዜያትን አሳልፋለች። አሸባሪው ትህነግ ከውጭ ጠላቶች ጋር በመሆን ከአንድም ሶስት ጊዜ በሕዝብ ላይ ጦርነት ከፍቷል። ብዙዎችን ገድሏል፤ አፈናቅሏል፤ ደፍሯል፤ የሃይማኖት ቦታዎችን አርክሷል፤ የሰው ልጅን አዋርዷል።

ከሸብር ቡድኖቹ ሸኔና አልሻባብ ጋር በመሆንም ኢትዮጵያን አኬልዳማ ለማድረግ በብርቱ ሰርቷል። ሆኖም ሀገር ወዳድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ የውጭ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎችን ሀገር የማፍረስ ሴራ በማክሸፍ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያም ከመፍረስ ስጋት ወደ ጠንካራ ብልጽግና ማምራት ጀምራለች። ልክ እንደኢሬቻ ሁሉ ጨለማው አልፎ በብርሃን እየተተካ ነው።

ኢሬቻ የሰላም በዓል ነው። በኢሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደኅንነት ፈጣሪውን ዋቃን ይለምናል። ሰላም ማውረድ ውዴታ ሳይሆን ግዴታ ነው። ቂምና በቀል፣ አለመግባባትና ጥላቻ ያለው ማንኛውም ግለሰብ ጥላቻውን ሳይሽር፣ እርቅ ሳያወርድ፣ የገደለ ሳይክስ፣ እጁ ንፁህ ያልሆነ ግለሰብ ወደ ኢሬቻ ክብረ በአል አይሄድም።

ኢሬቻ ከመድረሱ በፊት አባ ገዳዎች በየአካባቢያቸው፤ በየደረጃው ባለው መዋቅር ያሉትን ችግሮች ይፈታሉ። የተጣላውን ያስታርቃሉ፤ የበደለ እንዲክስ ያደርጋሉ። ይህም የሚሆነው ኢሬቻ ካለው እሴት መካከል ሠላምና እርቅ አንዱና ትልቁ ስለሆነ ነው። ስለዚህ የኢሬቻ ዕለት ሠላም ይታወጃል፤ ይወደሳል። በኢሬቻ በዓል ስለሠላም ይሰበካል። ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት፣ ከሰፊው ህዝብ፣ ከፈጣሪና ከፍጡር ጋር በሠላም አብሮ መኖር እንደሚገባ ይታወጃል።

ኦሮሞ በአባባሉ «Yoo namni walitti araarame, Waaqnis namaaf araarama» «ሰው ርስ በርሱ ከታረቀ እግዚአብሔርም ይታረቃል» የሚለው ለዚህ ነው።

ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት ሁኔታ የኢሬቻ ዕሴቶች ያስፈልጓታል። ከጦርነት ፤ከግጭት፤ ከአለመረጋጋትና መፈናቀል ተላቃ ሰላሟ የተረጋገጠባት፤ሰዎች በሰላም ወጥተው የሚገቡባት፤ አርሰው የሚበሉባት፤ ነግደው የሚያተርፉባት ምቹ መኖርያ እንድትሆን ሕዝብና መንግስት ቃል የሚገቡበት ዕለት ሊሆንም ይገባል። የኢሬቻም ትውፊት ይኸው ነውና።

ኢሬቻ የአንድነት በዓል ነው። ሴት ወንድ ሳይል፤ ሃብታም ከድሃ ሳይለይ ሁሉም በአንድነት ኢሬቻን ያከብራል። በኢሬቻ አንድነት እንጂ ልዩነት ቦታ የለውም። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ከመለያየት ይልቅ አንድነትን፤ ከመጠፋፋት መገነባባትን ፤ ከማፍረስ ይልቅ መገንባትን መርሆዎችን ከኢሬቻ በመማርና በመተግበር ኢትዮጵያን በጠንካራ መሰረቷ ላይ ማኖር ይገባል።

ኢሬቻ ማለት መስማማት፣ አንድነት፣ እርቅ ማለት ነው። ይህ ምሳሌነቱ ደግሞ አገራዊ ፋይዳውን በሚገባ ያሳየናል። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ተስማምቶና ተግባብቶ መኖር ነውና፤ ኢትዮጵያዊነት አብሮ መብላትና ተሰባስቦ መደሰትና በችግር ግዜ አንዱ ለአንዱ መድረስና መተጋገዝ ነው። ኢትዮጵያዊነት ይቅር ባይነት፤ በፍቅር መኖርም ነው። ያለው የሌለውን ደግሞ የሚያሻግርበት፤ ችግርን በአብሮነት ለመፍታት የሚረባረብበትም ነው። ስለዚህም ኢሬቻን ስናከብር የኢሬቻን ዕሴቶች በመላበስ ሊሆን ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት

### እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

**የገዳ ሥርዓት ባለቤት የሆንከው የተከበርከው የኦሮሞ ሕዝብ፤**

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ከክረምቱ ወደ ብርሃናማው መጸው ተሸጋገራችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች እንዲሁም ከትንሽ እስከ ትልቅ ጠላቶቻችን የደቀኑብንን አደጋ አሳልፎ ለመጸው ብርሃን ላበቃን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው። ኦሮሞ ከገዳ ሥርዓት በወረሰው ዕሴት ክረምት አልፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪውን ያመሰግናል።

የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ፣ እህልን አብቅለህ፣ ማሳውን አሳምረህ የመጸውን ንጋት ስላሳየህን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ይላል። ርጥብ ሣር ይዞም «መሬሆ» «መሬሆ» እያለ ወደ መልካ በማቅናት የኢሬቻ ሥርዓትን ይከውናል።

ኢሬቻ ክረምት አልፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪ የሚመሰገንበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበር ነው። በድጋሚ የኦሮሞ ሕዝብን፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብን እንኳን አደረሳችሁ ስል ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ኢሬቻ የሰላም መድረክ ነው።

ለኢሬቻ ወደ መልካ የሚሄዱ ርጥብ ሣር በእጃቸው ይዘው የኢሬቻ ሥርዓትን ከመከወናቸው በፊት ሦስት ጥያቄዎችን መመለስ አለባቸው። የገዳ አባቶች «በመካከላችሁ ሰላም አለ?» «ለፈጣሪስ ሰላማዊ ናችሁ?» «ከተፈጥሮስ ጋር ሰላም ናችሁ?» ብለው ይጠይቃሉ።

ወደ መልካ ለኢሬቻ የሄደው የበዓሉ አክባሪም መልካውን በርጥብ ሣር ከመንካቱ በፊት ሰላም ነው ብሎ ይመልሳል። ከዛም በርጥብ ሣሩ መልካውን ነክቶ «መሬሆ» «መሬሆ» በማለት ፈጣሪውን ያመሰግናል። ለዚህም ኢሬቻን የሚያውቅ ሰው ቂምና በቀልን ትቶ ሰላምን ይሰብካል። አንድነትና ሰላምን ትብብርና ወንድማማችነትን ያጠናክራል። ከፈጣሪ ላገኘው የከበረ ስጦታ ዕውቅና ይሰጣል። በተፈጥሮ ያለውን መስተጋብርና ትብብር እያደነቀ ለፈጣሪው ምስጋና ያቀርባል። ልምላሜን የፈጠረ አምላክ ከሰው ልጅ ምስጋና ያገኛል። የሰው ልጅ ፈጣሪ የሰጠውን ርጥብ ሣር ይዞ ተፈጥሮን ያደንቃል ፈጣሪን ያመሰግናል።

ኢሬቻን የሚያከብር ከራሱ፣ ከጎረቤቱ፣ ከውስጥና ከውጪ በአገሩ እና ሩቅ ላለው ሰው ሰላማዊ መሆን አለበት። ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ጥላቻን ትቶ ዕርቅ ማውረድ አለበት ከኢሬቻ ሲመለስም ቂምና ጥላቻን እንዲሁም ያለፈ ጉዳትን ከማስታወስ ራሱን መቆጠብ አለበት። ኢሬቻን ማክበር በጋራ ምስጋናን ማቅረብ ነው። የተፈጥሮ ሕግ እንዳይስተጓጎል ፈጣሪ በፍጡራን እንዳያዝን ፈጣሪን መለመን ነው። ስለዚህ ኢሬቻ ዕርቅ ነው። ሰላም ነው ፍቅርና አንድነት ነው። ይህ ደግሞ የገዳ ሥርዓት ባህልና ዕሴት ነው። ኢሬቻ የንጽሕና መድረክ ነው። ኢሬቻ በሐሳብ መንጻትን ይፈልጋል።

ቂም መያዝና ስም ማጥፋት ከኢሬቻ ዕሴቶች ተቃራኒ ናቸው። ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ይቅር ባይ የሆንከው ፈጣሪ በማለት እጁን ዘርግቶ አምላኩን ይለምናል ያመሰግናል።

በኢሬቻ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ይመሰገናል። ሐቅን ማዛባት እውነትን መደበቅ ነውር እንደሆነ ይሰበካል። የተፈጥሮና የፍጡራን ሕግ የሚታወቅበት ነው።

የመጸው ወቅት የፈጣሪ የእጅ ሥራ የሚደነቅበት ነው። ከጨለማ ምዕራፍ ወደ ብርሃን ከክረምት ወደ መጸው ከቡቃያ ወደ አዝመራ የምንሸጋገርበትም ነው። ይህን የፈጣሪ ሥራ የሆነውን የተፈጥሮ ኡደትን «መሬሆ» «መሬሆ» በማለት የሚደነቅበት የኢሬቻ በዓል የብርሃንና የምርቃት ቀን ነው። ኢሬቻ የወንድማማችነት/ እኅትማማችነትና የአንድነት ቀን ነው።

በገዳ ሥርዓት በጋራ ሠርቶ በጋራ መመገብ መተባበርና አብሮ መቆም ለሐቅ መታገልና በችግር ጊዜ መረዳዳት የገዳ ሥርዓት የቀደመ ባህል ነው። ኢሬቻ አንድነትና ወንድማማችነት/እኅትማማችነት የሚጠነክርበት ነው። ኅብረት የሚጠነክርበት የፍቅር የወዳጅነት በጋራ የመኖር ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ነው። ይህ ትልቅ ዕሴት የሰው ልጆችን ሁሉ እኩል ማየትና ማክበር በመቅረብ መረዳትን የሚያስተምር ነው። ስለዚህ የበዓሉ አክባሪ ይህን የኢሬቻ ሥርዓትን በማክበር ፈጣሪን ያመሰግናሉ።

ኢሬቻ በዘር፣ በጾታ እና በእድሜ በሃይማኖትና በየትኛውም መሥፈርት ሰውን አይከፋፍልም። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በአንድነት የሚያከብሩት በዓል የሆነው። ለዚህም ነው ከኢትዮጵያውያን አልፎም የውጭ አገር ቱሪስቶችን መሳብም የቻለው።

እኛ እንደ አገር እና ሕዝብ የባህልና ወግ ባለፀጎች ነን፤ የሃይማኖት መቻቻል እና አብሮ መኖርን የሚያጠናክሩ የባህል ሥርዓቶች አሉን። አንዳችን የአንዳችንን ጉድለት ከመፈለግ ይልቅ መደማመጥን ያበረታታል ቂምና ጥላቻን ከመዘመር ሰላምና እውነትን መውደድን ያጠናክራል። የዘፈቀደ እና የስንፍና ኑሮ የእኛ አይደለም።

ለሁሉም ነገር ሕግ አለን። በሥርዓትና ወግ ለመኖር እንገደዳለን፤ ጀግንነት እንጂ ክህደት እኛን አይገልጸንም። በታሪክ ውስጥ በአንድነት እንጂ በልዩነት ተከብረን ተፈርተንም ሆነ አሸንፈን አናውቅም። አንድ ሆነን ስንቆም በሁሉም ግንባር ድልን እንደምንጎናጸፍ አይተናል የትኛውንም የሚሸረብብንን ሤራ ማክሸፍ እንደምንችል በተጨባጭ አሳይተናል።

ያለፈው አራት ዓመት ልምዳችንም ይህንኑ ነው የሚገልጸው። ጠላቶቻችን ወድቀዋል ሲሉን ተነስተን፤ ፈርሰዋል ሲሉን ተገንብተን አይተውናል። አሁንም ብዙ ነፃነታችንን እና ሉዓላዊነታችንን የሚፈታተኑ አሉ፤ ከመንገዳችን ግን ሊያሰናክሉን አይችሉም። ሐቅ አለን፤ እውነት ላይ ቆመን እንታገላለን ፈጣሪም ከእኛ ጋር ነው። ለየትኛውም ምድራዊ ኃይል አንንበረከክም። ትልቁ ጠላታችን የሆነውን ድህነት ለማሸነፍ መሥራት ይገባናል።

የሥራ ባህላችንን በማሻሻል በሁሉም የልማት መስኮች ተሠማርተን ለማሸነፍ በቁጭት መትጋት አለብን። ችግርን የመቋቋም አቅማችን በንቃታችን ተደራጅተን አንድነታችንን ጠብቀንና በተጨባጭ ሥርተን ባሳየነው ልክ በችግር በፈተና ጊዜ ካሳለፍነው ልምዳችን ተምረናል።

እንደ ኢሬቻ ያሉ ታላላቅ ክብረ በዓላትን እንደ አንድነታችን ማጠናከሪያ መሣሪያ ይዘን በአጭርና በረዥም ጊዜ የያዝነውን የብልፅግና ጉዟችንን ለማደናቀፍ የተከፈተብንን ዘመቻዎች ሁሉ ጥሰን በማለፍ የያዝነውን ራእይ ለማሳካት በአንድነት እንድንሠራ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የዘንድሮ ኢሬቻ ወደ አዲስ ምዕራፍ የምንሸጋገርበት እና በድል ላይ ድል የምናስመዘግብበት እንዲሆንልን እመኛለሁ።

**ዓመቱ የስኬትና የድል ይሁንልን።**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**መስከረም 20፣ 2015 ዓ.ም**

# ማህደረ ጤና

# የአንጀት ካንሰር

በአንጀት ካንሰር የሞተችው የአርባ ዓመቷ ጎልማሳ ዴሚ ዴብራ ጄምስ በሽታውን ቀድሞ ለማወቅ ሁሉም ሰው ሰገራው ላይ ያሉ ለውጦችን ትኩረት እንዲሰጥ ስትመክር ቆይታለች።

## ታዲያ እንዴት የአንጀት ካንሰርን ልንለይ እንችላለን?

ከዚህ የጤና ችግር ጋር በተያያዘ ሦስት ነገሮችን ልብ ማለት ይኖርብናል።

- በሰገራ ላይ ደማቅ ቀይ ወይም ጠቆር ያለ ቀይ ደም መታየት
- በሰገራ ላይ ለውጥ መታየት - በተደጋጋሚ መፀዳጃ ቤት መጠቀም ወይም ተቅማጥ ወይም የሰገራ መድረቅ
- ከምግብ በኋላ ሆድ የሞላ ሲመስል በታችኛው የሆድ ክፍል ላይ ሕመም ወይም እብጠት መኖር

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ በአንጀት ካንሰር የተያዘ ሰው የሚከተሉት አይነት ሌሎች ምልክቶችም ሊኖሩት ይችላሉ።

የክብደት መቀነስ፣ መፀዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኋላ በደንብ ያልተፀዳዱ ያህል መሰማት፣ ከተለመደው በተለየ የሰውነት መድከምና የመዛል ስሜት ያጋጥማል።

እነዚህ ምልክቶች ታዩ ማለት ግን የአንጀት ካንሰር አለ ማለት ላይሆን ይችላል።

ነገር ግን እነዚህ ምልክቶች ለሦስት ሳምንታትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ከታዩ እንዲሁም የሚሰማን ነገር ትክክል ካልሆነ ሐኪም ማማከር ያስፈልጋል።

በዚህም ተገቢው ምርመራ በፍጥነት ተደርጎ ካንሰር ከሆነ እና በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ከተደረሰበት ለማከም ቀላል ይሆናል።

አንዳንድ ጊዜ የአንጀት ካንሰር ሰገራ በተገቢው መስመር እንዳይወገድ በማድረግ መዘጋትን ሊፈጥርና ይህም ከባድ የሆድ ቁርጠት፣ ድርቀት እና ህመምን ሊያስከትል ይችላል።

እንዲህ አይነት ችግር ሲያጋጥም ችላ ሳይሉ ወደ ሐኪም ዘንድ በመሄድ አስፈላጊውን ምርመራ ማድረግ ተገቢ ነው።

## የበሽታውን ምልክቶች እንዴት መለየት ይቻላል?

መፀዳጃ ቤት በሚጠቀሙ ጊዜ የሚወጣውን ሰገራ ይመልከቱ፣ የተለየ ነገር ሲያጋጥምዎት የሕክምና ባለሙያ ለማማከር ወደ ኋላ አይበሉ።

በተለይ ሰገራ ላይ የደም ምልክትና መፀዳጃ ቤት ሲጠቀሙ የመድማት ሁኔታ ካጋጠመ በቀላሉ መታለፍ የለበትም።

አንዳንድ ጊዜ በሰገራ መተላለፊያ አካል ላይ ባሉ የደም ስሮች እብጠት ሳቢያ ቀይ ደም ሊወጣ ይችላል፤ ነገር ግን ይህ በአንጀት ካንሰር ሳቢያ የተከሰተ ሊሆን ይችላል።

ጠቆር ያለ ደም ወይም ጥቁር ደም ሰገራ ላይ ከታየ ይህ የተከሰተው በአንጀት ወይም በጨጓራ ላይ ባጋጠመ የጤና ችግር ስለሚሆን አሳሳቢ ሊሆንም ይችላል።

ከዚህም በተጨማሪ ቀጠን ያለ ሰገራ መኖር ወይም ከወትሮው በተለየ ቶሎ ቶሎ መፀዳዳት ሊኖር ይችላል።

ወይም ደግሞ አንጀት ውስጥ የተከማቸው ሰገራ ያልወጣ መስሎ መሰማት አሊያም በበቂ ሁኔታ አለመፀዳዳት ያጋጥማል።

በዩናይትድ ኪንግደም ስለ አንጀት ካንሰር መረጃ የሚሰጠው ድረ ገጽ ወደ ሐኪም ዘንድ ከመሄድ በፊት በየዕለቱ የሚታዩ ምልክቶችን በመከታተል መመዝገብ እንደሚገባ ይመከራል። ይህንንም ለሐኪምዎ መናገር ያለብዎትን ሳይዘነጉ አንድ ባንድ መናገር እንዲችሉ ይረዳል።

ሐኪሞች በተለያዩ የአንጀት ጤና እክሎች ያሉባቸው በርካታ ሰዎችን ስለሚመለከቱ በእራሳችሁ ላይ ያያችሁትን ለውጥ ወይም መድማት ካለ መናገራችሁ የበሽታውን መንስዔ ማወቅ እንዲችሉ ያግዛል።



የአንጀት ካንሰር በትልቁ አንጀት ወይም በፊንጢጣ አካባቢ የሚከሰት ነው

## የአንጀት ካንሰር በዘር ይተላለፋል?

በአብዛኛው የአንጀት ካንሰር በዘር አይተላለፍም። ይሁን እንጂ የቅርብ የቤተሰብ አባል ከሃምሳ ዓመት ዕድሜ በፊት በበሽታው ተይዘው ሕክምና አድርገው የሚያውቁ ከሆነ፣ ይህንን ለሐኪም መናገር አስፈላጊ ነው።

እንደ ሊንቼ ሲንድረም ያሉ አንዳንድ በዘር የሚተላለፉ ካንሰሮች ለአንጀት ካንሰር የመጋለጥ እድል እንዲሰፋ ያደርጋል። ስለዚህ ሁኔታ ሐኪም ማወቅ ከቻለ በሽታውን ቀድሞ ለመከላከል ያስችላል።

## የመጋለጥ ዕድልን እንዴት መቀነስ ይቻላል?

የሚከሰቱት የአንጀት ካንሰሮች ግማሽ ያህሉ ጤናማ የሕይወት ዘይቤን በመከተል ቀድመን ልንከላከላቸው የምንችላቸው እንደሆኑ ተመራማሪዎች ይናገራሉ።

በቂ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ፣ በብዛት አሰር ያላቸውን ምግቦችን በመመገብ እና ስብን በመቀነስ እንዲሁም በቀን ውስጥ ከስድስት እስከ ስምንት ብርጭቆ ውሃ በመጠጣት የአንጀት ካንሰርን ቀድሞ መከላከል ይቻላል።

ነገር ግን የሚያሳስብ ምልክት ከተከሰተ የጤና ባለሙያን ማማከር እና የካንሰር ምርመራ ማድረግ ይመከራል።

የአንጀት ካንሰር በትልቁ አንጀት ወይም በፊንጢጣ አካባቢ የሚከሰት ነው

## የአንጀት ካንሰርን እንዴት መለየት ይቻላል?

የአንጀት ካንሰር ምልክቶች ከታዩ ፈጠን ብሎ ሐኪም ማማከር በሽታውን ለመቆጣጠር ወሳኝ ነው።

ምርመራውም ቱቦ በመጠቀም ሁሉንም የአንጀት ክፍሎች በካሜራ በሚያሳይ መሣሪያ (ኮሎኖስኮፒ) ይደረጋል።

ወይም ደግሞ የተወሰነውን ክፍል ለማየት በሚያስችል መሣሪያ (ሲግሞዶስኮፒ) በተባለ ተጣጣፊ መሣሪያ ምርመራው ይካሄዳል።

በመጀመሪያው የአንጀት ካንሰር ደረጃ ላይ ምርመራ ያደረጉ ሰዎች በሽታውን በቶሎ በመለየት አስፈላጊውን ሕክምና በወቅቱ ማግኘት ስለሚችሉ የሚከሰተውን ጉዳት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ይቻላል።

የካንሰር በሽታ በብዛት የሚከሰተውና ገዳይ የሚሆነው እድሜያቸው በገፉ ሰዎች ላይ በመሆኑ ልክ እንደ ሌሎች የካንሰር በሽታዎች ሁሉ በአንጀት ካንሰር የተያዙ ከ15 እስከ 40 ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች በሕይወት የመቆየታቸው ዕድል ሰፊ ነው።

ሆኖም አጠቃላይ በሕይወት የመቆየት እድል ከሌሎች የአውሮፓ አገራት ጋር ሲነጻጸር በዩኬ ያለው ጥሩ የሚባል አይደለም።

## የአንጀት ካንሰር ሕክምና ምንድን ነው?

የአንጀት ካንሰር በተለይ ቀድሞ ሕክምና ማድረግ ከተቻለ የሚድን በሽታ ነው።

በሽታውን ቀድሞ ለመከላከል ያለው ሕክምና በአብዛኛው በግል የሚከናወን ሲሆን፣ የዘረመል ምርመራ ቀድሞ ማድረግ የተከሰተውን ካንሰር ለማከም ያስችላል። ይህ ዘዴ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ተጨማሪ ዓመታትን በሕይወት እንዲቆዩ ይረዳል።

በየትኛውም የዕድሜ ክልል በበሽታው ለተያዘ ሰው ሕክምናው ይሰጣል።

ሕክምናው ቀዶ ሕክምና፣ ኬሞቴራፒ፣ ራዲዮቴራፒ ወይም ደግሞ እንደየግለሰቡ የካንሰር ሁኔታ ሌሎች ሕክምናዎች ሊሰጡ ይችላሉ።

## የካንሰር ደረጃዎች የትኞቹ ናቸው?

- ደረጃ አንድ ካንሰር፡ በመጠን ትንሽ እና ወደ ሌሎች የአካል ክፍል ያልተሰራጨ
- ደረጃ ሁለት ካንሰር ፡ በመጠን ትልቅ ግን ወደ ሌሎች የአካል ክፍሎች ያልተሰራጨ
- ደረጃ ሦስት ካንሰር፡ በአካባቢው ወዳሉ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች (ሊይምፍ ኖድስ ) የተሰራጨ
- ደረጃ አራት ካንሰር፡ ካንሰሩ ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች በመሰራጨት ሁለተኛ ዕጢ ይፈጥራል።

**ምንጭ ፡- ቢቢሲ**

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ሠርቶ የመለወጥ ፍላጎትና ትጋት ውጤት

ስምስም መንግሥቱ





ወጣት ዮናስ ጌቱ

በምልክት በተነገረን አቅጣጫ ከአስፓልቱ ወጥተን ኅርበጥባጣውን መንገድ ይዘን መድረሻችንን እየፈለግን ነው:: በቆርቆሮ አጥር በታጠሩ አንዳንድ ቤቶች ደጃፍ ያገለገሉ የታሸገ ውሃ ኮዳዎች ተከማችተዋል:: የኮዳዎቹ ምልክት አካባቢው ከመኖሪያ መንደርነት ይልቅ የሥራ አካባቢ እንደሆነ ይጠቁማል::

መዳረሻችንም እንዲህ ካሉ የፕላስቲክ የውሃ ኮዳዎችና ከፕላስቲክ ተረፈ ምርቶች የተለያዩ ምርቶች ከሚመረቱበት ድርጅት ስለነበር ቅኝታችንን እያረግን ከምንፈልገው ቦታ ደረስን::

ከቆርቆሮው አጥር ላይ አነስ ባለ ጽሁፍ የተጻፈውን የድርጅቱን ስም አልተለመከትነውም ነበርና ድርጅቱን አልፈነው ሄደናል፤ በኃላ ላይ ግን አጠያይቀን ተመልስን:: ለካስ አጥሩ ላይ የተለጠፈውን « ኖብል» የሚል ጽሁፍ አልተመለከትነውም ነበር:: የቆርቆሮውን አጥር በር ገፍተን ወደ ውስጥ ዘለቅን:: ወደ ውስጥ ስንገባ ያልጠበቅነውን ነገር ተመለከትን በአግራሞች አፋችንን ያዝን::

ለቤት፣ ለበረንዳና ለመንገድ ዳር ችግኝ መትከያ የሚሆኑ ምርቶች ፣ ሞተረኞች ከኃላ የሚያስገጥሙት ሳጥን፣ ተቋማት ድርጅታቸውን ለማስተዋወቅ የሚጠቀሙበት ሰሌዳ (ቢልቦርድ)፣ የመሳሰሉት ቅርጽ ሲወጣላቸው፣ የተጠናቀቁት በቀለም ሲዋቡ ተመለከትን:: በተለያየ ቀለማትና መጠን ውብ ሆነው ለገበያ ዝግጁ የተደረጉት ደግሞ በመደርደሪያ ላይ በአንድ ረድፍ ተደርገዋል:: ከምርቶቹ መደርደሪያ ላይ ተቋማት በአርማቸው ወይንም በምልክታቸው በትእዛዝ ያሰሯቸው የአበባ መትከያዎችንም ተመልክትን፤ በኖብል ድርጅት ግቢ ውስጥ::

ምርቶቹ የእጅ ጥበብ ሥራ ውጤት መሆናቸው ደግሞ ይበልጥ አስደነቀን:: ምርትና ማርታማነትን ለመጨመርና ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል ዘመናዊ መሳሪያዎችን መጠቀም የሚመረጥ ቢሆንም፣ የእጅ ጥበብ ውጤቶች በደንበኞች በእጅጉ ተፈላጊ መሆናቸው ይታወቃል:: የእጅ ጥበብ ውጤቶች በዋጋም ውድ እንደሆኑ ይነገራል::

ለነገሩ ኢትዮጵያውያን የሚታወቁት በእጅ ጥበብ ሥራቸውም አይደል:: ለእዚህም የሸክላ ውጤት የሸመና ሥራው ይጠቀሳል:: የእጅ ጥበብ ስራ ትእግሥትን ይጠይቃል:: ወጣት ካለው የትኩስነት ባህሪ ጋር ተያይዞ እንዲህ ባለው ሥራ ላይ ተሰማርቶ ለውጤት ይበቃል ተብሎ ላይጠበቅ ይችላል::

እኛ ያየነው ግን በተቃራኒ ነው:: ሰራተኞቹም አሰሪዎቹም በሥራ ያልደከሙ ትኩስ ኃይሎች ናቸው:: ሥራውን ለመሥራት ፍላጎት ብቻ ነው የሚያስፈልገው ክህሎቱን እርስበርስ በመማማር ያዳበሩት መሆናቸውን ሥራቸውንና አሰራራቸውን ተዘዋውረን ባየንበት ወቅት አረጋግጠናል:: በሙያው ላይ የሚገኙት ወጣቶች በተለያየ የትምህርት ደረጃና ኑሮ ላይ የነበሩ ናቸው::

ስራው በተለያየ አጋጣሚ በተዋወቁ ሶስት ወጣቶች ነው የተጀመረው፤ ከብዙ ውጣ ውረድና ልፋት በኃላ ነው ሰርቶ የመለወጥ ፍላጎት ያላቸውን ወጣት ሠራተኞች በማሳተፍ ጥሩ መስመር በመያዝ ላይ የሚገኘውን ኖብል ድርጅት በሁለት እግሩ ማቆም የተቻለው::

ሥራው በሶስት ወጣቶች ቢጀመርም፣ ሀሳብ ከማፍለቅ ጀምሮ ድርጅቱን ለስኬት ለማብቃት በኃላፊነት እየተጋ ያለውና በኢንቨስትመንት ደረጃ ለማሳደግ እንደ ታላቅ ወንድምም እንደመሪም አጥፊውን እየገሰፀ፣ እየተቆጣ፣ በወጣትነት ከሚስተዋለው ችኩልነት ሰከን ብለው፣የነገን ጣፋጭ ፍሬ ለመብላት ሩቅ አልመው እንዲሰሩ በማድረግ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ወጣት ዮናስ ጌቱ ይባላል::

ሁለቱ የሥራ አጋሮቹ ወጣት ዮናስ መረጃውን እንዲሰጠን መርጠውታልና ቆይታችን ከወጣት ዮናስ ጋር ሆነ:: ወጣት ዮናስ የተወለደውና እድገቱ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል ጌዲኦ ዞን ዲላ ከተማ ሲሆን፣ ለወላጆቹ ሁለተኛ ልጅ ነው:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እስኪያጠናቅቅ ብቻ ነው በዲላ የኖረው::

በሸቀጣሸቀጥ ንግድ ሥራ የሚተዳደሩት ቤተሰቦቹ ኑሯቸውን በአዲስ አበባ ከተማ በማድረጋቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአዲስ አበባ ከተማ ፀሐይጮራ ተብሎ በሚጠራው ትምህርትቤት ነው የተከታተለው:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኃላ በአንድ የግል ትምህርትቤት ኮምፒውተር ሳይንስ ተምሮ 2002ዓምበዲፕሎማ ተመርቋል::

ወጣቱ በተማረበት የትምህርት መስክም ሆነ የተገኘውን ሥራ ለመሥራት የተለያየ ጥረት ቢያደርግም የልቡ አልሞላለትም:: ቤተሰቡ ይተዳደርበት በነበረው የንግድ ሥራ መስመር ውስጥ ለመግባት መንገዱ ቀላል ቢሆንም፣ በፈጠራ ሥራ የራሱን ሥራ መሥራት ፍላጎት ነበረው::

ያን ወቅት በአሁኑ እድሜው ላይ ሆኖ ሲያስበው ፈጠራን በታዳጊነት እድሜው ነው ያዳበረው:: ታዳጊ ሆኖ ቤት ውስጥ የተበላሹ የቁም ሳጥንና የተለያዩ ሳጥኖችን መጠገን፣እየፈቱ ማሰር፣ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን መሞከር ከሚያደርጋቸው ጥረቶች መካከል ይጠቀሳሉ:: ጥረቶቹም ይሳኩለት ስለነበር ቤተሰቦቹ ለሚያጋጥሙ አንዳንድ ብልሽቶች ለባለሙያ የሚያወጡትን አስቀርቶላቸው እንደነበር ያስታውሳል::

ጉርምስናው ሲመጣ ደግሞ አንዳንዶች በውጭ ሀገር የተሻለ ኑሮ ይገኛል ብለው እንደሚያስቡት እርሱም ወደ ውጭ መሰደድን ተመኘ:: በአሜሪካ የሚኖሩ ዘመዶቹ ግፊት ደግሞ የበለጠ ለስደት እንዲነሳሳ አደረገው:: በኬንያ በኩል አድርጎ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ኬኒያ ሄደ:: በዚያም ከሁለት ወራት በላይ አልቆየም::

የስደትን አስከፊነት በአጭር ጊዜ ውስጥ በማየቱና ገና ‹ላም አለኝ በሰማይ› እንደሚባለው አይነት የአሜሪካ ጉዞው መቼ እንደሚሳካ እርግጠኛ ባልሆነበት፣ ሌሎች አምስትና አስርት አመታት በስደት እንደቆዩት በኬኒያ ሆኖ መጠበቁን ጊዜ ማባከን እንደሆነ ተገንዝቦ ወደ ሀገሩ ተመለሰ::

መለወጥና በኢኮኖሚ ማደግ ሀገር በመቀያየር ሳይሆን፣ሰርቶ በመለወጥ መሆኑን ማመኑ እንደጠቀመው የሚናገረው ወጣት ዮናስ፣ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኃላ በታዳጊነት እድሜው ይሞካከራቸው የነበሩ የጥገናና የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ማጠናከር ፈለገ:: ለእዚህም አጫጭር ስልጠናዎችን ወሰደ::

የኤሌክትሪክ የሙያ ክህሎቱን በማጎልበት ከኤሌክትሪክ ሥራ ጋር የተያያዘ ሥራ ለመሥራት የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ አነስተኛ ድርጅት ከፈተ:: ሙያው ከግንባታ ዘርፍ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በዘርፉ ላይ ከሚገኙ አንዳንድ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋር በመሆን በሙያው መሥራት ጀመረ:: በኤሌክትሪክ ሥራ አጋጣሚም ከግንባታው ጋር የተያያዙ ሌሎች ሙያዎችን ለመቅሰም ዕድሉን ከማግኘቱ በተጨማሪ ሥራም እየሰራ ገቢ እያገኘ ኑሮውን መምራት ቻለ:: ይህ ስራው ከፍተኛ የገንዘብ ትርፍ ባያገኝበትም፣ የተለያየ ሙያ የማወቅ እድል ከፍቶለታል::

ለአሁኑ ሥራው መነሻዎቹ በዚህ በግንባታው ዘርፍ ላይ የቆየባቸው ጥቂት ጊዜያቶች ናቸው:: በተለይ ደግሞ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ በተነሳሽነት የጀመሩት አረንጓዴ አሻራና ፓርኮችን የማስዋብ ሥራ ሀገራዊ ንቅናቄ እንዲፈጠር በማድረጉ የአበባ መትከያዎችን ሰርቶ ለገበያ ማቅረብ አዋጭ እንደሆነ በአእምሮው የመጣለትን ሀሳብ ሳይውል ሳያደር ወደ ተግባር ለማዋል ወሰነ::

ሀሳቡንም በተለያየ አጋጣሚ ለተዋወቃቸው ሴትና ወንድ ጓደኞቹ አጋራቸው:: ሶስቱም በአንድ ላይ ሆነው ለመሥራት ሲወስኑም፣ ለሥራ መነሻ የሚሆናቸው ብድርና የመሥሪያ ቦታ የሚያገኙበትን መንገድ በመምከር ነው ወደ ሥራ የገቡት::

በኦሮሚያ ክልል የሰበታ ከተማ አስተዳደር የሥራ ቦታ በመስጠት ያደረገላቸው ድጋፍ ለሀሳባቸው እውን መሆን ትልቅ እገዛ አደረገላቸው:: ለሥራ መነሻ የሚሆን ብድርም ዋልኮ ከሚባል ድርጅት አገኙ:: ቦታውንም እንደ ተረከቡ ጊዜ ሳያጠፉ በጋራ ሆነው አንድም ሁለትም የአበባ መትከያ ሰርተው ለገበያ ማቅረብ ጀመሩ::

መጀመሪያ የተሰራው የአበባ መትከያ በመጠን አነስተኛ ነው፤ በቀጣይም ለአበባ መትከያ የሚሆን ግብአት ለመግዛት አንድ ሺ ብር ወጭ አድርጉ:: የአበባ መተኪያ አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር ተሸጦ ስምንት መቶ ብር ትርፍ አስገኘላቸው:: በዚህም ተደሰቱ፤ የተፈጠረው የደስታ ስሜትም በቃላት የሚገለጽ አልነበረም:: ሁኔታው በተለይ የመጀመሪያዋን የአበባ መትከያ ለብቻው ለሰራው ወጣት ዮናስ የተለየ ደስታ የፈጠረ ነበር:: ሀሳቡን ከማፍለቅ ጀምሮ ለውጤት በማድረስ ያደረገውን ጥረትና ውጣ ውረድ የሚያውቀው እርሱ ብቻ በመሆኑ ነው ከሌሎቹ ስሜቱ የተለየው::

መቸም ደስታ ነው:: ጋብዙኝ የሚል ጓደኛም ስለማይጠፋ መጀመሪያ የተገኘውን ገንዘብ ለዚህ ተግባር አውላችሁት ይሆን ስል ወጣቱን ጠየቅሁት:: «በፍጹም» የሚል ነበር ምላሹ:: እድገት የሚመጣው አንድ ተብሎ በመሆኑ አስፈላጊ ከሆኑ ወጭዎች ውጭ ለግል እንዳላዋሉት ነው አጫወተን::

የሥራ መነሻው ዓላማ መለወጥና ማደግ ነው፤ የግል ፍላጎት ይደርሳል የሚል የጋራ አቋም እሱና አጋሮቹ እንዳላቸው ወጣት ዮናስ ያስረዳል:: እዚህ ላይ ስለእርሱ ጠንካራ መሪነትም ወጣቱ ይናገራል::

እነ ወጣት ዮናስ ምርታቸውን በመጨመር ገበያውንም በማስፋት በተለይም ትእዛዞችን ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭም በመቀበል፣ የፈጠራ ክህሎታቸውንም በማሳደግ የተለያዩ ምርቶችን በመጨመር፣ የራሳቸውን ዲዛይን (ንድፍ) ይዘው የሚመጡ ደንበኞችንም ሀሳብ መሠረት አድርገው ሥራቸውን አሰፉ::

በየጊዜው ለውጦችን ማምጣት እንደቻሉና ተቋማትና ግለሰብ ደንበኞችን ማፍራት መቻላቸውን የገለጸው ወጣት ዮናስ፣ የመጀመሪያ የሥራ ውጤታቸውን ከመቀበል ጀምሮ እስካሁን በደንበኝነት አብሮአቸው የዘለቀውን የተለያዩ የማስዋቢያና የዛፍ ችግኞችን በመሸጥ የሚተዳደረውን ወጣት ጅላሎ መኩሪያን ውለታም አልዘነጋውም::

ገበያ ላይ ተፈላጊ ሆኖ የደንበኖች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ አጋዥ ሠራተኞችን በቅጥር ማሰራት የግድ ነበርና የተወሰኑ ሠራተኞችን ቀጠሩ:: ሥራቸው እያደገ መጥቶ ከ60 በላይ ሠራተኞችን መያዝ ቻለ:: በረዳትነት ሥራ የጀመሩ አንዳንድ ሠራተኞችም የሙያ ክህሎታቸውን ማሳደግ (ፕሮፌሽናል መሆን) ችለዋል::

የመሥሪያ ቦታቸውንም በአጥር በመከለልና ምቹ ለማድረግ ጥረት ማድረጋቸው አንዱ ማሳያ ከቢሮ አደረጃጀት ጀምሮ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል ምቹ መደረጉ ነው:: ለቢሮ ያዋሏቸው መቀመጫዎችም በድርጅታቸው የተሰሩ ናቸው:: ምርቶቹ ወደ ገበያ ቢወጡም አዋጭ እንደሆኑም እኛም ተቀምጠንባቸው አይተናቸዋል::

የእነርሱን ፈለግ የተከተሉ ሌሎች ደርጅቶችን መፍጠር እንደቻሉም ወጣት ዮናስ ይጠቅሳል:: በድርጅታቸው ምርት ለውጭ ገበያም ሊቀርብ የሚችል እንደሆነ በእርግጠኝነት ይናገራል:: እነ ወጣት ዮናስ ከውጭ ከሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር በማወዳደር ራሳቸውን በመፈተሽ ነው በሥራ ውጤታቸው መተማመንን የፈጠሩት:: ምርቱን በሀገር ውስጥ የመተካት አቅም እንደተፈጠረም ይገልጻል::

ደንበኞች በዋጋ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት በሀገር ውስጥ ተመርቶ ሲቀርብ እንደሆነም ያስረዳል:: እርሱ እንዳለው፤ ምርቶቻቸው ከ700 ብር እስከ 15ሺ ብር የሚያወጡ ናቸው::

ድርጅታቸውን አሁን ከሚገኝበት መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ከሚባለው ደረጃ ወደ ከፍተኛ መሸጋገር የእርሱና የአጋሮቹ ፍላጎት ነው:: ድርጅታቸው የሚቀበለውን ትእዛዝ ሌት ከቀን ሰርቶ በጊዜው የማድረስና በመደበኛ የማምረት ጊዜውም በመጠቀም አቅም ከመፍጠሩ በተጨማሪ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭም የምርት ማስተዋወቂያ በመክፈት የሚያደርገው ጥረት ለኢንቨስትመንት የሚያበቃው መሆኑን ነው ወጣት ዮናስ የሚናገረው:: መንግሥት ወደ እድገት የሚያሸጋግራቸውን ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥርላቸው ይፈልጋል::

ወጣት ዮናስ እንደማነቀ ያነሳው የጥሬ ዕቃ ግብአት አቅርቦት ዋጋ ውድ መሆንን ነው:: እነሱ ከአስመጪዎች በመግዛት ነው የሚያመርቱት:: ለምርቱ ወደ አምስት አይነት የሚሆኑ ግብአቶች ያስፈልጋሉ:: ቀጥታ ግብአቱን ማስገባት የሚችሉበት መንገድ በመንግሥት ቢመቻች ትርፋማነታቸው እንደሚጨምርም ይገልጻል:: ይህ ሲሆን ተጠቃሚውም ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማግኘት ያስችለዋል ይላል::

በሌላ በኩል እነ ወጣት ዮናስ በአንዳንድ አዲስ ጀማሪ ድርጅቶች ሰራተኞችን በማስኮብለልና በተለያየ መንገድ ገበያቸውን ለመጣል የሚደረገው ጥረት የሚያሳዝን ሆኖ ቢያገኙትም፣ የበለጠ እንዲተጉ እንዳደረጋቸው ያስረዳል:: በዚህ «ተስፋ ልቆርጥ አልችልም:: ወደፊትም ተስፋ አልቆርጥም:: ተጋፍጬ ለማደግ ነው ጥረት የማደርገው» ይላል:: የሥራ አጋሮቼ አቋምም ይሄው መሆኑን ይገልጻል::

በአንዳንድ ሀገራት ባለሀብቶች እንደነርሱ ያሉ ጀማሪ አምራቾችን ምርት በመቀበልና ገበያ እንዲያገኙ በማድረግ ያበረታቷቸዋል ያለው ወጣት ዮናስ፣ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶችም እንዲህ ያለውን ተሞክሮ እንዲጋሩ ሀሳብ አቅርቧል::

ኖብል ድርጅት የመጀመሪያ ምርቱን ከመግዛት ጀምሮ እስካሁን በደንበኝነቱ አብሯቸው የዘለቀው የማስዋቢያና የዛፍ ችግኞችን በመሸጥ የሚተዳደረው ወጣት ጅላሎ መኩሪያ፣ የአበባ መትከያ አቅራቢ ደንበኞች አሉት፤ የኖብልን ምርት መግዛት ከጀመረ ወዲህ ደንበኝነቱን ከኖብሎች ጋር አጠናክሯል:: ምርቱ በደንበኞቹ ተፈላጊ ሆኖ ስላገኘውም ደንበኝነቱን አጠናክሮ የቀጠለው::

ደንበኝነቱ የወጣቶቹን ጥረት በተለይም የዮናስን ትጋት የማየት ዕድል እንዲያገኝ እንዳረገው ገልጾ፣ የዮናስን ትጋት እንደሚያደንቀውም ነው የተናገረው:: « እነ ዮናስ በየጊዜውም በፈጠራና ሥራቸውን በማሻሻል እያደጉ የመጡ ናቸው:: የገበያ ውድድርንም አሸንፈው ነው የወጡት:: የሥራ ዕድል በመፍጠርም ቢሆን ብዙ ሚና ተወጥተዋል» ሲል ገልጾ፣ ገበያው እነርሱ ጋ ብቻ እንደማይቆምም እየሰፋ እንደሚሄድም ነው የጠቆመው::

ወጣት ጅላሎ በአልባሌ ቦታ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ ወጣቶች ከእነርሱ እንዲማሩም ምክሩን ሰጥቷል:: አንድ ውጤት ላይ ለመድረስ ጥረትና ተስፋ አለመቁረጥ እንደሚያስፈልግም ከኖብል አሰሪዎችና ሠራተኞች ተሞክሮ ማግኘኑንም ተናግሯል::


ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተሳምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## በዕድሜ ማምሻ - ኑሮን ታግሎ መጣል

መልካም ሥራ አፈወርቅ



ብርቱ ናቸው ጠንካራ ። በስራ የተገነባ አካላቸው ዛሬም ቢሆን ድካም የለውም። የፊታቸው ገጽታ እርጅና የበገረው አይመስልም። በፈገግታ እንደተሞላ ያለፈውን ውጣውረድ ይመሰክራል ። የአንደበታቸው ቃል ተደምጦ አይጠገብም፣ ተጫዋች ናቸው። አጠገቤ ደርሰው ሰላምታ እንደሰጡኝ ንግግራቸውን በተለየ ምርቃት ጀመሩ።

‹‹አሜን›› እያልኩ በረከታቸውን ተቀበልኩ። ምርቃታቸው ልብ ያሞቃል፣ አቀራረባቸው ያስገርማል። ከዚሁ አድናቆት ሳልወጣ ፣ ስማቸውን ጠየኩ። ቀልጠፍ ብለው ወይዘሮ በለጠች ደበላ እንደሚባሉ ነገሩኝ። በልቤ እውነትም ‹‹በለጠች›› አልኩ ። ኑሮን ታግለው ችግርን በልጠው ማሸነፋቸው እየታየኝ።

ከወይዘሮ በለጠች ጋር ጭውውታችን ጀምሯል። በለጠች ሶዶ ጉራጌ ‹‹አማውቴ›› ከተባለ ስፍራ ነው የተወለዱት። ትውልዳቸው በዚህች ቀበሌ ይሁን እንጂ ዕድገታቸው ‹‹ገሬኖ›› ከሚባል አካባቢ ስለመሆኑ ይናገራሉ። ወላጅ አባታቸውን አያውቁም። እሳቸው እንደተወለዱ መሞታቸውን ሰምተዋል። እናታቸው ባላቸውን በሞት እንዳጡ ለሌላ ባል ተዳሩ። በአካባቢው ባሏ የሞተባት ሴት ብዙ አትቀመጥም፣ እጇን የሚፈልግ ሙያዋን የሚሻ አጠያይቆ ይወስዳታል።

እናት ባል ሲያገቡ በለጡ ለአንዲት አክስታቸው በማደጎ ተሰጡ። አክስት ትንሽዬዋን ልጅ በደስታ ተቀብለው መንከበካብ ያዙ። በቅንጦት ያደጉት በለጡ አንዳች ሳይጎድልባቸውን ልጅነታቸውን በአክስታቸው ዕልፍኝ አሳለፉ።

ዕድሜያቸው ከፍ እንዳለ እንደማንኛወም የአካቢው ሰው እጃቸው በስራ ሊፈተን ፣ ጉልበታቸው በጥንካሬ ሊበረታ ግድ ሆነ ። ለቁፋሮው፣ ለእንሰት ቆረጣው ፣ ለእንጨት ፈለጣው የሚያህላቸው አልተገኘም ። አቅማቸውን ሳይሸሽጉ በታዥነት ከሁሉም ተገኙ ። ወጣትነታቸው ሲያበብ፣ኮረዳነታቸው ከዓይን ሲገባ ደግሞ ትዳር የሚሹ ዓይኖች አረፉባቸው። በወግ ማዕረግ ተድረው ያደጉበትን ቤት በክብር ተሰናቱ ፣ ከደጓ አክስታቸው ጉያም ተለዩ።

በለጡ ትዳር ከያዙ በኋላ ኑሮን ለማሸነፍ ብዙ ታግለዋል። ካቲካላ አውጥተው ጠርሙሱን በሀምሳ ሳንቲም ፣ ጥሩ ጠላ ጠምቀው፤ ጣሳውን በአስር ሳንቲም ሸጠዋል። ባለቤታቸው አብረዋቸው ጥቂት እንደቆዩ አዲስ አበባ በመሄዳቸው ራሳቸውን ለመርዳት የወሰዱት አማራጭ ነበር።

በእነሱ ዘመን ሴት ልጅ ከአማቷ እንጂ ከአባቷ ሀብት አንዳች የመውረስ መብት አልነበራትም። ትዳር ይዛ ወደ ባሏ ስትሄድ ባዶ እጇን እንድትገባ ትገደዳለች። በለጡ ትዳር ይዘው ጎጆን ባቀኑበት ዓመታት ከባለቤታቸው ጋር በእኩል ለፍተዋል። ጥቂት ቆይተው አማቻቸው ባረፉ ጊዜ ባለቤታቸውና እሳቸው ከቤተሰቡ ሀብት ንብረት የመውረስ መብቱ እንደነበራቸው ያውቃሉ ።

ባል ግን በመብታቸው አልተጠቀሙም። ሀብቱን ሌሎች ሲጠቀሙበት እያዩ በዝምታ አለፉ። ወንድማቸው በእኩል ሲካፈሉ እሳቸው በዝምታ ዕድላቸውን አሳለፉት ። ይህኔ ከሁለት ያጣ የሆኑት በለጡ በሁኔታው በእጅጉ አዘኑ። የባለቤታቸው ግዴለሽነት ከልብ አበሳጫቸው። ከአባትም ከአማትም ቤት ያላገኙትን በረከት እያሰቡ ዕድላቸውን ረገሙ፣ባላቸውን ኮነኑ። ይህን ቅያሜ መነሻ አድርገው ልባቸው የሸፈተው በለጡ በአገራቸው መኖር፣ መቀመጥ አስጠላቸው። ጊዜ ወስደው አርቀው አለሙ ፣ ብዙ ተመኙ ፣ ያሰቡትን ሊያደርጉት፣ሊፈጽሙት ቆረጡ።

በለጡ የመጀመሪያ ልጃቸውን ታቅፈዋል። ባል ከጎናቸው ባይኖሩም ትዳራቸው አዲስና የሚያጓጓ ነው ። እንዲያም ቢሆን ከፍቷቸዋል። ጠዋት ማታ መንገድ ያሰበው ልባቸው አርፎ አልተቀመጠም ። ከዕለታት በአንዱ ቀን የህሳባቸውን ሊሞሉ መኪና ተሳፍረው አዲስ አበባ ደረሱ።

### የገጠሯ ወይዘሮ

ወቅቱ የአጼ ኃይለ ሰላሴ ዘመን ነው። እንደአሁኑ ከተማ ባይሰፋም ፣ ከገጠር ለመጡት ወይዘሮ ሁሉም አዲስና አስገራሚ ነበር ። በለጡ አዲስአበባ ሲገቡ በዕድሜ ወጣት ናቸው ። ለአገሩ ባዳ፣ ለሰዉ እንግዳ ቢሆኑም በወቅቱ የንጉሱን ሚስትና የልጃቸውን ሀዘን ታድመዋል። የዛኔ የእነሱን ሞት ተከትሎ በየቦታው የነበረ ለቅሶ ከዛሬው ይለያል። በገጠር፤ በከተማ፣ በገበያ በመንደሩ ህዝቡ ሀዘኑን በምሬት ይገልጻል ። እሳቸው በጊዜው የነበረው የለቅሶ ስርዓት ደንብና ወግን የተከተለ እንደነበር አይዘነጉም ። ይህ ሁሉ እውነት የበለጡ የልጅነት ትዝታ ነው።

አሁን ወይዘሮዋ አስቀድመው ከተማ ከመጡት ባላቸው ጋር ኑሮን ዳግም ጀምረዋል ። ከተማ እንደ ገጠር አይደለም። አኗኗሩ ይለያል ። መኖሪያና በቂ ገንዘብ ማግኘት የግድ ነው ። ከሰዎች ፣ ከአካባቢው መግባበት፣ መላመድን ይጠይቃል ። ባል ከገቡበት ሥራ በሳምንት ስድስት ብር ይከፈላቸዋል።

በወቅቱ ገንዘቡ ጥሩ ዋጋ ነበረው ። የሚገኘው ገቢ ተጠራቅሞ የወር ቀለብ ይሸምታል፣የቤት ኪራይ ይከፍላል። የጎደለውን ሞልቶ ስለነገው ይቆጠባል። እንዲያም ሆኖ በለጠች ቁጭ አላሉም ። ጎጂቸውን ለማቅናት ቤታቸውን ለመሟላት ከአረቄ፣ ከጠላው ይሉ ነበር ። አረቄና ጠላቸውን የሚወዱ ደንበኞች የእጃቸውን ሙያ እየሻቱ ይጎበኟቸዋል። ወይዘሮዋ ከጣሳ ጠላው አስርሳንቲም፣ ከጠርሙስ አረቄው ሀምሳ ሳንቲም ይቀበላሉ።

አሁን በለጡና የአዲስ አበባ ህይወት በወጉ ተላምደዋል። የልጅነት ባለቸው ከጎናቸው ሆነው ያግዟቸዋል። በለሙያዋ ወይዘሮ ኑሮን ለማሸነፍ ህይወትን ለማሳመር ሌት ተቀን ይለፋሉ። ውሎ እያደር የቤተሰብ ቁጥር መጨመር ይዟል። አንድ የነበረው ልጅ በእህት ወንድም ተከቧል ።

በየጊዜው ቤተሰቡ ሲጨምር ፍላጎት ያይላል፣ የሚበላው ፣ የሚለብሰው ይበዛል፣ የሚፈልግ የሚጠይቅ ይበረክታል። ሆድን ሞልቶ ኑሮን ለማሸነፍ ደግሞ ልጆች ለሆድ እንጂ ለስራ አልደረሱም። በላይ በላይ የሚወለዱት ህጻናት የወላጆችን እገዛ ይሻሉ። ለሚበሉት፣ ለሚለብሱት፣ ለሚኖሩበት ሁሉ ግዴታው በእናት አባት ትከሻ ወድቋል።

### የአስራ አንድ ልጆች እናት- በለጠች

አሁን ወይዘሮ በለጠች በልጆች ተከበዋል። አንድ ብለው የጀመሩት መውለድ ተበራክቶ ከአስራ አንድ ልጆች እናት አድርጓቸዋል። ኑሮ ልፋት እየጠየቀ፣ ህይወት በፈተና እየተሞላ ነው። ልጆች ማደግ ሲጀምሩ ፍላጎታቸው በርክቷል። በለጠችና ባለቤታቸው ኑሮን ለማሸነፍ በሩጫ ላይ ናቸው። አንዳንዴ ባሰቡት መዋል አይገኝም፤ ይሆናል ያሉት ተለውጦ ካልታሰበው ይጥላል። ይበጃል ይሉት ተቀይሮ ቤት በፈተና ይሞላል ። በበለጠች ህይወት ያለፈው እውነትም ይኼው ነው።

ከወለዷቸው አስራአንድ ልጆች አምስቱን በየጊዜው በሞት አጥተዋል። በየሰበቡ የልጅ ሞት ቢያጠቃቸው በሆነው ሁሉ ማዘናቸው አልቀረም ። ዛሬ ላይ ሲያስቡት ግን ፈቃዱን ሁሉ ለፈጣሪያቸወ ያሳልፋሉ። በተቀሩት ፍሬዎች ተጽናንተውም ነገን በተስፋ ያስባሉ። በለጠች ቤተሰባቸውን ለማኖር ያልሞከሩት የለም። በቀን ሰራተኝነት የአናጺ ረዳት ሆነዋል። በጽዳት ስራ ህንጻዎችን ዞረው ጠርገዋል።

ትራንስፖርቱ ከዛሬው ሲታይ ወጪው ትንሽ ይመስላል። የዛኔ የእለቱን ማግኘት ግን ቀላል አልነበረም። በለጠች ካሰቡት ለመድረስ ረዥሙን መንገድ በእግራቸው አቋርጠዋል ። ሲያገኙ በታክሲ ቢሞክሩም አብዛኛው ጉዞ የጉልበታቸው ነው ። ቤታቸው ሲገቡ ሰውነታቸው ይዝላል፣ አቅማቸው በድካም ይፈተናል። እንዲያም ሆኖ ለራሳቸው ስንፍናን አያሳዩም። ስራ ካሏቸው ባገኙበት ገብተው እንጀራቸው ያደርጉታል።

### የትዳር- ወስምታ

የበለጠችና ባለቤታቸው ትዳር የሚጀምረው ከልጅነት ዕድሜ ነው። ደጋግመው እንደሚናገሩት ከእሳቸው ውጭ ሌላ ሰው አያውቁም ። ክፉ ደጉን፣ ሀዘን ደስታውን ያለፉበት ጎጆ አስራ አንድ ልጆችን አፍርቷል። ሁለቱም ባተሌ ሆነው ቤት አቅንተዋል፣ ልጆችን በእኩል አሳድገዋል። ባለቤታቸው ከልጅነት እስከ ዕውቀት ከጎናቸው አልራቁም። ጥንዶቹ ከገጠር ወጥተው ከተማን በመረጡ ጊዜ በሀሳብ አንድ ሆነው ዘልቀዋል።

አንዳንዴ የአባወራው የስራ ባህርይ ከቤት ያርቃል። የመስራት ዕድሉን ባገኙ ጊዜ እንጀራ ፈላጊው አባት ቤተሰቦቻቸውን ትተው ከሌላ ቦታ ይከርማሉ። አስፈላጊ ከሆነ ወራት የሚያሰቆጥር ቆይታ ይኖራቸዋል። ይህ ልማድ በእሳቸውና በቤተሰቡ ዘንድ ሲመላለስ የኖረ እውነት ነው።

በአንድወቅት አባወራው ከቤት ከአካባቢ የሚያርቅ ስራ ተገኘላቸው። ይህን ዕድል ማለፍ ያልፈለጉት ሰው እንደልማዳቸው ቤተሰቡን ተሰናብተው ወደታሰበው ስፍራ አቀኑ። አባወራው ካሉበት ስራውን ጀምረው ወራት አስቆጠሩ ። ቦታው የተስማማቸው ይመስላል። በቶሎ ሳይመጡ ጊዚያት ተቆጠሩ። ለስራ መሄዳቸውን የሚያውቁት በለጠችና ልጆቻቸው መመለሳቸውን እየናፈቁ ጠበቋቸው ። እንደታሰበው አባወራው አልመጡም ። ጥቂት ቆይቶ ከቤተሰቡ ጆሮ አንድ ወሬ ደረሰ። አባወራው ከሌላ ሴት ጋር ኑሮ መያዛቸው ታወቀ።

ይህን እውነት የሰሙት ልጆች አባታቸውን አጥብቀው ተቃወሙ። ከዚህ ዕድሜ በኋላ ከሌላ ጎጆ ትዳር መያዛቸውን ሲያውቁ ከልብ አዘኑ። ይህ ቆይታ እምብዛም አልቀጠለም። አባወራው ያደረባቸው ህመም አልጋ አስያዛቸው። ከፉኛ መታመማቸውን ሲያውቁ ወደ ቤት ሊመለሱ ግድ ሆነ ። በለጠች የልጅነት ባለቸውን የልጆቻቸውን አባት ባዩ ጊዜ አልጨከኑም። ከነችግራቸው ተቀብለው ማስታመም፣ መንከባከብ ያዙ።

አባወራው ከደጓ ባለቤታቸው እጅ ወድቀው የህመም ጊዜያቸውን ገፉ። አስታማሚዋ በለጠች በሆነው ሁሉ ሳይከፉ ፣ ባፈጸሙት በደል ቂም ሳይዙ ባላቸውን ደገፉ። እንደልፋታቸው አልሆነም። ባል ከሞት አላመለጡም ። አንድ ማለዳ ህይወታቸው ማለፉ ተሰማ ። ወይዘሮዋ በደላቸውን ሳያስቡ፣ መካዳቸውን ሳይቆጥሩ አባወራቸውን በክብር ሸኑ።

### ኑሮን ከልጆች ጋር

ከሞት የተረፉት ሰድስቱ የበለጡ ልጆች በራሳቸው ዓለም ይኖራሉ። ሁሉም የግል ህይወት ሲያሮጣቸው ይውላል። በለጠች የማረፊያ ዕድሜ ላይ ቢገኙም የልጅ እጅን አልናፍቁም። አሁን ባሉበት አቅም ሮጠው፣ ደክመው ማደርን ይሻሉ። በእርግጥ ከድካም የሚያሳርፍ ፣ ‹‹አለሁሽ›› የሚል ልጅ ቢኖራቸው አይጠሉም። ልጆቹ ግን ይህን ያስቡ አይመስልም። የእሳቸው ጥንካሬም ለዚህ አይነቱ እገዛ የሚጋብዝ አልሆነም። ሁሌም ከልጆቻቸው ፊት ቀድመው መገኘት ልማዳቸው ሆኗል።

ከልጃቸው መሀል አንደኛዋ በክፉ ደግ ከጎናቸው አትርቅም። ሰርታ ካገኘችው ሁሉ የእጇን ታቃምሳቸዋለች፣ አንዳንዴ እናትና ልጅ ባለመግባባት ይጋጫሉ። ጠብ ኩርፊያቸው ግን ዕድሜ አይፈጅም ። ትንሽ እንደሚያማት የሚያውቁት በለጠች ሁሉን በትዕግስት ችለው ያልፋሉ ። በእሳቸው የማትጨክነው ልጅም መልካም በዋለች ቁጥር የእናት ምርቃት ይደርሳታል ።

ካሉት ወንዶች ልጆች አንደኛው በውትድርና እንደዘመተ አልተመለሰም። ይሙት ይኑር ያላወቁት እናት ለዓመታት ደጁን ሲናፍቁ ኖረዋል። እሱን ሲያስቡ አለ ብለው አይደሰቱም፣ ሞቷል ሲሉም ተስፋ አይቆርጡም። በተጋጩ ስሜት ሲዋልሉ ኖረዋል ።

ቀሪዎቹ ሁለት ወንዶችም እናታቸውን ሊጦሩ አልታደሉም ። በተለይ አንደኛው ጥሩ የእጅ ሙያ ከእሱ ጋር ነው። ስራ የተባለውን አሳምሮ ለመጨረስም የሚያህለው የለም። በሚያገኘው ገንዘብ ግን ለእናቱም ሆነ ለራሱ አይበጅም ። ገቢውን ለካቲካላ አውሎ በስካር ሲንገዳገድ ይገባል። ሌሎቹም ራሳቸውን ከመርዳት ባለፈ ለእናታቸው ጓዳ የሚተርፍ አቅም የላቸውም ።

እንዲህ መሆኑ እናት በለጠችን ፈጽሞ አያስከፋም ። ልጆቹ ራሳቸውን ችለው ማደራቸው ብቻ በቂ መሆኑን አምነው ፈጣሪን ያመሰግናሉ። ‹‹ዳሳሼ›› የሚሏት ሌላዋ ሴት ልጃቸው የልጅ ልጆች አሳይታቸዋለች። አንዳንዴም ብቅ እያለች ጓዳቸውን ትጎበኛለች ፣ ጎናቸውን ትዳብሳለች ። በለጠች በዚህ ደስ ይላቸዋል።

### በለጠችን በዘንድሮ

ወይዘሮዋና የዘንድሮ ኑሮ ውድነት በግንባር ተፋጠዋል። ዛሬ ምንም ነገር በቀላል ዋጋ የሚገኝ አልሆነም። ገበያ ወጥተው ባዶ እጃቸውን የሚመለሱበት ጊዜ ይበረክታል። እሳቸው ካገኙ በልተው፣ ካልሆነም ‹‹ተመስገን›› ብለው ማደርን ለምደዋል። ብዙ ቤተሰብ ያላቸውን ባዩ ጊዜ ግን ልባቸው ከልቡ ይሰበራል ።

በለጠች አብዝተው ቡና ይወዳሉ። ቀድሞ በቀን ሶስቴ አፍልተው መጠጣት ልምዳቸው ነበር ። አሁን ይህን ቢተውም አንዳንዴ ከእጃቸው ማጣት የዕለቱ ልምድ ሊቀርባቸው ይችላል። እንዲህ ሲገጥማቸው የቀድሞ ጎረቤቶቻቸውን ያሳታውሳሉ። እነሱ ዛሬ ከጎናቸው የሉም። ሁሉንም በሞት አጥተዋል። ይህ ክፉ አጋጣሚ ዛሬን ብቸኛ አድርጎ በትናንት ትዝታ ያመላልሳቸዋል።

አሁን እንደቀድሞው በጉርብትና የሚቀርቡት የለም። በአጋጣሚው ከሌሎች ቢገናኙም ኑሯቸው ከእነሱ ስለማይመስል አብሮነትን አይመርጡም። እንዲህ መሆኑ ገለልተኛ አድርጎ ለብቻ አኑሯቸዋል። በአጼው ዘመን ያገኙት መኖሪያ ቤት ‹‹የቀበሌ›› የሚል ስያሜ ተችሮት በዝቅተኛ ክፍያ እየኖሩበት ነው። በዓመት ስልሳብር ይከፍሉበታል። በቤታቸው ዓለም ደስተኛ ናቸው። ወይዘሮዋ ዕድሜያቸው ቢገፋም ስራ ካሏቸው ወደኋላ አይሉም። ዛሬም ቢሆን ሰርተው ማደር፣ ሮጠው ማረፍን ይመርጣሉ።

በለጠች አመስጋኝ ሴት ናቸው። ዛሬም ከአንደበታቸው ‹‹ተመስገን›› ይሉት ቃል ተደጋግሞ ይሰማል። የጌጃ ሰፈሯ ወይዘሮ በዕድሜያቸው ማምሻ የሰው እጅ ላለማየት ፣ ከራስ ጋር ትግል ጀምረዋል። አስራአንድ ልጆች ወልደው ሰድስቱ በህይወት ቢኖሩም ከራሳቸው በላይ ለራሳቸው የቅርብ ደራሽ አላገኙም። በልጆቻቸው አለመጦር ፣ አለመደገፋቸው ፈጽሞ አያሳዝናቸውም። ሁሉም ለራሱ እንጂ ለሰው አልተፈጠረም የሚል ዕምነት አላቸው ።

እሳቸው በሆነባቸው ሁሉ ተጨንቀው አያውቁም። ዛሬን በምስጋና እየተሻገሩ የነገዋን ጸሀይ ዳግም ለማየት በንቃት ይነሳሉ። ህይወት ማለት፡- ለእመት በለጠች ራስን አሸንፎ መታየት ነው። ህይወት ማለት፡- ለብርቱዋ ሴት ዛሬን በትጋት መስራት ነው። ህይወት ለእሳቸው በልፋት ድካም የሚቀድሙት፣ የሚያሸንፉት ትግል ነው ። ለበለጠች፣ ለክንደ ብርቱዋ ዕድሜ ጠገብ ወይዘሮ።